DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



# የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) የወላጆች መመሪያ

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች | dcps.dc.gov

ኤፕሪል 2016

# እኛ DCPS ፒኤስ በመሆናችን ይህን ልንሰራው እንችላለን!




## ታላቅ ቁርጠኝነት

ተግባራችን በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፣ ማንነትን ወይም ሁኔታዎችን ሳይመለከት ሁሉንም ተማሪዎቻችንን ለኮሌጅ፣ ለስራና ለህይወት ስኬታማነት የሚያዘጋጅ፣ ለዓለምአቀፍ ደረጃ የሚመጥን ትምህርት መስጠት መቻሉን ማረጋገጥ ነው።

አምስት ታላላቅ ግቦች አሉን፡-

1. የስኬታማነት ደረጃን ማሻሻል
   ቢያንስ 70 በመቶ ተማሪዎቻችን በንባብ ችሎትና ሂሳብ ትምህርት ከፍተኛ ክህሎት ያላቸው ይሆናሉ፤ እንዲሁም የዲስትሪክቱን ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር በእጥፍ እናሳድጋለን።
2. ደከም ያሉ ትምህርት ቤቶችን አቅም ለማጎልበት ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግ
   40 ያህሉ ደከም-ያሉ ትምህርት ቤቶቻችን የብቃት ደረጃ ወደ 40 በመቶ ነጥቦች ከፍ ይላል።
3. የምሩቃንን ቁጥር ማሳደግ
   ዘጠነኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች መካከል ቢያንስ 75 በመቶ ያህሉ በአራት ዓመት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ይመረቃሉ።
4. እርካታን ማሻሻል
   90 በመቶ ያህሉ ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን እንደሚወዱት ይመሰክራሉ።
5. የተመዝጋቢዎችን ቁጥር መጨመር
   የ DCPS የተመዝጋቢ ተማሪዎችን ቁጥር በዓመታት ሂደት ያሳድጋል።

*የDCPS የወላጆች መመሪያ የሚያካትታቸው መረጃዎች፣ ወላጆችና ቤተሰቦች የትምህርት ቤት ስርዓቱን ለመረዳት የሚያስፈልጉዋቸውን ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችንና ተግባራትን ይጨምራል። ሆኖም ሁሉን-ዓቀፍ የ DCPS ፖሊሲዎችንና ተግባራትን ለማያካተት ያልታሰበ ከመሆኑም በላይ፣ እንደየሁኔታው ሊለወጥ የሚችልም ነው። ይሄ የመመሪያው ሶስተኛ እትም ሲሆን፣ በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የተካተቱት መረጃዎችም ከ2015-2016 የትምህርት ዓመት ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው።*

*የሽፋን ፎቶው ለልጃችው ትምህርት ከፍተኛ ቁርጠኝነትን ያሳዩት፣ የዲቦራ ብራውን፣ እና የቅድመ-መዋእለ-ህጻናት-3 (PK-3) ተማሪ የሆነው፣ የአማሪ ሊትል ፎቶ ሲሆን፣ በብራዎኒ ትምህርት ካምፓስ በትምህርት ቤት መከፈቻ የመጀመሪያው ቀን የተነሱት ነው።*

## የ DCPS ከአድሎ-ነጻ የመሆን መግለጫ

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ሁሉም ሰራተኞቹ በፌዴራልና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢ ከአድሎ-ነጻ የመሆን ህግጋት መሰረት የሚሰሩ መሆናቸውን የማረጋገጥ ቁርጠኝነት አለው፤ እነዚህም ህግጋት የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ የ1964 የሲቪል መብቶች ህግ ርዕስ 6 እና 7፤ የ1967 የአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ ያለው የእድሜ አድልዎ፤ የ1975 የእድሜ አድልዎ ህግ፤ የ 1972 የትምህርት ህግ ማሻሻያዎች ርዕስ 9፤ የ1973 የመልሶ መቋቋም ህግ ክፍል 504፤ የ1990 አካል ጉዳትያለባቸው አሜሪካውያን ህግ፤ አካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ህግ፤ የ1977 የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሰብአዊ መብቶ ህግ፤ እንዲሁም የ2008 የጄኔቲክ መረጃ ከአድሎ-ነጻ ህግ ።

በመሆኑም DCPS በሰራተኞች፣ በስራ አመልካቾች ወይም በተማሪዎች ላይ ዘር፣ ቀለም፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ ጾታ (እርግዝናን ጨምሮ)፣ እድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ አካላዊ ገጽታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ስርዓተ-ጾታዊ ማንነት ወይም መገለጫ፣ ቤተሰባዊ ሁኔታ፣ ቤተሰባዊ ሃላፊነቶች፣ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና (ማትሪኩሌሽን)፣ ፖለቲካዊ አባልነት፣ ዝርያዊ መረጃ፣ አካል-ጉዳተኛነት፣ የገቢ ምንጭ፣ በቤተሰቦች መካከል ወይም በመኖሪያ ወይም በስራ ቦታ የሚከሰት ግጭት ሰለባነትን መሰረት አድርጎ አድሎ የማይፈጽም ወይም እነዚህን መሰረት አድርጎ የሚፈጸም አድሎን የማይቀበል ነው።

በተጨማሪም DCPS ከላይ በተዘረዘሩት በህግ የተጠበቁ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ትንኮሳን ወይም ማንገላታትን የሚከለክል ከመሆኑም በላይ፣ አንድ ግለሰብ የተፈጸመበትን ወይም የተፈጸመባትን አድሎ አስመልክቶ አቤቱታ በማሰማቱ ወይም በማሰማቷ ምክንያት፣ ወይም የአድሎ ክስ በመመስረቱ ወይም በመመስረቷ፣ ወይም በአድሎ ምርመራ ወይም የህግ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በመሆኑ ወይም በመሆኗ ምክንያት የሚፈጸምበ/ባትን የበቀል እርምጃ ይከላከላል።

በእንደዚህ ባሉት የተከለከሉ የአድሎ፣ የትንኮሳ ወይም የማጉላላት፣ ወይም የብቀላ ተግባራት ላይ ተሰማርተው የተገኙ ሰራተኞች የዲስፒሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

የአካል-ጉዳተኛነትን በተመለከተ የተፈጸመ አድሎ ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆችና አሳዳጊዎች ለሚከተለው አካል ያሳውቁ፦

ኮሊን ቢሾፕ (Colin Bishop)
Section 504 Coordinator
Office of Specialized Instruction
District of Columbia Public Schools
1200 First St, NE, 9th Floor
Washington, DC 20002
202.442.5485

*ወይም*

D.C. Office of Human Rights
441 4th Street, NW, Suite 570N
Washington, D.C. 20001
202.727.4559

ጾታዊ አድሎን በተመለከተ ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆችና አሳዳጊዎች ለሚከተለው አካል ያሳውቁ፦

ሄዘር ሆላደይ (Heather Holaday)
Title IX Coordinator
Office of Teaching and Learning
District of Columbia Public Schools
1200 First St, NE, 8th Floor
Washington, DC 20002
202.645.6073

*ወይም*

Assistant Secretary for Civil Rights
U.S. Department of Education
Office for Civil Rights
400 Maryland Avenue, SW
Washington, D.C. 20202-1100
Telephone: 1.800.421.3481
TDD: 877.521.2172
FAX: 202.245.6840
Email: OCR@ed.gov

አድሎን በተመለከተ ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆችና አሳዳጊዎች፣ እንዲሁም ሌሎች የ DCPS ቅሬታ ማሰሚያ ሂደቶችንም መጠቀም ይችላሉ። የወላጆች፣ አሳዳጊዎችና ጠያቂዎች መከተል ያለባቸው ሂደቶች ቅጂዎች ከ http://dcps.dc.gov/page/dcps-notice-non-discrimination ማግኘት ይቻላል። አድሎን በተመለከተ ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆችና አሳዳጊዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ለሚከተለውን አካል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፦

Assistant Secretary for Civil Rights
U.S. Department of Education
Office for Civil Rights
400 Maryland Avenue, SW
Washington, D.C. 20202-1100
Telephone: 1.800.421.3481
TDD: 877.521.2172
FAX: 202.245.6840
Email: OCR@ed.gov

ወይም

D.C. Office of Human Rights
441 4th Street, NW, Suite 570N
Washington, D.C. 20001
202.727.4559

# የይዘት ማውጫ

## ከቻንስለሩ የተላለፈ መልእክት ....6

## እናንተን የመሳሰሉ ወላጆችና ቤተሰቦች ጠቃሚ ስለመሆናቸው ....7

## በ DCPS መመዝገብ ....10

- የክልላችሁ ውስጥ ትምህርት ቤት
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምዝገባ ውሳኔ መወሰን
- የትምህርት ቤቱ ዲሲ ሎተሪ
- የቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ፒኬ3 (PK3) እና ፒኬ4 (PK4) ሎተሪ
- የከአካባቢ-ውጭ ሎተሪ (Out-of-Boundary Lottery) (ክፍሎች ኬ-12) (Grades K-12))
- ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ቁልፍ የምዝገባ ቀናት

## ከ DCPS የሚጠበቁ ነገሮች ....14

- የክፍል ተሳትፎ (Attendance)
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ፖሊሲ
- የአለባበስ ስርዓት
- የትምህርት ቤት መርሃ-ግብር
- ቅድም-እና-ድህረ-ትምህርት ፕሮግራሞች
- ተራዛሚ ቀን
- አትሌቲክስ
- የምግብ አገልግሎት
- ጤናና ደህንነት
- ሌሎችን ሰላም መንሳት (Bullying)
- የዲሲፒሊን ፖሊሲዎች
- መጓጓዣ
- የትምህርት ቤቶች የድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ መዘግየት ወይም መዘጋት
- የትምህርት ቤት ጉብኝት ፖሊሲ

### አካዳሚያዊ አቅርቦት እና መስፈርት ....23

- የህጻንነት ትምህርት (Early Childhood Education PK3-PK4)
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (ክፍሎች K-5) አካዳሚያዊ አቅርቦት
- የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ክፍሎች 6-8) አካዳሚያዊ አቅርቦት
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ክፍሎች 9-12) አካዳሚያዊ አቅርቦት
- ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውርና በትምህርት ገበታ ላይ ማስቀጠል
- ለምረቃ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች (መስፈርት)
- የናቪያንስ/ወላጅ ጥምረት (Naviance/Family Connections)
- የክሬዲት አከፋፈል
- ምዘናዎች
- የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መመሪያ ተፈጻሚነት መሻሪያ (“ማንኛውም ህጻን ከትምህርት ወደኋላ መቅረት የለበትም”)
- ደረጃ 1 ትምህርት ቤቶች

### የተማሪ ድጋፍ ፕሮግራሞች ....39

- 500 ለ 500፦ በንባብ አማካኝነት ማስጠናት
- የክረምት ትምህርት
- የተማሪዎቸ ምደባ
- አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
- ባለሁለት ቋንቋ ትምህርት/እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች
- የሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ባይሴክሹዋል፣ ትራንስጀንደር እና (Lesbian, Gay, Bisexual, Transgender) የጠያቂ ተማሪዎች ድጋፍ
- ነፍሰጡርና ልጅ ያላቸው ተማሪዎች
- የችግረኛ ህጻናት ፈንድ/ወደ ስኬት መሸጋገሪያ ድልድይ
- ቤትአልባ ወጣቶች
- የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችና ልዩ ልዩ ምንጮች

## በተደጋጋሚ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ....48

## የማእከላዊ ጽሕፈት ቤት ቢሮዎች ዝርዝር....53

## የተለመዱ ምህጻር-ቃላት....55

## አባሪ፡ የትምህርት ቤት አካዳሚያዊ አቅርቦት....58

# ከቻንስለሩ የተላለፈ መልእክት



*Kaya Henderson*
*Chancellor*
*DC Public Schools*

## የተከበራችሁ የተማሪ ወላጆች እንዲሁም ቤተሰቦች፣

ዲሲፒኤስ ወደ ላቀ ምእራፍ እየተሸጋገረ ነዉ! ከተማሪዎች ቅበላ ጀምሮ እስከ ተመራቂ ተማሪዎች ቁጥር፣ እንዲሁም የተማሪዎች የእርካታ ደረጃን ስንመዝን የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤት ወደ ላቀ ምእራፍ እየተሸጋገረ ነዉ! እንዲህም ሆኖ፣ አሁንም ከእኛ ብዙ የሚጠበቅ መሆኑን ለአፍታ እንኳን አንዘነጋም፤ የትምህርት ቤቶቻችንን ሁኔታ ለማሻሻል ከእናንተ ከወላጆች እና ከቤተሰቦች ጋር አብረን እየሰራን ባለነዉ ስራ ኩራት ይሰማኛል፡፡

የዘንድሮዉ የትምህርት ዘመን ሲጠናቀቅ በ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በቻንስለርነት ለአምስተኛ ዓመት ያገለገልኩበት ጊዜ በመሆኑ ዘንድሮም ለሶስተኛ ጊዜ ከእናንተ ከተማሪ ወላጆች እና ቤተሰቦች ጋር ሆኜ የወላጆች መመሪያ ጽሁፍን በመጋራቴ ደስ ተሰኝቻለሁ፡፡ የወላጆች መመሪያ ጽሁፍ ተጠቅማችሁ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የህዝብ ትምህርት ቤቶችን የእለት ተእለት ተግባራት፣ እንዲሁም የሚመሩበትን ፖሊሲ እና አሰራር እንድትመረምሩ አሳስባለሁ፡፡ በጽኁፉ ተጠቅማችሁ በትምህርት ገበታቸዉ ላይ ስለተገኙ፣ የቅበላ አቅማችንን እና ስለ ትምህርት አማራጮች ጠቃሚ መረጃ እንድታገኙ እጋብዛችኋለሁ፡፡

ይህ ጽሁፍ በትምህርት ቤቶቻችን ለተማሪዎች የምናቀርባተቸዉን የትምህርት ዘርፎች፣ አይነት እና ስብጥር ይበልጥ ለማጎልበት ጠቃሚ መሳሪያ ሆኖ ያገለግለናል፡፡ እናንተም እንደወላጆች እና ቤተሰቦች፣ ልጆቻችሁ ሁሌም የተሻሉ ብሎም ጎበዝ ተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ ልታበረታቷቸዉ እና ልትደግፏቸዉ ይገባል እያልኩ፣ በየጊዜዉ የሚኖራቸዉ ግብ ከፍ እንዲል የበኩላችሁን አስተዋጽዎ ታበረክቱ ዘንድ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡ በዚህም መሰረት በአሁኑ ሰዓት በአለማችን ላይ ባለዉ ፉክክር እና ውድድር የበዛበት ሁኔታ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ ተተኪ ትውልዶችን ለማፍራት እንችል ዘንድ ከፍተኛ ችግር የተጋረጠባቸዉን ተማሪዎች፣ በተለይም በቆዳ ቀለማቸዉ ምክኒያ ለመገለል እና ለመድሎ የተጋለጡትን ለመርዳት ቆርጠናል፡፡

ይህንን አላማችንን ለማሳካት ደግሞ የእናንተ እገዛ ሊታከልበት ይገባል፣ እናም ከእናንተ ጋር ተቀናጅተን በመስራታችን ልባዊ ኩራት የተሰማኝ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ፡፡ ለአሁን ብቻ ሳይሆን ለመጪ ትውልዶች ጭምር የምንኮራበትን የትምህርት ስርአት እንፈጥር ዘንድ ከእናንተ ዘንድ የምናገኘዉ ግብረ- መልስ ቁልፍ ነዉና እንደተለመደዉ ግብረ -መልስ ትሰጡን ዘንድ ከአደራ ጭምር አሳስባችኋለሁ፡፡

በዚህ ጽፍ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የወላጆች እና የህዝብ ጥምረት አስተባባሪ ጽ/ቤቱን ያነጋግሩ፣ አድራሻችን ፡- Office of Family and Public Engagement ስልክ ቁጥር፡ 202.719.6613 ወይም በኢሜይል፡- ofpe.info@dc.gov.

ከአክብሮት ጋር፣
ካያ ሐንደርሶን (Kaya Henderson)



ቻንስለር

# እርስዎን የመሳሰሉ ወላጆችና ቤተሰቦች ጠቃሚ ስለመሆናቸው



# እርስዎን የመሳሰሉ ወላጆችና ቤተሰቦች ጠቃሚ ስለመሆናቸው

## ወላጆች የልጆቻቸው የመጀምሪያዎቹና እጅግ ጠቃሚዎቹ አስተማሪዎች ናቸው። ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ ሲሆኑ፣ ተማሪዎች ከፍተኛው አቅማቸው ላይ ለመድረስ የመቻላቸው አጋጣሚ የላቀ ይሆናል፤ ለዚህም ነው በቤተሰብና በትምህርት ቤት መካከል ጥብቅ አጋርነትና ግንኙነት መኖር አስፈላጊ የሚሆነው።

ከቤተሰብ ተሳትፎ ትምህርት ቤቶችም ተጠቃሚዎች ናቸው። ከተሻለ የንባብ ውጤት ጀምሮ የላቀ የትምህርት ቤት ደህንነትን እስከማረጋገጥ ድረስ፣ ተሳታፊ ወላጆች፣ ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ መሆን ይችሉ ዘንድ ትምህርት ቤቶች ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዘው መጓዝ እንዲችሉ ያግዛሉ። ቤተሰቦችና ትምህርት ቤቶች በአጋርነት ሲሰሩ፣ የሚከተሉት ራእዮቻችን እውን ሲሆኑ ማየት እንችላለን፦

- የተማሪዎች ስኬት መጨመር፤
- ተማሪዎች ለትምህርት የሚኖራቸው ጥረትና አመለካከት መሻሻል፤
- የተማሪዎች ማህበራዊ ኪሂሎት መሻሻልና አጓጉል ባህርያት መቀነስ፤
- ከትምህርት ቤት አቋርጦ የመውጣት ደረጃ መቀነስ፤ እና
- ከፍተኛ የምረቃ መጠን።

ሁሉም ወላጆች ስለልጆቻቸው አካዳሚያዊ መረጃዎችን ማግኘት መቻላቸውን ምረጋገጥ ጠቃሚ በመሆኑ፣ ወላጆች በመጀምሪያ ቋንቋቸው መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ለማስቻል፣ DCPS በስልክ መስመር ነጻ የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል። ይህንንም የቋንቋ ስልክ መስመር 202-727-4559 በመደወል ማግኘት ይቻላል። "የመናገሪያ" ካርዶችንም በተለያዩ ቋንቋውዎች ከ http://ohr.dc.gov/ispeakcards ማውረድ ይቻላል።

ከአስተርጓሚ ጋር በግምባር ለመነጋገር፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር ቢያንስ ከሶስት ቀናት አስቀድሞ፣ የአስተርጓሚ መጠየቂያ ቅጽ በመሙላት ለቋንቋ ማግኛና እድገት ጽህፈት ቤት ማቅረብ ይኖርበታል። የትርጉምና የአስተርጓሚ አገልግሎት ማግኘት የሚፈልጉ ወላጆች ትምህርት ቤቱን ባስቸኳይ ማነጋገር ይኖርባቸዋል።

## በቤት የትምህርት ድጋፍ

- ልጅዎት በየቀኑ በትምህርት ገበታ ላይ በሰዓቱ መገኘቱ/ቷንና በቂ እረፍት ማግኘቱ/ቷን ያረጋግጡ።
- ልጅዎት በእሱ/እሷ ላይ እምነት እንዳልዎትና ከፍተኛ የስኬት ደረጃ ላይ እንደሚደርስ/እንደምትደርስ እንደሚጠብቁ ማወቁን/ማወቋን ያረጋግጡ። የልጆችዎ ጉዳይ የርስዎ ጉዳይ መሆኑን እንዲያውቁ ያድርጉ፦ ስለምን እየተማሩ እንደሆነ ይጠይቋቸው፤ ወደ መስክ አብረዋቸው ይሂዱ፤ በማንኛውም ክዋኔዎቻቸውና ስፖርታዊ ውድድሮቻቸው ላይ ይገኙ፤ ወዘተ.።
- ልጅዎት ከሁሉ የትምህርት ዓይነቶች መሀከል የትኛውን የበለጠ እንደሚወድ/እንደምትወድ ይጠይቁ። እነዚህን ፍላጎቶቻቸውን ከልጆችዎ ራእዮችና ከትምህርት ቤት ከሚማሯቸው ነገሮች ጋር የጠበቀ ህይወታዊ ቁረኝት በመፍጠር የበለጠ ያበረታቷቸው፤ ያሳድጓቸው።
- የልጅዎን የትምህርት እርምጃና እድገት ይከታተሉ። ለምሳሌ፣ ልጆችዎ የተሰጧቸውን የቤት ስራ ወይም ፕሮጀክቶች ናሙና እንዲያሳዩዎት የጠይቋቸው፤ የቤት ስራዎቻቸውን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማጠናቀቃቸውንና ማስረከባቸውን ያረጋግጡ፤ ልጆችዎ የትኛውን የትምህርት ዓይነት የበለጠ እንደሚወዱ/ወይም እንደሚከብዳቸው ይጠይቋዋቸው። ስለ ልጅዎት ያልዎትን ምልከታና አስተያየት ከመምህራኑ ጋር ለምነጋገር ግንኙነት ይፍጠሩ።
- ለንባብ ጠቀሜታ አጽንኦት ይስጡ። ለልጅዎ ያንብቡላቸው፤ ቤተመጽሃፍቱን ይጎብኙ፤ እናም ስለምን እንደሚያነቡ ከልጆችዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ለልጆችዎ ጸጥታና በቂ ብርሃን ያለበት የጥናትና የቤት ስራ መስሪያ ስፍራ ያዘጋጁላቸው።
- ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም ስርዓት እንዲያዳብሩ ይርዷቸው። ለትምህርታቸውና ለቤተሰብ፣ ለጨዋታ፣ ለስፖርትና ሌሎችም ከትምህርት ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች የተመጣጠነ ጊዜ እንዲኖራቸው ያድርጉ።
- ልጆችዎት በስክሪን ላይ (ለምሳሌ፣ በቲቪ፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት) የሚመለከቷቸውን ነገሮች ይከታተሉ፤ ገደብም ያብጁላቸው።

## በትምህርት ቤት መማርን መደገፍ

- በተቻለ መጠን ሁሉ፣ በትምህርት-ነክ እንቅስቃሴዎች ላይ መገኘትና መሳተፍ ይገባል። በመስክ ጉዞ፣ በስርዓተ-ትምህርት-ነክ ምሽቶች፣ በሂሳብ ወይም የንባብ ምሽቶች፣ ማህበረሰባዊ አገልግሎት ሁነቶችና ልዩ ከዋኔዎች ላይ መገኘት። በተጨማሪም፣ ልጅዎትን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ልጆች የሚደግፉበትን ልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ለመፍጠር፣ መምህራን እነዚህን የመሳሰሉ ልዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት ሂደት ለማገዝ ፈቃደኛ ይሁኑ።
- ስለልጆችዎ ሙብትና ደህንነት ተሟጋች ይሁኑ። ስለ ልጅዎ ያልዎትን ዓላማና ግቦች ለመምህራኑ በማሳወቅ፣ በልጅዎ ትምህርት ውስጥ አጋር ለመሆን ዝግጁነትዎን ያሳዩ።
- በወላጅና-መምህራን ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ከልጅዎት መምህራን ጋር ዘወትር ይነጋገሩ። ልጅዎ በዚህ ዓመት በደንብ ሊማራቸው/ ልትማራቸው ስለሚያስፈልጉት/ሚያስፈልጓት ክህሎት፣ በትምህርት ቤትም ሰላለው/ላላት እንቅስቃሴና እርስዎ ማገዝ የሚችሉበትን መንገድ የተመለከቱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። መረጃ በመለዋወጥ የቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነትን ያጠናክሩ።

**ምክር ለወላጆች**

*እድሜያቸው ምንም ያህል ቢሆን፣ የልጆቻችሁ ትምህርትና እድገት የርስዎን ትኩረት ይፈልጋል። ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ልጆች ጭንዎ ላይ አስቀምጠው ሲያነቡላቸውና በመማሪያ ክፍላቸው ሲገኙላቸው ደስ ይላቸዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የቤት ስራቸውን ከእርስዎ ጋር በጋራ መስራትንና ለስብሰባ ወይም ለተግባራዊ ክዋኔ ወደ ትምህርት ቤታቸው ሲመጡላቸው ደስ ይላቸዋል። የመካለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የእርስዎን በትምህርት ቤት መገኘት ወይም የቤት ስራ የመስራት ድጋፍ ያን ያህል ላይፈልጉት የችላሉ፤ በተለይም ጥሩ የጥናት ልምድ ያዳበሩ ከሆነ። ከዚህ ይልቅ፣ የመካለኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ለምረቃ የሚያበቃቸው ትክክለኛው መንገድ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የእርስዎን እርዳታ ይፈልጋሉ። ስለ ወደፊቱ ህይወታቸው ከእርስዎ ጋር የመነጋገሪያ ጊዜም ይፈልጉ ይሆናል።*

## በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚቻል

- በልዩ ልዩ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ላይ በመገኘት ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ለመተዋወቀ ። የልጆቻችሁ እድሜ ምንም ያህል ቢሆን፣ ወላጆች እርስ በርስ መደጋገፍ ትችላላችሁ።
- አዳዲስ ወላጆች ወደ ትምህርትር ቤት እንዲመጡና ስለ ትምህርት ቤቱ እንዲያውቁ ለመርዳት የወላጅ ምክር ፕሮግራም መጀመር።
- የወላጅ ቡድን አባል ይሁኑ (ለምሳሌ፣ የወላጅ-መምህር ማህበር፣ የወላጅ-መምህር ድርጅት (PTA, PTO) ወይም ትምህርት ቤቱ እስካሁን ምንም የወላጅ ቡድን የሌለው ከሆነ እርስዎ ይጀምሩ። የወላጅ ቡድኑን ትኩረት የተማሪዎችን ስኬት ለማሻሻል ከሚረዱ የትምህርት ቤቱ ግቦች ጋር በሚቀናጁ ልዩ ልዩ እንቅሴዎችና ሁነቶች ላይ ማድረግ።
- ትምህርት ቤቱ በክፍል ውስጥ ትምህርት እገዛ ለማድረግ የበጎ-ፈቃደኝነት እድሎች እንዳሉትና እንደሌሉት ይጠይቁ።
- በአካባቢ የትምህርት መማክርት ቡድን (LSAT) ዲሪክቴሩን የተማሪዎችን ስኬትና እደርስበቶች ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ በመምከር ያገልግሉ።
- የዲሲን ስቴት የትምህርት የበላይ አስተዳደር (OSSE) ቢሮ የትምህርት ቤት ሪፖርት በመቃኘት (ይኸውም ከ www.learndc.org ይገኛል) ከዲሪክቴሩና ሌሎች ወላጆች ጋር ይነጋገሩበት።
- በዲሲ ስቴት የትምህርት ቦርድ ስብሰባ ላይ ይገኙ። ስለ ስብሰባው ሰዓቶች ለማወቅ በስልክ ቁጥር 202-741-0888 በመደወል ይጠይቁ።

# በ DCPS መመዝገብ



# በ DCPS መመዝገብ

አንዳንድ ጊዜ የትምህርት ቤት ምዝገባ በርካታ ቀናትንና ፎርሞችን ማስታወስን ስለሚጠይቅ አድካሚና አታካች ሊመስል ይችላል። ይህንኑ ቀላል ለማድረግ የሚጠቅሙ ጥቂት መረጃዎች ከታች ቀርበዋል።

- የክልላችሁ ውስጥ ትምህርት ቤት
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምዝገባ ውሳኔ መወሰን
- የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ
- ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 (PK3) እና ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4 (PK 4) ሎተሪ
- የከአካባቢ-ውጭ ሎተሪ (Out-of-Boundary Lottery) (ክፍሎች ኬ-12) (Grades K-12))
- ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
- ቁልፍ የምዝገባ ቀናት

## የክልላችሁ ውስጥ ትምህርት ቤት

እያንዳንዱ/ዷ ህጻን በመኖሪያ ቤቱ አድራሻ መሰረት በሁሉም መደበኛ የትምህርት ክፍሎች (K-12) የሚመደብበት ትምህርት ቤት አለው/አላት። እያንዳንዱ/ዷ ህጻን ከቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ጀምሮ በሰፈሩ አካባቢ ትምህርት ቤት የመማር መብት አለው/አላት። የልጅዎን የመኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ለማወቅ፣ http://dcatlas.dcgis.dc.gov/schools ይጎብኙ።

ከቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ጀምሮ በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ለመማር፣ ለትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ (My School DC lottery) ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልግም። በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ፣ አስፈላጊውን የምዝገባ ፓኬት ለትምህርት ቤቱ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህን የማድረጊያ ጊዜው እንደሚከተለው ነው:-

- በልግ (Spring):- የምዝገባ ፓኬት ይመጣል።
- የዓመቱ የመጨረሻ የትምህርት ቀን:- የምዝገባ ፓኬቱን ለአካባቢዎ ትምህርት ቤት ማስረከብ ያስፈልጋል።

በሽግግር ክፍሎች (በተለይም 5ተኛና 6ተኛ) በትምህርት ላይ ያሉ ከአካባቢያቸው ውጭ ባሉ ትምህርት ቤቶች የሚማሩተን ጨምሮ የ DCPS ተማሪዎች፣ ባሉበት ትምህርት ቤት አካባቢ ባለ ቀጣዩ "መዳረሻ ትምህርት ቤት" ገብተው የመማር መብት አላቸው። በቀጣዩ የመዳረሻ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ የምዝገባ ፓኬት ለትምህርት ቤቱ ማስገባት ያስፈልጋል። ቀጣዩን የመዳረሻ ትምህርት ቤትዎን ለማወቅ፣ እባክዎት በሚከተለው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደረ-ገጽ ውስጥ የሚገኘውን የአሁኑን ትምህርት ቤትዎን ፕሮፋይል በ profiles.dcps.dc.gov ይመልከቱ።

## በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምዝገባ ውሳኔ መወሰን

ልጅዎ በአካባቢዎ ትምህርት ቤት ወይም በቀጣዩ የመዳረሻ ትምህርት ቤት ገብቶ/ታ እንዲማር/እንድትማር፣ ወይም ያሉትን ሌሎች አማራጮች ለማወቅ ይፈልጉ ይሆናል። ያሉትን ልዩ ልዩ አማራጮች ለመመርመር የሚከተሉትን ይጠቀሙ:-

- የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎች:- የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎች፣ ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቱ ያሉትን ልዩ ልዩ አካዳሚያዊ አማራጮችና የመርጃ ምንጮች መገንዘብ ይችሉ ዘንድ ለመርዳት የተዘጋጁ ናቸው። እያንዳንዱ ፕሮፋይል፣ አካዳሚያዊ ፕሮግራምን ጨምሮ፣ ስለ ትምህርት ቤቱ ስፖርታዊና ከስርዓተ-ትምህርቱ በተጓኝ ያሉትን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን፣ እንዲሁም የትምህርት ቤቱን አካዳሚያዊ ብቃትና እድገት መመዘኛ ካርድን፣ የድህንነትና የቤተሰብ ተሳትፎን የሚመለከቱ አጫጭር መግለጫዎችን ያካትታል። የትምህርት ቤት ፕሮፋይሎችን በ profiles.dcps.dc.gov ማግኘት ይቻላል።
- ክፍት ቤቶች: ክፍት ቤቶች ለቤተሰቦች ትምህርት ቤቶችን ለመጎብኘትና ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር መስተጋብር ለመፍጠር እድል ይሰጣሉ። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የጉብኝትና የጥያቄ መልስ ጊዜያት ይመድባሉ። ለተጨማሪ መረጃ ትምህርት ቤቱን ማነጋገር ወይም የትምህርት ቤቱን ድረ-ገጽ መመልከት (በትምህርት ቤቱ ፕሮፋይል ገጽ ላይ የሚገኘውን) ይቻላል። በተጨማሪ በሚከተለው የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን የክፍት ቤቶች ዝርዝርም መመልከት ይቻላል http://dcps.dc.gov/page/open-house።
- ትምህርት ቤት-ነክ ክስተቶች:- ትምህርት ቤቶችም በመማር ላይ ለሚገኙና በቀጣይ ለመማር ሊመዘገቡ ለሚችሉ ተማሪዎች ቤተሰቦች ማህበረሰባዊ ሁነቶችን ማዘጋጀት ይችላሉ። እንዲህ ያሉት ሁነቶችም ከሙዚቃ ኮንሰርትና ፌስቲቫል ጀምሮ ትምህርት ቤቶችንና ፕሮግራሞቻቸውን እስከማስተዋወቅ ዝግጅቶች የሚደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ ሁነቶች ላይ መገኘት ስለ ትምህርት ቤቱ ባህል ለማወቅ ከመርዳቱም በላይ፣ በቀጣይ ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ቤተሰቦች፣ አሁን በመማር ላይ ካሉ ተማሪዎች ወላጆች ጋር ለመተዋወቅ እድል ይሰጣል። ስለ ቀጣይ ሁነቶች ዝግጅቶች ለማወቅ ከፈለጉ፣ ትምህርትር ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።
- የዲሲ ትምህርታዊ ፌስቲቫል፡ የዲሲ ትምህርታዊ ፌስቲቫል፣ አሁን በመማር ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ወላጆችና በቀጣይ ሊመዘገቡ ለሚችሉ ተማሪዎች ወላጆች በዲሲ ውስጥ የትምህርት ቤት-ምርጫን በተመለከት ስላሉ አማራጮች ሁሉ ለማወቅ እድል ለመስጠት በዲሲ ትምህርት ቤቴ (My School DC) የሚዘጋጅ ሁነት ነው። ከዲሲ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ተወካዮች ለተማሪዎች ቤተሰቦች ስለ ትምህርት ቤቶቻቸው ተጨማሪ መረጃዎችን ለመስጠትና ጥያቄዎቻን ለመመለስ ሲሉ በትምህርታዊ ፌስቲቫሉ ዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

## የዲሲ ትምህርት ቤቱ ሎተሪ

ከአካባቢያቸው ውጭ ወይም ከተመጋጋቢ ትምህርት ቤቶች ውጭ ባሉ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶችና ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ መብት በሌሏቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ወላጆች ለሚፈልጉት ትምህርት ቤት የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሎተሪ የሚገቡ ማመልከቻዎች በሶስት ይከፈላሉ፡-

- ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 እና ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4
- የከአካባቢ-ውጭ ሎተሪ (Out-of-Boundary Lottery) (ክፍሎች ኬ-12) (Grades K-12))
- ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።

የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻ በድረ-ገጽ ቀጥታ-መስመር (online) ብቻ የሚካሄድ የማመልከቻ ሂደት ነው። ስለ ትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻ ወይም ሂደት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ MyschoolDC.org. ይጎብኙ። ማመልከቻውን ለመሙላት እርዳታ ካስፈለግዎት፣ የምዝገባ ቡድንን በስልክ ቁጥር 202-478-5738 ወይም በኢሜል አድራሻ ማግኘት ይችላሉ። enroll@dc.gov.

## ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 (PK3) እና ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4 (PK4) ሎተሪ

የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እድሜያቸው 3 እና 4 ለሆኑ ህጻናት የመማሪያ ቦታዎች ይሰጣል። ምንም እንኳን ህጻናት በቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 ወይም ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4 እንዲመዘገቡ በህግ የማይገደዱ ቢሆንም፣ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለቅድመ-ልጅነት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። በእነዚህ ክፍሎች በተቻለ መጠን ፍትሃዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለበርካታ ህጻናት ቦታዎችን ለማዘጋጀት ጥረት እናደርጋለን። ለልጆቻቸው በቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 ወይም 4 ውስጥ ቦታ ማግኘት የሚፈልጉ ሁሉም ወላጆች ለትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው። የቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 እና 4 ማመልከቻ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር MyschoolDC.org ላይ ብቻ ይገኛል።

## የከአካባቢ-ውጭ ሎተሪ (Out-of-Boundary Lottery) (ክፍሎች ኬ-12) (Grades K-12)

የከመኖሪያ አካባቢ ውጭ ሎተሪ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለወላጆች ልጆቻቸውን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ውጭ ባሉ ትምህርት ቤቶች ከመዋእለ-ህጻናት-12ኛ ክፍሎች (Grades K-12) ውስጥ ባሉ ክፍት ቦታዎች ውስጥ ለማስመዝገብ እንዲችሉ እድል ለመስጠት የሚዘጋጅ የትምህርት-ቤት ምርጫ አገልግሎት ነው። ልጅዎት ከመኖሪያ አካባቢ ውጭ ባለ ትምህርት ቤት ማስመዝገብ ከፈለጉ፣ በድረ-ገጽ-ቀጥታ-መስመር ላይ በሚገኝ ለትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ በኩል ማመልከቻ ማስገባት ይኖርቦታል። የከአካባቢ-ውጭ ትምህርት ቤቶች ሎተሪ ማመልከቻዎች የሚገኙት በድረ-ገጽ-ቀጥታ-መስመር MyschoolDC.org ብቻ ነው።

ከአካባቢ-ውጭ ባለ ትምህርት ቤት ውስጥ በሎተሪ ቦታ የሚያገኙ ተማሪዎች በዚያ ትምህርት ቤት እስከ መጨረሻው ክፍል ድረስ ("terminal grade") ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ፤ ከዚያም በቀጣዩ የመዳረሻ ትምህርት ቤት ለድጋሚ ሎተሪ ማመልከት ሳያስፈልጋቸው ትምህርታቸውን ማከታተል ይችላሉ። ከመኖሪያ አካባቢ-ውጭ ባለ ትምህርት ቤት ተመዝግበው የሚማሩ ተማሪዎች በየዓመቱ የምዝገባ ፓኬት መሙላት እንደሚኖርባቸው ማስታወስ ይገባል።

## ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የ DCPS ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚወሰን የቅበላ ሂደት ተማሪዎችን ይመርጣሉ። ከቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3/4 እና ከመኖሪያ አካባቢ-ውጭ ትምህርት ቤትሎተሪዎች በተለየ መልኩ፣ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ልዩ የሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ቅበላ በሎተሪ እድል ላይ የተመሰረተ አይደለም። ባንጻሩ፣ ተማሪዎች ወደ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ገብተው ለመማር የተወሰኑ መመዘኛዎችን ማሟላትና/ ወይም ተቀባይነት ለማግኘት ተጨማሪ ተግባራትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ስለ ዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ልዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቅበላ ሂደት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ፣ የትምህርት ቤቱን ድረ-ገጽ (በትምህርት ቤቱ profiles.dcps.dc.gov የሚገኘውን) ወይም MyschoolDC.org ይመልከቱ።

ለዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ልዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻ ማስገባት ከፈለጉ፣ በቅድሚያ በድረ-ገጽ-ቀጥታ-መስመር MyschoolDC.org. ማመልከቻ ማስገባት አለቦት። የዲሲ ትምህርት ቤቴን ማመልከቻ ከሞሉ በኋላ፣ ተማሪዎች የቅበላ ፈተና፣ ቃለ-መጠይቅ ወይም የተግባር ክዋኔ እንዲያሟሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። ምንም እንኳን የከፍተኛ ክፍሎች ቦታዎች ውስን ቢሆኑም፣ ከ9-12ተኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች ማመልከት ይችላሉ።

የ DCPS ልዩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- Benjamin Banneker Academic High School
- Columbia Heights Education Campus
- Duke Ellington School of the Arts
- McKinley Technology High School
- Phelps Architecture, Construction, and Engineering High School
- School Without Walls Senior High School.

ማስታወሻ፡- ይህን የተወሰነ የማመልከቻ ሂደት በሌሎች ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ልዩ-ባልሆኑት) ገብቶ ለመማር ማሟላት አያስፈልግም።

## ቁልፍ የምዝገባ ቀናት

ወላጆች በየትምህርት ዘመኑ ከምዝገባ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዓበይት በርካታ ቀናት ልብ ብለው ማስታወስ ይኖርባቸዋል። የሚከተለውን የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድረ-ገጽ ይመልከቱ dcps.dc.gov/enroll ወይም የትምህርት ቤቱ የመጨረሻ የምዝገባ ቅን እንዳያመልጥዎት ከትምህርት ቤቱ ጋር በመነጋገር ያረጋግጡ።

- የዲሲ ትምህርት ቤቴ ማመልከቻ (ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3-12 ክፍሎች) በዚህ የትምህርት ዘመን ዲሰምበር ወር ይጀመራል።
- የዲሲ ትምህርት ቤቴ ማመልከቻ (ከ3-12 ክፍሎች) በዚህ የትምህርት ዘመን ፌብርዋሪ ወር ያበቃል።
- የዲሲ ትምህርት ቤቴ ማመልከቻ (ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3-8 ክፍሎች) በዚህ የትምህርት ዘመን ማርች ወር ይጀመራል።
- የመጪው ዓመት የምዝገባ ፓኬት በዚህ የትምህርት ዘመን ኤፕሪል ወር ይገኛል።
- በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ቦታ ላገኙ ተማሪዎች የምዝገባ ፓኬት በዚህ የትምህርት ዘመን ሜይ ወር ይገኛል።

ማስታወሻ፡- በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት ልጅዎን ለማስመዝገብ፣ በየትምህርት ዘመኑ የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅቦታል። ለተሟላ የምዝገባ ፓኬትና ተቀባይነት ያላቸው የነዋሪነት ማረጋገጫ ሰነዶች ዝርዝር፣ የዲሲን የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድረ-ገጽ dcps.dc.gov/enroll ይመልከቱ።



# በDCPSምን መጠበቅ ይቻላል



# በDCPS ምን መጠበቅ ይቻላል

ለDCPS ነባርም ሆኑ አዲስ ወላጅ፣ ስለ DCPS ማወቅ የሚገባዎ ጥቂት “መሰረታዊ” ጉዳዮች እዚህ ተጠቅሰዋል።

- የክፍል ተሳትፎ (Attendance)
- የሁለተኛ ደረጃ ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ፖሊሲ
- የአለባበስ ስርዓት
- የትምህርት ቤት መርሃ-ግብር
- ቅድም-እና-ድህረ-ትምህርት ፕሮግራሞች
- ተራዛሚ ቀን
- አትሌቲክስ
- የምግብ አገልግሎት
- ጤናና ደህንነት
- ሌሎችን ሰላም መንሳት (Bullying)
- የዲሲፕሊን ፖሊሲዎች
- መጓጓዣ
- የትምህርት ቤቶች የድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ መዘግየት ወይም መዘጋት
- የትምህርት ቤት ጉብኝት ፖሊሲ

## የክፍል ተሳትፎ (Attendance)

እድሜያቸው ከ5-18 ዓመት የሆናቸው ተማሪዎች ሁሉ መደበኛ ትምህርት እንዲከታተሉ የዲሲ ህግ ያስገድዳል። ህግ ባያስገድድም እንኳን፣ እድሜያቸው 3 እና 4 ዓመት የሆናቸው ህጻናትም በመደበኛነት ትምህርት መከታተላቸው አስፈላጊ ነው። በትምህርት ገበታ ላይ በየቀኑና በሰዓቱ መገኘት እጅግ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ፣ ከመዋእለ-ህጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባለ የመማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው። ልጆች እያደጉና እራሳቸውን እየቻሉ ሲሄዱ እንኳን፣ ቤተሰቦች ልጆቻቸው በመደበኛነት ትምህርት ገበታቸው ላይ መገኘታቸውን ቅድሚያ የሚሰጡት ተግባር መሆኑን የማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ።

አንዳንድ ጊዜ ከትመህርት ቤት መቅረት የግድ የሚሆንበት ሁኔታ ቢኖርም፣ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ብዙ ጊዜ ከቀረ/ች (በቂ ምክንያት ቢኖርም ባይኖርም)፣ በትምህርቱ/ቷ ወደኋላ ሊቀር/ልትቀር ይችላል/ትችላለች። ተማሪዎች በተደጋጋሚ ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ከሆነ፣ ወይም በአንድ ዓመት 18 ወይም ከዚያም በላይ ቀናት ከቀሩ፣ ስኬታማ መሆናቸው በጣም አጠራጣሪ ነው።

ከተመደበው የአንድ ቀን ትምህርት ክፍለ-ጊዜያት ውስጥ ከ20% በላይ የሚሆነውን ያልተከታተሉ ተማሪዎች፣ በህጉ መሰረት ቀኑን ሙሉ ቀሪ እንደሆኑ ይቆጠራሉ።

ልጆችዎ በሎተሪ በከአካባቢ ውጭ ትምህርት ቤት ቦታ አግኝተው ተቀባይነት በሌለው ምክንያት 10 ቀናት ከቀሩ ወይም 20 የማርፈድ ጥፋቶች ካሉባቸው፣ በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት እንዲመለሱ ሊደረጉ ይችላሉ።

**ይህን ያውቁ ኖሯል?**

- በመዋእለ-ህጻናትና አንደኛ ክፍል በተደጋጋሚ ቀሪ የሚሆኑ ተማሪዎች፣ በሶስተኛ ክፍል መጨረሻ ላይ በክፍል ደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን ያህል የንባብ ችሎታ ሊኖራቸው የመቻል እድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው።
- በስድስተኛ ክፍል በተደጋጋሚ ቀሪ መሆን፣ ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት አቋርጠው የመውጣት አደጋ ላይ መሆናቸውን አመላካች ምልክት ነው።
- በዘጠነኛ ክፍል፣ በመደበኛነት በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ከስምንትኛ ክፍል ፈተና ወጤቶች በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የምረቃ ደረጃ ይጠቁማል።

የተፈቀዱ ቀሪዎች የሚባሉት ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ተቀባይነት/ህጋዊ ባላቸው ምክንያቶችና በወላጆች ይሁንታ ከትምህርት ቤት ሲቀሩ ነው።

ለቀሪነት ህጋዊ ምክንያቶች የሚባሉት በዲሲ ከተማ ደንቦች (DCMR) ምእራፍ 21 ውስጥ ተጠቅሰዋል (http://dcregs.dc.gov/)፤ እነዚህም ከታች የተጠቀሱትንና ያልተጠቀሱትንም ሌሎች ምክንያቶች የጨምራሉ፦

- የተማሪው/ዋ መታመም ወይም ህክምና-ነክ ጉዳይ (ተማሪው/ዋ አምስት ቀንና ከዚያም በላይ ቀናት ቀሪ ከሆነ/ች፣ የሂኪም ማስረጃ ያስፈልጋል)፤
- የተማሪው/ዋ የሂኪም ወይም የጥርስ ህክምና ቀጠሮ፤
- በተማሪው/ዋ የቅርብ ቤተሰብ ውስጥ ሞት ካጋጠመ፤
- በተላላፊ በሽታ ምክንያት ወይም በሌላ ጤና-ነክ ቁጥጥር ምክንያት፣ ወዘተ. ከትምህርት ቤት ውጭ መደረግ፤
- እያንዳንዱ ተማሪ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ምስክር፣ ወይም ከህዝብ የሚመረጡ ችሎት ሰሚ ዳኞች ቡድን አባል (juror) ሆኖ/ና ማገልገል ይኖርበታል/ባታል፤
- የሃይማኖታዊ በዓል አከባበር፤
- በህግ ከትምህርት ቤት ውጭ ስለመደረግ ወይም በትምህርት ቤት ውሳኔ ስለመባረር፤
- በአየር ንብረት መዛባት፣ በአደገኛ ሁኔታዎች ወይም በሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ምክንያት የትምህርታዊ አገልግሎቶች ጊዜያዊ መዘጋት፤

- ህጋዊ ሀላፊነት እያለበት የዲሲ መጓጓዣ ማቅረብ አለመቻል፤
- ተማሪዎች ወላጃቸውን/አሳዳጊያቸውን ለወታደራዊ አገልግሎት ከመጠራታቸው በፊት፣ በተጠሩበት ጊዜ ወይም ከተጠሩ በኋላ ለማየት፤ እና
- በወረዳው የትምህርት ቤት አስተዳደር በተረጋገጠ የድንገተኛ አደጋ ወይም መሰል ሁኔታ ጊዜ።

ልጅዎ ከትምህርት ቤት ቀሪ ከሆነ/ች በኋላ ተመልሶ/ሳ በሚመጣበት/በምትመጣበት ጊዜ፣ ለትምህርት ቤቱ አስተባባሪ ቢሮ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የቀሪ ክትትል ሃላፊ በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወሻ ማስገባት ይጠበቅቦታል። ማስታወሻው የልጅዎን ስም፣ ከትምህርት ቤት የቀረባቸውን/የቀረችባቸውን ቀናት፣ የመቅረት ምክንያትና የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ ማካተት አለበት። በህመም ምክንያት ከአምስት ተከታታይ ቀናት በላይ ቀሪ ከሆነ/ች፣ የኪም ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል። ያለበቂ ምክንያት ወይም ማስረጃ ወይም ተቀባይነት በሌለው ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት "ይቅርታ" የማይደረግለት ይሆናል።

ቀሪው አስምን በመሳሰሉ መዳኛ በሌላቸው የጤና ችግሮች ምክንያት የተፈጠረ ከሆነ፣ ወላጆች የትምህርት ቤቱን ነርስ በማነጋገር ለልጃቸው አስፈላጊው የጤና ክትትል እቅድ እንዲዘረጋ ማድረግ መቻል አለባቸው።

በትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ http://dcps.dc.gov/page/student-attendance-and-support የሚለውን ድረ-ገጽ መመልከት ወይም የልጅዎን ትምህርት ቤት ማነጋገር።

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ፖሊሲ

የDCPS አዲሱ የሁለተኛ ደረጃ የውጤትና ሪፖርት አሰጣጥ ፖሊሲ ከ6-12ኛ ክፍሎች ላሉ ተማሪዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ሲሆን፣ ይህም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትክክለኛና ፍትሃዊ ደረጃ መጠበቂያዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው። የDCPS ለሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ኮርሶች ይህን አንድ ዓይነት የፈተና ውጤት አሰጣጥ ስርትዓት የፈጠረው፣ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ውጤት ማግኘት የሚችሉባቸው የመመዘኛ ደረጃዎች ተመሳሳይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው።

ይህ ፖሊሲ፣ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ስራዎች መዝነው ውጤት እንዲሰጡ፣ ውጤቱንም እንዲለጥፉና የታረሙ ፈተናዎች ውጤቶችንም ተማሪዎቹ ስራቸውን ባስረከቡ አስር የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ ለተማሪዎች እንዲመልሱ ስለሚያስገድድ፣ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው የትምህርት እርምጃ የተሻለ መረጃ ማግኘት ያስችላቸዋል።

በፖሊሲው መሰረት አሁን እያንዳንዱ ትምህርት ቤትም ይህንኑ ኤሌትሮኒክ ውጤት ማስተላለፊያ በመጠቀም ለወላጆች ስለ ልጆቻቸው እርምጃ በየሳምንቱ መረጃ ይሰጣል። ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ትምህርት እርምጃ ለመከታተል ማድረግ ያለባቸው የምስጢር ቁልፋቸውን (ፓስዎርድ) በመጠቀም ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተመደበውን አንድ ሲስተም ገብተው ማየት ብቻ ነው። ተማሪዎች ወይም ወላጆች በሪፖርት ካርድ ላይ ስለ ተለጠፈው ውጤት ቅሬታ ካላቸው፣ ለትምህርት ቤታቸው ውጤቱ እንዲስተካከልላቸው ማመልከት ይችላሉ። ሁሉም ውጤት-ነክ ማመልከቻዎችና የውጤት ለውጥ ጥያቄዎች በትምህርት ቤት ደረጃ የሚጀምሩ ናቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## የአለባበስ ስርዓት

የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ዩኒፎርም አለባበስ ስርዓት በተመለከተ አስገዳጅ ፖሊሲዎችን እንዲነድፉና ስራ ላይ እንዲያውሉ ለዳይሬክተሮች ልዩ ስልጣን ይሰጣል። ዳይረክተሮች ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም እንዲለብሱ ማስገደድ ባይፈልጉም እንኳን፣ የልጅዎ አለባበስ በትምህርት ቤቱ የአለባበስ ስነስርዓት መሰረት ንጹህና ንጽህናን የተላበሰ፣ እንዲሁም ተገቢነት ያለው እንዲሆን ይገደዳል። የትምህርት ቤቱን የአለባበስ ስነስርዓት ወይም መደበኛ ዩኒፎርም የመልበስ ፖሊሲ የሚያጓድሉ ተማሪዎች ተከታታይ የዲሲፕሊኒ እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

የልጅዎ ትምህርት ቤት መደበኛ ዩኒፎርም ያለው መሆን ስላለምሆኑ ማወቅ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ። ከአለባበስ ስነስርዓት ጋር ተያያዥነት ባለው የተማሪዎች መብትና ግዴታ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ፣ ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ ወይም የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይመልከቱ http://1.usa.gov/1LgWQSg።

## የትምህርት ቤት መርሃ-ግብር

የትምህርት ክፍለ-ጊዜያት እንደ ክፍሉ ወይም የትምህርት ደረጃው ይለያያሉ።

- ከቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3-5ተኛ ክፍሎች፣ ልጅዎ በጠቅላላው ቀኑን ሙሉ በአንድ ክፍል ውስጥ ከአንድ አስተማሪ ጋር ይቆያል/ትቆያለች። እድሚያቸው እየጨመረ ሲሄድ፣ ተማሪዎች ለተመረጡ ትምህርት ዓይነቶች (ለምሳሌ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት) እና አጋዥ ልምምዶች (ለምሳሌ ንባብ) ወደ ሌላ መምህር ሊዛወሩ ይችላሉ።
- ከ6-12ተኛ ክፍሎች፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የክፍለ-ጊዜ ደወል መሰርት ከአንድ የትምህርት ዓይነት መምህር ወደ ሌላው ይዟዟሯሉ። የትምህርት ክፍለ-ጊዜያት አብዛኛውን ጊዜ በ45 እና 90 ደቂቃዎች መሀከል የሚሆን እርዝማኔ፣ እንዲሁም ለ9 ወይም 18 ወይም 36 ሳምንታት ያህል ይካሄዳሉ። እንደየትምህርት ቤቱ የጊዜ ሰሌዳ፣ ተማሪዎች በቀን ከአራት እስከ ሰባት ሊሚደርሱ ክፍለ-ጊዚያት ሊማሩ ይችላሉ።

ስለ ልጅዎ ትምህርት ቤት የጊዜ ሰሌዳ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካስፈለግዎት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።

## ቅድም-እና-ድህረ-ትምህርት ፐሮግራሞች

ቅድመ-ትምህርት ፐሮግራሞች በያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚዘጋጁ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎነ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

ልጅዎ ትምህርታዊ፣ የማበልጸጊያና ደህንነት ውሁድ የሆኑ ተግባራትን አካቶ በሚሰጥ ድህረ-ትምህርት ፐሮግራም ውስጥ መሳተፍ ይችላል/ትችላለች። ከፍተኛ ጥራት ባላቸው የድህረ-ትምህርት ፐሮግራሞች ውስጥ መሳተፍ በትምህርት ቤት ትምህርትን የመከታተል ደረጃን፣ ትምህርታዊ ስኬትን፣ የምረቃ መጠንንና ለትምህርት አዎንታዊ አመለካከትን ለማሻሻል እንደሚረዳ ጥናቶች በተጨባጭ ያመለክታሉ። የተማሪዎችን ግላዊና ማህበረ-ስሜታዊ ኪሂሎትን ለማሻሻልም ይረዳሉ።

የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (ዲሲ .ህ.ት.ቤ.ት.) የከትምህርት-ቤት ውጭ ጊዜ ፐሮግራሞች ጽህፈት ቤት (OSTP)፣ ከማህበረሰብ-ምስርት ድርጅቶችና የዲሲ ህ.ት.ቤ.ት. መምህራንና ረዳቶች ጋር በመተባበር፣ ልዩ ልዩ የድህረ-ትምህርት ፐሮግራም እድሎችን ይሰጣሉ። እነዚህም ፐሮግራሞች አብዛኛውን ጊዜ ከሰኞ እስከ ዓርብ (ግማሽ ቀን ብቻ ትምህርት ከሚስጥባቸው ቀናት፣ እንዲሁም ከበዓላትና የእረፍት ዝግ ውጭ) ከ3:30 ፒ.ኤም. – 6:00 ፒ.ኤም. ይካሄዳሉ። ሆኖም ሰዓቶቹ እንደየትምህርት ቤቱ የሚለያዩ ከመሆናቸውም በላይ፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች በየከትምህርት-ቤት ውጭ ጊዜ ፐሮግራሞች ጽህፈት ቤት (OSTP) የሚመሩ ድህረ-ትምህርት ፐሮግራሞች አሏቸው ማለት አይደለም። በነዚህ ፐሮግራሞች ውስጥ ለሚሳተፉ ተማሪዎች የመጓጓዣ አገልግሎት አይሰጥም። ይህም ዘወትር ወደ ትምህርት ቤትና ወደ ቢታቸው በአውቶብስ የሚጓዝ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ይጨምራል። ነጻ መክሰስ/ካትረን ይሰጣል።

## ተራዛሚ ቀን

ተራዛሚ ቀን ማለት ከዘወትሩ የትምህርት ቀን የበለጠ ርዝማኔ ያለው፣ ከጠዋቱ 8:45 ኤ.ኤም - 3:15 ፒ.ኤም. የሚካሄድ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከ1-2 ሰዓታት ያህል ተጨማሪ የትምህርት ጊዜያት ያሉትና ከ4:15-5:15 ፒ.ኤም. ባሉት ሰዓታት የሚጠናቀቅ ይሆናል። ይህም ለተማሪዎች ተጨማሪ በትምህርት ገበታ ላይ የመቆያ ጊዜ የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ፣ ለመምህራንም ተጨማሪ የማስተማሪያ ጊዜ በመስጠት የተማሪዎችን ትምህርታዊ ስኬት የበለጠ ለማሻሻል እንደሚረዳ በተግባር የታየ ነው። የተራዛሚ ቀን ዋና ዓላማ በተመረጡ የDCPS ለተማሪዎች ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ በመስጠት፣ የመማር አቅማቸውን ማጎልበትና የትምህርታዊ ስኬት ደረጃቸውን ማሻሻል ነው። ይህም የትምህርት ጊዜ ተማሪዎችን በመደበኛው የትምህርት ክፍለ-ጊዜያት በሚያስተምሩ የትምህርት ይዘት መምህራን የሚሰጥ ሲሆን፣ የትምህርቱን ጊዜ ተራዛሚነት ለመጠበቅ ሲባልም ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ የሚደረግ መዟዟር አይኖርም። ተራዛሚ ክፍለ-ጊዜያት የመደበኛው ትምህርት ቀን አካል በመሆናቸው ያለምንም ቀሪ መከታተል የግድ ነው። ስለ ተራዛሚ ቀናት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካስፈለግዎት የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## አትሌቲክስ

አትሌቲክስ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች ጠቃሚ አካል ነው። በመሆኑም፣ ከ4-12ተኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች በልዩ ልዩ ትምህርታዊና የስፖርት ክለቦች መካከል በሚደረጉ ውድድሮች መሳተፍ ይችላሉ።

### *ይህን ያውቁ ኖሯል?*

አትሌቲክስ ለሚከተሉት ይረዳል፦

- ለማደግና እድገትን ለማፋጠን፤
- ማህበራዊ፣ ተዝናኖታዊና የአመራር ክሂሎትን ለማዳበር፤
- የጠቃሚ ዜጋ ባህርያትንና ስፖርታዊ ጨዋነትን ለማዳበር፤ እንዲሁም
- ተማሪዎች በመልካም ትምህርታዊ ድባብ ውስጥ የማደግ ችሎታቸውን ለማካዝ።



ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው በሌለ ስፖርት ውስጥ መሳተፍ ከፈለጉ፣ በሌላ የDCPS ባለው ስፖርቱ ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። ተማሪዎቹ ሊሳተፉበት የሚፈልጉት የስፖርት ቡድን አሰልጣኙን በማነጋገር እና በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ዲሬክቴሮች መካከል በሚደረግ ስምምነት ቡድኑን መቀላቀል ይችላሉ። ለዚህም የአትሌቲክሱ ዲሬክቴር አስፈላጊ የሆነውን ሰነድ የማዘጋጀት ስራ ያከናውናል።

አንዳንድ የአትሌቲክስ ፕሮግራሞች የክለብ ተደርገው ስለሚቆጠሩ ትምህርት-ነክ ስፖርታዊ ውድድር አይደሉም። የክለብ ስፖርቶች ከትምህርታዊ ስፖርቶች ጋር ተመሳሳይ የጤና ጥቅማጥቅምና የኢንሹራንስ ሽፋን የማይሰጡ በመሆናቸው፣ ለሊግ ሻምፒዮና ውድድሮችም ብቁ አይደሉም። የልጅዎ አትሌቲካዊ ፕሮግራም ትምህርታዊ ወይም የክለብ ስፖርት ስለመሆን አለመሆኑ ማወቅ ከፈለጉ፣ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

በማንኛውም የአትሌቲክስ ፕሮግራም ውስጥ ከመሳተፍ አስቀድሞ የሚከተሉት ፎርሞች መሞላት አለባቸው፦

- በአትሌቲክስ የመሳተፍ ፈቃድ ፎርም
- የአካላዊ ምርመራ ፎርም
- የድንገተኛ አደጋ ጊዜ መረጃ የተፈረመ ፎርም

እነዚህን ሁሉ ፎርሞች ከሚከተለው የድረ-ገጽ ቀጥታ-መስመር ማግኘት ይቻላል http://dcps.dc.gov/service/athletics።

ልጅዎ በትምህርታዊ ስፖርታዊ ውድድሮች ለመሳተፍ 2.0 የሰሚስተር ግሬድ ነጥብ ወይም አማካኝ ነጥብ (GPA) ወይም ከዚህ የተሻለ ተቀባይነት ያለው ነጥብ ሊኖረው/ሊኖራት ይገባል። በስፖርታዊ ውድድሮች መሳተፍ መቻል አለመቻልን ለመወሰን ተከታታይ የምዘና ውጤቶች ወይም ነጥቦች አያገለግሉም።

የአትሌቲክስ ዲፓርትመንት ለተሳታፊነት ብቁ መሆን አለመሆንን የማረጋገጥና የውድድር መርሀ-ግብር የመዘርጋት ሃላፊነት አለበት። የመጓጓዣ አገልግሎት ለሊግ ውድድሮች ብቻ ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ http://dcps.dc.gov/service/athletics ወይም thedciaa.com ይመልከቱ።

## የምግብ አገልግሎት

ተመጣጣኝ ምግብ ለልጅዎ አካዳሚያዊ ስኬት ወሳኝ በመሆኑ፣ የDCPS ተመጣጣኝ ምግቦችንና ቅምሻዎችን ከትምህርት በፊት፣ በትምህርት ጊዜና ከትምህርት በኋላ ለተማሪዎች ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል። የትምህርት ቤት መኑዎች በየቀኑ የሚለዋወጡ ከመሆናቸውም በላይ፣ ልዩ ልዩ ትኩስና ቀዝቃዛ ምግቦችን ያካትታሉ። የትምህርት ቤት ሜኑዎችን በድረ-ገጽ-ቀጥታ-መስመር dcps.dc.gov/food ማግኘት ይቻላል።

- ቁርስ በማንኛውም የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ለሁሉም ተማሪዎች በነጻ ይሰጣል።
- ምሳ:-
  - በነጻና ቅናሽ ዋጋ ምግብ (FARM) የሚፈቅድላቸው በርካታ ተማሪዎች ባሉባቸው 84 ትምህርት ቤቶች በነጻ ይሰጣል። የእነዚህን ትምህርት ቤቶች የተሟላ ዝርዝር ከ http://dcps.dc.gov/page/nutrition-and-meals ማግኘት ይቻላል።
  - በሌሎች ሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ ነጻ ምግብ እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ ተማሪዎች የነጻና ቅናሽ ዋጋ ምግብ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
  - የነጻና ቅናሽ ዋጋ ምግብ ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ተማሪዎች ምሳቸውን በየቀኑ መግዛት አለባቸው። በተማሪዎች የምሳ አካውንት ውስጥ ገንዘብ የመሙያ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ለምሳ ገንዘብ መክፈል ስለሚቻልባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በመስመር ላይ http://dcps.dc.gov/page/nutrition-and-meals ይመልከቱ።
- የከትምህርት በኋላ መክሰስና ቅምሻዎች ከ90 በላይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች በነጻ ይሰጣሉ።

ለጅዎ የምግብ አለርጂ ካለበት/ባት፣ የምግብ አቅርቦት መጠየቂያ ፎርም (Dietary Accommodations form) መሙላት አለቦት፤ (ፎርሙን ከ (http://dcps.dc.gov/page/nutrition-and-mealsማግኘት ይችላሉ)። ፎርሙን ከሞሉ በኋላ የሃኪም ማረጋገጫ ፊርማ ማግኘት ያስፈልጋል። በDCPS ማንኛውም ዓይነት ለውዝ ወይም ኦቾሎኒ አይቀርብም፤ ሆኖም ወላጆች የምግብ አቅርቦት መጠየቂያ ፎርሙን በመሙላት በትምህርት ቤቱ የነርስ ቢሮ ፋይል ላይ እንዲቀመጥ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

ስለ ምግብ አገልግሎት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የትምህርት ቤትዎን ሜኑ ማየት ከፈለጉ፣ ወይም ነጻ የምግብ አገልግሎት ለማግኘት ማመልከቻ እንዴት መሙላት እንዳለቦት ለማወቅ ከፈልጉ፣ የዲሲ.ህ.ት.ቤ.ትን ዌብሳይት http://dcps.dc.gov/page/nutrition-and-meals ይመልከቱ፤ ወይም ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።

## ጤናና ደህንነት

የDCPS ሰራተኞች፣ ቤተሰቦችና ማህበረሰቡ የተማሪዎችን ጤንነት ለመጠብቅ በጋር የሚሰሩበትና ተማሪዎቻችን ስለራሳችውና ለሌሎች ጤናማ ምርጫ ማድረግ እንዴት እንደሚችሉ የሚማሩባቸው ስፍራዎች ናቸው።

### የጤና መስፈርትማ ፎርሞች

በየዓመቱ አጠቃላይ የጤና ምርመራና የአፍ ውስጥ ጤና ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ትምህርታቸውን ማካታተል ይችሉ ዘንድም የክትባት መርጃቸው ወቅቱን የጠበቀ መሆን አለበት። ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው፣ ከምዝገባ ሂደት አንዱ መስፈርት ተከታታይ የጤና ምርመራ ፎርሞችን እየሞሉ ለትምህርት ቤቱ ማስገባትና ዓመቱን ሙሉም የታደሱ የምርመራ ፎርሞችን ለትምህርት ቤቱ ነርስ ቢሮ ማስገባት ነው።

- ወቅታዊ የሆነ (ባለፉት 365 ቀናት ውስጥ) እና የተሟላ ዓለም-አቀፋዊ የጤና ሰርቲፊኬት (በየዓመቱ ለሁሉም ክፍል ተማሪዎች የሚያስፈልግ፣ የክትባት ሰነዶች፣ የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ምርመራ፣ የሊድ ምርመራና አካላዊ የቴና ምርመራ) ያስፈልጋል። ስለ ዲሲ የክትባት መስፈርት ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎ ከልጅዎ ሃኪም ጋር ይነጋገሩበት። የዲሲን የጤና ክትባት ክፍል ዲፓርትመንትም በስልክ ቁጥር 202-576-9325 ማነጋገር ይችላሉ።
- የአፍ ውስጥ ጤና ምርመራ (ለሁሉም ክፍል ተማሪዎች በየዓመቱ የሚያስፈልግ)
- የመድሃኒትና የህክምና ማዘዣ ፎርም (እንደየአስፈላጊነቱ)
- የአስም ጥንቃቄ እቅድ (እንደየአስፈላጊነቱ)
- የአለርጂ (Anaphylaxis) ጥንቃቄ እቅድ (እንደአስፈላጊነቱ)።

ከክትባት ነጻ የመሆን ፍስይል ማስገባት ከፈለጉ፣ እባክዎ የትምህርት ቤትዎን ነርስ ያነጋግሩ። ሁሉንም ጤና-ነክ ፎርሞች ከሚከተለው ድረ-ገጽ ማግኘት ይችላሉ፤ http://dcps.dc.gov/service/school-based-health-centers-dcps

### መድሃኒቶች

በተቻለ ጊዜ ሁሉ፣ ወላጆች ለልጆቻቸው መድሃኒቶችን በቢቶቻቸው እንዲሰጡ ይመከራሉ። ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ መድሃኒቶች መውሰድ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ እባክዎ ሃኪምዎ አስፈላጊዎቹን ከላይ የተዘረዘሩ ፎርሞች እንዲሞሉሎት በማድረግ ለትምህርት ቤቱ ነርስ ያስረክቡዋቸው። ለተጨማሪ መረጃ dcps.dc.gov/health ይመልከቱ።

### የትምህርት ቤት ነርስ ፕሮግራም

የትምህርት ቤቱ ነርስ የትምህርት ቤቱን አካባቢ ጤንነት ለመጠበቅ ከመርዳቱም ባሻገር፣ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አካላዊና ስሜታዊ ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ለማሟላት ያስችላል። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በየትምህርት ዓመቱ ቢያንስ የትርፍ-ጊዜ ነርስ አገልግሎት ጽፋን ይኖረዋል። ትምህርት ቤቱ የክረምት ፕሮግራም ካለው፣ በክረምት ወቅትም በትምህርት ቤቱ ውስጥ አንድ ነርስ ይኖራል።

### የጤኛ፡አገልግሎጦጭ

የDCPS ከዲሲ የጤና ዲፓርትመንት ጋር በመተባበር የነጻና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ በልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ (chlamydia) እና የጨብጥ ምርመራ በዓመት አንድ ጊዜ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ይሰጣል። የኤች አይ ቪ ምርመራም በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጣል። ከእያንዳንዱ ምርመራ በፊት፣ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ስለሚሰጡ የተወሰኑ አገልግሎቶች አስፈላጊውን መረጃ ለቤቶቻቸው ይልካሉ። እባክዎትን እነዚህን መርጃዎች አግኝተው በማንበብ፣ ቀደም ብለው ስለ ምርመራዎቹ ከልጅዎ ጋር ለመወያየት ይዘጋጁ።

የዲሲ.ህ.ት.ብ.ት. በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዲሲን የጤና ዲፓርትመንት የኤች አይ ቪና ሌሎች በልቅ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሊተላለፉ የሚችሉ በሽታዎች የመከላከል የኮንዶም ፕሮግራም (DOH's Wrap MC Condom program) በመተግበር፣ በሰለጠኑ የትምህርት ቤት ሰራተኞች አማካኝነት ከ9-12 ክፍል ተማሪዎች እንደ አንድ የተሟላ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ኮንደሞችን ያድላል። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎችም ኮንደሞችን ለማደል ሰልጥነዋል። ኮንደሞችን ከትምህርት ቤቱ ነርስም ማግኘት ይቻላል። ለተጨማሪ መረጃ http://dcps.dc.gov/service/school-based-health-centers-dcps ይመልከቱ።

### ነጻ የህክምና ክብካቤ

ተማሪዎች መደበኛ የጤና ክብካቤ የሚሰጣቸው እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። የጠቅላላ ጤና ወይም የጥርስ ኢንሹራንስ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የሜዲክኤይድ (Medicaid) ወይም በከፊል በመንግስት ወጪ የሚሸፈን የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃ dchealthlink.com ይመልከቱ። በተጨማሪም፣ ሜዲክኤይድ ካልዎትና የጥርስ ጤና አገልግሎት ሰጪ ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለማያዝ እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆን፣ በስልክ ቁጥር 1-866-758-6807 መደወል፣ ወይም ኢንሹር ኪድስ ናዎ የተሰኘውን ዌብሳይት (Insure Kids Now website) insurekidsnow.gov/state/dc/district_oral.html መመልከት ይችላሉ።

ለህክምና ፎርም ቅጂዎችና ስለማንኛውም ጤና-ነክ ጥያቄዎችና አሳሳቢ ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ dcps.dc.gov/health ይመልከቱ ወይም ከትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ይነጋገሩ።

### የአእምሮ ጤና ድጋፍ

የተማሪዎችን ስሜታዊ ጤና ደህንነት ለመደገፍ፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤቱን ማህበራዊ ጉዳዮች ሰራተኛ፣ የስነልቦና ባለሙያና/ወይም አማካሪ ያካተተ አንድ የአእምሮ ጤና ቡድን ያለው ሲሆን፣ ይኸውም ከትምህርት ቤቱ ባህልና አካባቢ፣ ከዕጽ አጠቃቀም፣ በራስ-መተማመንና ከነዚህና ከሌሎችም እዚህ ውስጥ፡ካልተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚረዳ ነው። ስለሚሰጡት ግልጋሎቶች ተጨማሪ መረጃ በዚህ የወላጆች መመሪያ መጽሃፍ ገጽ 44፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ የአእምሮ ጤና ቡድን ጋር በመነጋገር ማግኘት ይቻላል።

### አካባቢያዊ የደህንነት ፖሊሲ

የDCPS አካባቢያዊ የደህንነት ፖሊሲ (LWP) ከአካባቢና ብሄራዊ የአመጋገብና አካላዊ እንቀስቃሴ ባልሙያዎች፣ ከትምህርት ቤት ሰራተኞችና ወላጆች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው። የተማሪዎችም አስተያየት በፖሊሲው ውስጥ ተካቷል።

የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲው የDCPS የአመጋገብና አካላዊ እንቅስቃሴ ፕሮግራሞችን ለመተግበር ያለውን ግቦች ያንጸባርቃል። እነዚህም ግቦች፡-የጤና ትምህርትንና ጤናማ ባህርያትን ማስፋፋት፤ ለተማሪዎች የጤናማ ምግብ አቅርቦትን አማራጭች መስጠት፤ ከትምህርት በፊት፣ በትምህርት ወቅትና ከትምህርት በኋላ የተማሪዎችን አካላዊ ብቃት እንቅስቃሴ ማሳደግ፤ የተማሪዎችን የጤና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ለወላጆችና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ሁለንተናዊ ድጋፍ መስጠት፤ የትምህርት ቤቶችን አካባቢያዊ ደህንነት ቀጣይነት ማጎልበት፤ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲውን ውጤታማነት መመዘን፤ እና ለተሻለ ፕሮግራም አስፈላጊ የሆኑ የማህበረሰብ አስተያየቶችን መሰብሰብ ናቸው። የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲውንከ http://dcps.dc.gov/page/health-and-wellness ማግኘት ይቻላል።

## ሌሎችን ሰላም መንሳት (Bullying)

የDCPS እያንዳንዱን ትምህርት ቤት ደህንነትን የተላበሰና ለልጆችዎና ለቤተሰቡም የሚመች የመማሪያ ስፍራ ለማድረግ ቁርጠኝነት ያለው ሲሆን፣ እነዚህም ለዚሁ ተግባር ስኬታማነት ለሚደረገው ጠረት አስፈላጊ አጋሮች ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን ከሚያውቁና ሰላም ከሚነሱ ሃይላት (ቡሊንግ) (bullying) መከላከል ከሚችሉባቸው እጅግ ፍሬያማ ተግባራት አንዱ፣ ከልጆቻቸው ጋር በሌሎች ቡሊ መደረግ ወይም ሌሎችን ቡሊ ማድረግ ምን ማለት ስለመሆኑ በቅድሚያና በግልጽ መነጋገር ነው። ይህን ማድረግ በእርስዎና በልጅዎ መካከል ግልጽ የውይይት መስመር እንዲኖር ማረጋገጥ ከማስቻሉም በላይ፣ በትምህርት ቤት ወስጥ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ችግሮች በግልጽ የመነጋገርን ጠቀሜታንም ያጠናክራል።

የDCPS በተቻለ መጠን ማንኛውንም ወይም ሁሉንም የቡሊንግ ሪፖርቶች ፍሬያማና ሁሉን-አቀፍ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚሞክርበት ቡሊንግን የመከላከል ፖሊሲ አለው።

- ልጅችዎ በትምህርት ቤት ቡሊ ተደርገው ሊሆን ይችላል ብለው ከተጠራጠሩ፣ እነሱኑ ስለ ችግሩ በግልጽ ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ።
- ልጆችዎን በማንኛውም ችግር ጊዜ ከጎናቸው እንደሚቆሙና የሚነግሩዎትንም ነገር እንደሚያምኑዋቸው መንገር እንዳለቦት አይዘንጉ።
- እባክዎ የቡሊንግ ችግር ካለ እርስዎ ወይም ልጅዎ ለትምህርት ቤቱ የቡሊንግ መከላከል ተጠሪ ወይም ለዲሪክቴሩ ሪፖርት አድርጉ።
- ልጅዎ ሌሎችን ልጆች ቡሊ ስለማድረጉ/ጓ ከተጠራጠሩ፣ ከልጅዎ ጋር ስለዚህ አጉል ጠባይ መወያየትና፣ ቡሊንግ በትምህርት ቤቱ እንደ ከፍተኛ ማህበራዊ ችግር እንደሚቆጠር ግልጽ ማድረግ ይገባል። ይህንን እያደርጉም ልጅዎ ከቡሊንጉ ጀርባ ስላለው ምክንያት እንዲረዳ/እንድትረዳ በጋር አብሮ መስራት ያስፈልግ ይሆናል።
- ሳይበር ቡሊንግ (ኢንተርኔትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚደርግ ቡሊንግ)፣ ማለትም ከባድ ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራትነ፣ ጸያፍ የህጻናት ወሲብ ፊልምን (child pornography) ወይም ግልጽ የወሲብ ተግባር የሚታይበት ማቴሪያል፣ ሌሎችን ጤና የሚነሳ የመከታተል ተግባር ወይም የጥላቻ ወንጀል መኖሩን ከራጋገጡ ወይም ካወቁ፣ እባክዎ ጉዳዩን ለህግ አስከባሪ አካላት ሪፖርት ማድረግ እንደሚኖርቦት አይዘንጉ። ሳይበር ቡሊንግ የክፍል ውስጥን ትምህርት ከማወኩም በላይ ግለሰቦች ቡሊ ወደ ማድረግም ሊሸጋገር ይችላል።

ስለ DCPS ቡሊንግን የመከላከል ፖሊሲ ተጨማሪ መርጃ ለማግኘት http://dcps.dc.gov/bullying ይመልከቱ።

**ምክር ለወላጆች**

*ልጅችዎ ቴክኖሎጂዎችን ሃላፊነት ባለው መንገድ መጠቀም የሚችሉ እንዲሆኑ መርዳት ደህንነታቸውን ለዘለቄታው ከመጠበቅ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። የሚከተሉት ማድረግ ከሚችሏቸው ነገሮች ጥቂቱ ናቸው፡-*

- *ሁሉም ልጆችዎ ኦንላይን አካውንቶች የምስጢር ቁልፎች (ፓስዎርዶች) ያሎት መሆኑን ያረጋግጡ።*
- *የልጆችዎን የስክሪን መመልከቻ ጊዜ (ቲቪ፣ ኢንተርኔት፣ ፌስቡክ/ትዊተር) ይከታተሉ።*
- *ቴክኖሎጂዎችን በቤትዎ ውስጥ ለሁሉም የጋራ በሆኑ ስፍራዎች ማስቀመጥ አጠቃቀማቸውን ለመከታተል ያስችሎታል።*
- *ቴክኖሎጂዎችን ማታ ማታ አጥፍተው ደህና ቦታ ያስቀምጡ።*
- *ሃላፊነት የተሞላበት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ልምድ በማዳበር ለልጆችዎ መልካም አርአያ ይሁኑ።*

## የዲሲፒሊን ፖሊሲዎች

ዋናው ዓላማችን ልጅዎ ከመማሪያ አካባቢው/ዋና የትምህርት ቤቱ/ቷ ማህበረሰብ ጋር በአዎንታዊ፣ ሃላፊነት በተሞላበትና ፍሬያማ በሆነ መንገድ መግባባት እንዲችል/እንድትችል መርዳት ነው። ሁሉም የDCPS ፖሊሲዎች፣ የተማሪዎችን ዲሲፕሊንና የተማሪዎች መብቶችና ሃላፊነቶችን ከሚመለከተው የዲሲ አስተዳደር ደንቦች (DC Municipal Regulations፣ DCMR Chapter 25) ጋር የሰመሩ ከመሆናቸውም በላይ በየደረጃው ከሚወሰዱ ዲስፕሊናዊ እርምጃዎች ጋር ተጣጥመው የተጻፉ ናቸው። የዲሲን አስተዳደር ደንቦች ዓላማ ለማክበርና የተማሪዎችን ጤናማ እድገት ለመደገፍ፣ የቅድመ-ልጅነት ተማሪዎች ለተወሰነ ጊዜ የመታገድ እርምጃ አይወሰድባቸውም። ይህም የትምህርት ቤት ውስጥና የከትምህርት ቤት ወጭ እገዳን ይጨምራል። እነዚህን ሰንዶች ለማግኘት፣ እባክዎ http://dcps.dc.gov/node/1014212 ይመልከቱ።

## መጓጓዣ

### የዲሲ ህጻናት መጓጓዣ ነጻ ፕሮግራም (DC Kids Ride Free Program)

የDCPS ለተማሪዎች የመጓጓዣ ቢጫ አውቶቡስ አይሰጥም። ይሁን እንጂ፣ የወረዳው መጓጓዣ ዲፓርትመንት (DDOT) በዲሲ ህጻናት መጓጓዣ ነጻ ፕሮግራም አማካኝነት ለተማሪዎች ነጻ የሜትሮባስና የሜትሮሬይል ቲኬት (Metrobus pass and Metrorail pass) ይሰጣል። ይህም እድሜያቸው ከ5-21 ዓመት ለሆነ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሙሉ ይሰጣል። ልጅዎ የዲሲ ዋን ካርድ (DC One Card) ከሌለው/ላት፣ ትምህርት ቤቱን በመጠየቅ፣ ወይም በስልክ ቁጥር 202-673-1740 በመደወል፣ ወይም ከ dconecard.dc.gov ማግኘት ይቻላል። ካርዱን ኦንላይን ላይ በማስመዝገብ የመመላለሻ ጥቅማጥቅሞቹን ልጅዎት የዲሲ ዋን ካርድ ላይ በቀጥታ መቻን ይችላሉ። ለተጨማሪ መርጃ፣ dconecard.dc.gov ይመልከቱ።

### የመጓጓዣ አገልግሎቶች

መጓጓዣ ከአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ደንብ (IDEA) ጋር የተዛመደ አገልግሎት በመሆኑ፣ ልጅዎ ለዚህ አገልግሎት ብቁ መሆን አለመሆኑ/ኗ፣ የስቴት ከፍተኛ የትምህርት አስተዳደር ቢሮ (OSSE) በሚያወጣው መስፈርት ላይ ተመስርቶ፣ በግለሰባዊ-ተኮር ትምህርት ፕሮግራም ቡድን (IEP) የሚወሰን ይሆናል። መጓጓዣ በ OSSE የትራንስፖርት ዲፓርትመንት (DOT) የሚሰጥ ይሆናል።

ስለ ልጅዎ የትራንስፖርት አገልግሎት በቃት ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ። ልጅዎ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ከሆነ/ችና ስለ አውቶቡሱ ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 202-576-5000 በመደወል የስቴት ከፍተኛ የትምህርት አስተዳደር ቢሮ፣ ትራንስፖርት ዲፓርትመንት፣ የወላጆች ሪሶርስ ሴንተር (OSSE DOT Parent Resource Center) ያነጋግሩ።

## የትምህርት ቤቶች የድንገተኛ አደጋ ጊዜ፣ መዘግየት ወይም መዘጋት

የትምህርት ቤት የድንገተኛ አደጋ ምላሽ እቅድና አስተዳድር መመሪያ (The School Emergency Response Plan and Management Guide) (bit.ly/EMGuide) ትምህርት ቤቶችን የአየር ንብረት መዛባትን፣ ተፈጥሯዊ አደጋዎችንና በመሳሪያ የሚፈጠሩ ስጋቶችን ጨምሮ ለድንገተኛ አደጋዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ ያዘጋጃል። መመሪያው ከ DCPS ፣ከሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ፣ ከአገር ውስጥ ደህንነትና ድንገተኛ አደጋዎች ቁጥጥር ኤጀንሲ እና ከሌሎችም የመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር በአጋርነት የተዘጋጀ ነው።

አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ወቅት፣ የDCPS ተማሪዎችና ሰራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ጠንክሮ ይሰራል። ዋና ዓላማውም፣ በተቻለ መጠን ሁሉ የDCPS ትምህርት ቤቶች ክፍት መሆናቸውንና ተማሪዎች አካዳሚያዊ ትምህርትን፣ የተመጣጠነ ምግብና ጤናማ ተጓዳኝ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው። ትምህርት ቤቱን የማዘግየት ወይም መዝጋት ውሳኔ የመንገድ ደህነትን፣ የእግረኛ መንገድ ደህነትንና የምግብ መኖርን ግምት ውስጥ በማስገባት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል። በእንደዚያ ያለው ቀን ልጅችዎ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው እራስዎ መወሰን ይችላሉ።

ስለ ትምህርት ቤት በድንገተኛ አደጋ ምክንያት መዘግየትና መዘጋት መረጃ ማግኘት የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ።

1. በቲቪና ሬዲዮ የአካባቢዎን ዜና ያዳምጡ።
2. የDCPS ዌብሳይትን ይመልከቱ፤(dcps.dc.gov)
3. ኢሜል የማስጠንቀቂያ መልእክቶች ከትምህርት ቤት እንዲደርስዎ ይመዝገቡ (dcps.dc.gov/signup)
4. የDCPS ን በትዊተር ይከታተሉ፤(twitter.com/dcpublicschools)
5. የDCPS ን በፌስቡክ ይከታተሉ፤(facebook.com/dcpublicschools)
6. በስልክዎ የቴክስት መልዕክት ለመቀበል በ 91990 ላይ NEWS የሚል ተክስት በመላክ ሳይን አፕ ያድርጉ

በትምህርት ቀን ድንገተኛ አደጋ ከተፈጠረ፣ ሰራተኞቹ መላውን የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለማረጋገጥ ከግቢው በደህና ለማስወጣትና ልጅዎን በተቻለ ፍጥነት ከእርስዎ ጋር ለማገናኘት የሰለጠኑ መሆናቸውን ይወቁ።

## የትምህርት ቤት ጉብኝት ፖሊሲ

ትምህርት ቤቶች የህዝብ ተቋም እንደመሆናቸው መጠን፣ የመማር-ማስተማር ሂደቱንና የትምህርት ቤቱን መደበኛው ተግባር፣ እንዲሁም የተማሪዎችንና ሰራተኞችን ደህንነት ጥያቄ ውስጥ እስካላስገባ ድረስ ለወላጆችና ለሌሎችም መጎብኘት ለሚፈልጉ አካላት ክፍት መሆን አለባቸው። በመሆኑም፣ የDCPS ትምህርታዊ ድርጅቶች (ህንጻዎችና መሳሪያዎች)፣ ጎብኚዎች የመማር-ማስተማሩን ተግባር እስካላወኩና የትምህርት ቤቱን ተግባርና እንቅስቃሴዎች እስካልረበሹ፣ እንዲሁም የተማሪዎችንና ሰራተኞችን ደህንነት አደጋ ውስር እስካላስገቡ ድረስ ለጎብኚዎች ክፍት መሆናቸውን ይቀጥላሉ። ሁሉም ጎብኚዎች ማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ የተለጠፈውን የጎብኚዎች ፖሊሲ ማክበር አለባቸው፤ ይህም መታወቂያ ማሳየትንና ለዋናው ጽህፈት ቤት ሪፖርት ማድረግን ይጨምራል።

# አካዳሚያዊ አቅርቦት እና መስፈርት



# አካዳሚያዊ አቅርቦት እና መስፈርት

የDCPS መማር ከልደት ጀምሮ ህይወትን ሙሉ ቀጣይ መሆኑን ይረዳል። የDCPS ይህን የመማር ሂደት የሚያሳድጉ የፕሮግራም ምርጫዎችንና የትምህርት ቤት አማራጮችን ይሰጣል። ከቅድመ-ልጅነት ጀምሮ እስከ በአንደኛ ደረጃ፣ በመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እስከሚሰጡ ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ድረስ፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ፍላጎት የሚመቹ የትምህርት ፕሮግራሞችን ለመምረጥ ይችላሉ።

ሁሉም ፕሮግራሞች ለልጅዎ ከፍተኛ እድገት ደረጃዎች ለመብቃት አስፈላጊ የሆነውን መሰረታዊውን እውቀት ለማስጨበጥ የተዘጋጁ ናቸው።

- የቅድመ-ልጅነት (ህጻንነት) ትምህርት
- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካዳሚያዊ አቅርቦት
- የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካዳሚያዊ አቅርቦት
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካዳሚያዊ አቅርቦት
- ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውርና በትምህርት ገበታ ላይ ማስቀጠል
- ለምረቃ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች (መስፈርት)
- የናቪያንስ/ወላጅ ጥምረት (Naviance/Family Connections)
- የክሬዲት አከፋፈል
- ምዘናዎች
- የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መመሪያ ተፈጻሚነት መሻሪያ ("ማንኛውም ህጻን ከትምህርት ወደኋላ መቅረት የለበትም")
- ደረጃ 1 ትምህርት ቤቶች

## የቅድመ-ልጅነት ትምህርት (ከ3-4 ዓመት እድሜ)

የDCPS ለ4-ዓመት ህጻናት በማንኛውም የDCPS አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት (PK4) ይሰጣል። ለ3-ዓመት ህጻናት በአብዛኛዎቹ የDCPS አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት (PK3) ይሰጣል። ተማሪዎች የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት (PK3 or PK4) ማከታተል ስለማይገደዱ፣ እንዲሁም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች የመቀበል አቅም ስለሌላቸው፣ ያሉት ክፍት ቦታዎች፣በ MyschoolDC.org አማካኝነት በሚካሄድ ፍትሃዊና የሁሉንም እኩልነት መሰረት በሚያደርግ የሎተሪ ዘዴ ይደለደላሉ።

የቅድመ-ልጅነት ፕሮግራሞች፣ የህጻናቱን እድገትና ጨዋታን መሰረት ያደረገ ትምህርት ለመደገፍ የሚረዱ በቂ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና የቤት ውስጥና የውጭ የመማሪያ ስፍራዎች ባሏቸው አነስተኛ የተማሪ ቁጥርን በሚይዙ ክፍሎች ይሰጣሉ።

### የሬጊዮ ኤሚሊያ አቀራርብ

የሬጊዮ ኤሚሊያ አቀራረብ ለህጻናቱ ጥንካሬ፣ የባህርይ መለዋወጥ (በቀላሉ መተጣጠፍ) እና የራሳቸውን የመማሪያ መንገድ መፍጠር መቻል ዋጋ የሚሰጥ ፈጠራዊ የቅድመ-ልጅነት ትምህርት ዘዴ ነው። የሬጊዮ ኤሚሊያን አቀራረብ የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በዚህ መመሪያ አባሪ ውስጥና ኦንላይን ላይ dcps.dc.gov/DCPS/ece ይገኛል።

### ሞንተሶሪ

ሞንተሶሪ የህጻናቱን ተፈጥሯዊ የመማር ፍላጎት (የማወቅ ጉጉት) ለማጎልበት የተዘጋጀ ስነዘዴ ነው። አንድ ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ ሞንተሶሪ ነው ለመባል ሊያሟሉ ከሚገቡ ነገሮች መካከል፣ የቢጤ-ትምህርትን ሊያበለጽግ የሚችል በተለያዩ የዕድሜ ላይ ያሉ ህጻናት ቡድኖች መኖር፣ ተከታታይነት ያለው (የማይቆራረጥ) የትምህርት ጊዜ መደብ፣ እና በጥንቃቄ የሚመራ ትምህርታዊ ተግባራት ምርጫ ይገኙበታል። የሞንተሶሪ ፕሮግራሞች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በዚህ መመሪያ አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/ece ላይ ይገኛል።

### የአእምሮ መሳሪያዎች

የአምሮ መሳሪያዎች (Tools of the Mind) የተማሪዎችን ጠንካራ የንባብና ሂሳብ ክሂሎትና እራሳቸውን የመምራት መሰረት መገንባት የሚያስችል ምርምር-ምስርት ፕሮግራም ነው። የአዕምሮ መሳሪያዎች ፕሮግራም ያላቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በዚህ መመሪያ አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/ece ላይ ይገኛል።

### የቅድመ-ትምህርት ቤት ፈጠራዊ ስራዓት-ትምህርት

የቅድመ-ትምህርት ቤት ፈጠራዊ-ስርዓት-ትምህርት ምርምር-ምስርት ፈርጀ-ብዙ ስርዓተ-ትምህርት ሲሆን፣ የመምህራንን መማርን አስደሳችና ለህጻንት ተገቢ የማድረግ ፈጠራዊና ጥንቃቄ የተሞላበት ሚና ማክበሩ እንዳለ ሆኖ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚረዳ ነው። ይህን ስርዓተ-ትምህርት የሚጠቀሙ የመማሪያ ክፍሎች፣ ነገሮችን መመርመርን፣ ማሰስንና ማግኘትን፣ እንዲሁም የህጻናቱን በራስ-የመተማመን፣ የፈጠራ ችሎታና ህይወታቸውን በሙሉ ነገሮችን በጥልቀት የመመርመር ክሂሎት ለማዳበር መርዳትን እንድ አንድ የመማሪያ ዘዴ በመጠቀም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ፈጠራዊ ስርዓተ-ትምህርት ያላቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በአባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/ece ላይ ይገኛል።

### ትምህርት ቤት-ፍጥር ስርዓት-ትምህርት

እነዚህ የቅድመ-ልጅነት ማስተማሪያ አቀራረቦች በትምህርት ቤቱ መምህራንና ሰራተኞች የተፈጠሩ ናቸው። እባክዎ ትምህርት ቤቱ ቅድመ-ልጅነት ተማሪዎቸን በየትኛው አቀራረብ እንደሚያስተምር ለማወቅ ትምህርት ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።

# አንደኛ ደርጃ ትምህርት ቤት (Grades K-5)

### መሰረታዊ የአንደኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ትምህርታዊ አደረጃጀት

በእያንዳንዱ የDCPS አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና መማሪያ ካምፓስ፣ ከመዋዕል-ህጻናት እስከ 5 ክፍሎች (Grades K-5) ያሉ ተማሪዎች በየቀኑ የሚከተሉተን የትምህርት ዓይነቶች ይማራሉ፡-

### ዓበይት የትምህርት ዓይነቶች

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የንባብና የሂሳብ ትምህርት ብሎኮችን በዋነኛነት የሚይዝ ሲሆን፣ እነዚህም ለተማሪዎች እድገትና የንባብና ሂሳብ ኪሂሎታቸውን በተግባር ለመጠቀም የሚያስችሉ የተለያዩ ትምህርቶችና ልምዶችን የሚሰጡ ናቸው። ተማሪዎች ማህበራዊ ሳይንስና ሳይንስንም የሚማሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ በኪን-ጥበብ፣ ሙዚቃ፣ በዓለም ቋንቋዎችና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ውስጥ የመሳተፍ እድልም ይኖራቸዋል።

### ልዩ ፕሮግርሞችና ትምህርታዊ አቅርቦት

ከፍተኛና የበለጸገ ትምህርት:- የDCPS ሁሉም ተማሪዎች ተፈጥሯዊ ተሰጥኦዎች (talents) እንዳሏቸው ያምናል። ማንኛውም ከአማካዩ ትምህርታዊ ችሎታ በላይ፣ ልዩ የፈጠራና/ወይም ከፍተኛ በጥናት ላይ የማተኮር ቁርጠኝነት ያለው/ላት ተማሪ፣ በከፍተኛ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ መሳተፍ ይችላል/ትችላለች።

የDCPS የከፍተኛ አንባቢዎች እክስቴንሽን ክፍሎች (Advanced Readers Extension (DARE) Units):- የDCPS የከፍተኛ አንባቢዎች እክስቴንሽን (DARE) ክፍሎች፣ ከ2-5 ክፍል ያሉ ተማሪዎች ፕሮግራም ሲሆን፣ ከፍተኛ አንባቢዎች ከክፍል ደርጃቸው በላይ የሆኑ መጻህፍትን እንዲያነቡ ያስችላል። ይህ ፕሮግራም ቁጥራቸው ከ25 በላይ በሆኑ የDCPS ውስጥ ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ የትምህርት ቤቱን መምህር ያነጋግሩ።

መኻለኛ ታላቅ መጻህፍት:- ይህ ፕሮግራም ከመዋዕል-ህጻናት-8 ክፍል የሚሰጥ ሲሆን፣ ተምሪዎች ውስብስና የበለጸጉ ጭብጦች ያሏቸውን ስነ-ጽሁፋዊ መጻህፍት የሚያነቡበትና የሚወያዩበት ነው። የመኻለኛ ታላቅ መጻህፍት ስርዓተ-ትምህርት 60 ያህል በሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጣል። ይህን ፕሮግራም የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አንላይን በ http://dcps.dc.gov/page/advanced-and-enriched-instruction ይገኛል።



## ምሶሶዎች (Cornerstones)

ምሶሶዎች በDCPS ዓበይት የስርዓተ-ትምህርት ክፍሎች ውስጥ የሚሰጡ ተጽዕኖ ፈጣሪ የትምህርት ልምዶች ናቸው። እነዚህም በእያንዳንዱ ክፍል (ከመዋዕለ-ህጻናት እስከ 12ተኛ ክፍል) ለሁሉም ተማሪዎች፣ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነ-ጥበብ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ አርት፣ ሙዚቃ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ የጤናና የዓለም ቋንቋ ትምህርቶች ጋር በተጓዳኝ የሚሰጡ ናቸው። ምሶሶዎች ትምህርትን ከሚያስደስትና ትርጉም ያለው የእውኑ ዓለም ህይወት ጋር በማያያዝ የሚያጠናክሩ ናቸው። አሳታፊና ጠንከር ያለ ይዘት ያላቸው ትምህርቶችንና በመምህራን ለመምህራን የተዘጋጁና በቀላሉ ተደራሽነት ያላቸው ትምህርታዊ ሞዴሎችን በማካተት፣ እንዲሁም የተቀናጀ የቤተሰብና የማህበረሰብ ድጋፍ በመጠቀም፣ ምሶሶዎች መሰረታዊ የጽንሰ-ሃሳብ ትምህርትን ለማጠናከርና ለያንዳንዱ አስተማሪና ተማሪ ስኬትን ለማስገኘት እንደ አንድ መሳሪያ ያገለግላሉ። የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በአራት የምሶሶዎች ተግባራት ውስጥ ይሳተፋሉ። ለተጨማሪ መርጃ፣ ዌብሳይቱን በ dcps.dc.gov/page/cornerstones ይመልከቱ ወይም የትምህርት ቤትዎን መምህር ያነጋግሩ።

## ዓለም-አቀፋዊ ትምህርት

የDCPS ዓለም-አቀፋዊ ትምህርት ፕሮግራሞች፣ ሁሉም ተማሪዎች ስለ ዓለማቸው የሚያወቁና የሚሳተፉ ዓለም-አቀፍ ዜጎች መሆን ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጓቸውን መሳሪያዎችና አጋጣሚዎችን ማግኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ ናቸው። በኤምባሲ የአዶፕሽን ፕሮግራም አማካኝነት የሃገር መሪዎችን ማናገር መቻልን ጨምሮ፣ የዓለም ቋንቋዎችን መማር፣ በሚኒ የተባበሩት መንግስታት መድረክ በዓለም-አቀፍ ጉዳዮች ላይ መከራከር፣ ወይም በዓለም-አቀፍ የምግብ ቀናት ውስጥ መሳተፍ፣ ወዘተ. የዲሲ.ህ.ት.ቤ.ት ለተማሪዎች በዓለም-አቀፍ ከተሞቻችንም ሆነ የእርስ በርስ ቁርኝቱ እያደገ በመጣው ዓለማችን ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት እውነተኛ ዓለም-አቀፋዊ ትምህርት ይሰጣል። በመላው የDCPS የተመረጡ 5ተኛ እና 6ተኛ ክፍሎች በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የልጅዎን መምህር ያነጋግሩ።

## የዓለም-አቀፋዊ ባክሎሬት የመጀመሪያ ዓመታት ፕሮግራም (Grades PK3-5)

የመጀመሪያ ዓመታት ፕሮግራም (PYP) ለጥልቅ ምርመራና መረዳት (critical thinking) እና ዓለም-አቀፋዊ ትኩረት አጽንኦት የሚሰጥ ስርዓተ-ትምህርት ሲሆን፣ ለተማሪዎች እራሳቸውን ችለው የምርምር ስራ እንዲያከናውኑ እድል የሚሰጥ ኘው። በ PYP ውስጥ ተማሪዎች እራስን መቻልንና ስለሚማሯቸው ነገሮች ጥያቄ የመጠየቅ ልምድን እንዲያዳብሩ ይበረታታሉ። PYP የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/IB ላይ ይገኛል።

## የዓለም ቋንቋ

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሶስት የዓለም ቋንቋ መማሪያ ሞዴሎች አሉ፦- የአንደኛ ደረጃ የውጭ ቋንቋ (FLES)፣ የአንደኛ ደረጃ የውጭ ቋንቋ አሰሳ (FLEX) እና (FLEX) ጥምር ቋንቋ ጠለቃ (DLI)። የ FLES ፕሮግራም በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ረዘም ላሉና በመደበኛነት በሚሰጡ ክፍለ-ጊዜያት፣ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው በትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በሚማሯቸው የጽንሰ-ሃሳብ ትምህርቶች አማካኝነት የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብሩበት ነው። የ FLEX ፕሮግራም፣ አጠር ያሉ መደበኛ ክፍለ-ጊዜያትን ረዘም ላለ ጊዜ በመስጠት፣ ሁሉም ተማሪዎች በታሪኮች፣ ጌሞች፣ ተግባራትና በሙዚቃ አማካኝነት የቋንቋና ባህል ልምድ እንዲያዳብሩ የሚረዳ ነው። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ቋንቋዎች፣ ፍሬንች፣ ላቲን፣ ማንደሪን እና ስፓኒሽን ይጨምራሉ። ትምህርት ቤትዎ የትኛውን ቋንቋ/ዎች እንደሚሰጥ ስልክ በመደወል ይጠይቁ።

በ DLI ፕሮግራሞች ውስጥ፣ ከመዋዕል-ህጻናት ጀምሮ ሁሉም ተማሪዎች ዓበይት የትምህርት ዓይነቶችን በሁለት ቋንቋዎች፣ ማለትም በስፓኒሽና እንግሊዝኛ ይማራሉ፤ የመማሪያ ክፍለ-ጊዜያትም ለሁለቱ ቋንቋዎች እኩል ይከፈላሉ። የጥምር ቋንቋ ጠላቃ ፕሮግራሞችን የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ http://dcps.dc.gov/page/global-education ላይ ይገኛል።

## ተርን አራውንድ አርትስ (Turnaround Arts)

የተርን አራውንድ አርትስ ፕሮግራም ዓላማ ትኩረትን ደከም ወዳሉ ትምህርት ቤቶች ማዞር ሲሆን፣ በአርት ትምህርቶች አማካኝነት በነዚህ ትምህርት ቤቶችና በሌሎች ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች መካከል ያለውን የስኬት ደረጃ ልዩነት ለማጥበብና የተማሪዎቹን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚሞከርበት ነው። በተርን አራውንድ አርትስ ፕሮግራም አማካኝነት ትምህርት ቤቶች የአርት ትምህርት ስልጠናና የአርት ቁሳቁስ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎችና እነዚህን የመሳሰሉ መሳሪያዎችን፣ እንዲሁም ከማህበረሰባዊ የአርት ትምህርትና ባህል-ነክ ድርጅቶች ጋር አጋርነት እንዲፈጥሩ የሚረዳ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። ከፕሮግራሙ ክፍሎች አንዱ፣ ከፍተኛ-እውቅና ያላቸው አርቲስቶች የተርን አራውንድ አርትስ ትምህርት ቤቶችን "አዶፕት" ማድረግና ከተማሪዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ማህበሰቦች ጋር በመስራት የስኬት ልምዳቸውን የሚያጋሩበት ነው። የተርን አራውንድ አርትስ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በአባሪ ውስጥና በ http://dcps.dc.gov/DCPS/academics ላይ ይገኛል።

## መላው ትምህርት ቤት ውሁድ ትምህርት

የመላው ትምህርት ቤት ውሁድ ትምህርት ፕሮግራም የግምባር-ለግምባር ትምህርትንና ከፍተኛ ጥራት ያለው ዲጂታል ይዘትንና ቴክኖሎጂን ባንድነት በማዋሃድ ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው መማር የሚችሉበት ነው። የዚህ ፕሮግራም ጠቀሚታው፣ ሶፍትዌር ተማሪዎችን በየራሳቸው ጊዜ፣ አቅም፣ መንገድ ወይም ስፍራ መማር የሚያስችል መሆኑ ነው። የመላው ትምህርት ቤት ውሁድ ትምህርትን የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/blendedlearning ላይ ይገኛል።

### ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ (STEM)

በየጊዜው እየጨመረ በሚሄድ የ STEM ችሎታ (የተማሪዎች የሂሳብና ሳይንስ ስኬት)፣ ውጤታማ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የምህንድስና ልምድ፣ እና የተለምዱ ዓበይት የስቴት ስታንዳርዶች (CCSS) ላይ የሚተኩሩ ፕሮግራሞችን በመጠቀም፣ለተማሪዎች የበለጸገና አሳታፊ የ STEM ልምድ ይሰጣል። በየዓመቱ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ STEM አውደ-ርእዮች የሚካሄዱ ሲሆን፣ እነዚህም ተማሪዎች የ STEM ዕውቀትና ክሂሎታቸውን በውኑ-ዓለም አውድ ውስጥ ተግባራዊ ለማደረግ የሚያስችሉ ናቸው።

# መካለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከ6-8ተኛ ክፍሎች)

የመካለኛ ደረጃ ትምህርት ዓመታት፣ የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን የሚያገናኙ ጠቃሚ ድልድይ ሲሆኑ፣ ተማሪዎችን ወደ ወጣት ጎልማሳ እውቀታዊ ተሳትፎና ማህበራዊ ሃላፊነት የሚያሸጋግሩ ናቸው። በነዚህ ዓመታት ለእያንዳንዱ የስድስተኛ፣ የሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጠንካራና አነቃቂ የትምህርት አቅርቦትን መስጠት ዋነኛ ጉዳይ ነው። ተማሪዎቹን ለአካላዊና ማህበራዊ እድገት ለማብቃት መደገፍም እንዲሁ ዋነኛ ጉዳይ ነው።

የመካለኛ ደረጃ ትምህርት ትኩረት ጠንካራ የፕሮግራም መሰረትና በወረዳው ውስጥ ላሉ ሁሉም የመካለኛ ክፍሎች ተማሪዎች ተመጣጣኝ የክፍለ-ጊዚያት ስርጭት መኖሩን ያረጋግጣል። ከዚህ በታች በጥቅሉ የተጠቀሰው የኮርስ ክፍለ-ጊዚያት አከፋፈልም ይህንኑ ዓላማ የሚያጠናክር ነው።

## ዓበይት የመካለኛ ደረጃ ክፍሎች ትምህርቶች

### ሁሉም ይ6ተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚከተሉትን ይማራሉ፡-

- እንግሊዝኛ (ዓመቱን ሙሉ)
- ሂሳብ (ዓመቱን ሙሉ)
- ማህበራዊ ሳይንስ፣ ሳይንስና የዓለም ቋንቋ (እያንዳንዱን ቢያንስ አንድ ሴሚስተር)
- አርትና ሙዚቃ (እያንዳንዱን ቢያንስ አንድ ተርም)
- ጤናና የሰውነት ማጎልመሻ (PE) (አንድ ሴሚስተር PE እና አንድ ተርም ጤና)
- የክፍለ-ጊዜ ርዝማኔ በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ
  - ለሁሉም አስፈላጊ የኮርስ አቅርቦት፣ የክፍለ-ጊዜው ርዝማኔ (ዓመቱን ሙሉ፣ ሴሚስተር ወይም ተርም) በ A/B ፕሮግራም ወይም ሌላ ፎርማት ሊደረስበት የሚችል ሲሆን፣ በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ ያህል ለተማሪዎች ይሰጣል።*በሁሉም መካለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ የሚሆኑ በርካታ የክፍለ-ጊዜያት ድልድል (ስኬጁል) ዓይነቶች ሲኖሩ፣ እነዚህም የተለመደውንና ድብልቁን የ 4X4፣ ወይም የ A/B ክፍለ-ጊዜ ድልድል ይጨምራሉ። የ A/B ክፍለ-ጊዜ፣ በዓመት ሙሉ ክሬዲት ኮርሶች፣ በአልፎ አልፎ በሚመጡ ቀኖች *4 ኮርሶች በቀን፣ እና ከ80-90 ጥቅል ደቂቃዎች ክፍለ-ጊዜያት ተለይቶ ይታወቃል።*

### የ6ተኛ ክፍል አጋዥ ጥቅል አማራጮችና ተመራጮች

- ጥምር አጋዥ ጥቅሎች ለእንግሊዝኛና ሂሳብ፣ እንዲሁም ለሌሎች የተለያዩ አጋዦች የሚያገለግሉ ናቸው። ይህ ጊዜ አካዳሚያዊ እገዛ ለማያስፈልጋቸው ተማሪዎች ማጠናከሪያነት ያገለግላል።
- ተመራጮች ከትምህርት ቤቱ ትኩረትና ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚቀናጁ ክፍሎች ናቸው።

### ሁሉም የ7ተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚከተሉትን ይወስዳሉ፡-

የ7ተኛ ክፍል ስኬጁል ከ6ተኛ ክፍል ስኬጁል ጋር በጣም ተመሳሳይ ሲሆን፣ የሚለየው አርትወይም ሙዚቃን የሚጠይቅ መሆኑ ነው። አርት 7ተኛ ክፍል የሚወሰድ ከሆን፣ ሙዚቃ ደግሞ 8ተኛ ክፍል ይወሰዳል ወይም በግልባጩ ይወሰዳሉ። ይህም ሁለተኛ ተመራጭ ትምህርትን በስኬጁሉ ውስጥ ማካተት ያስችላል።

- እንግሊዝኛና ሂሳብ (ዓመቱን ሙሉ)
- ማህበራዊ ሳይንስና ሳይንስ (እያንዳንዱ ቢያንስ ለሴሚስተር)
- የዓለም ቋንቋ (ቢያንስ ለሴሚስተር)
- አርት ወይም ሙዚቃ (ለቪዥዋል አርት ወይም ሙዚቃ በየዓመቱ አንድ አማካሪ)
- ጤናና የሰውነት ማጎልመሻ (PE) (አንድ ሴሚስተር PE እና አንድ ተርም ጤና)
- የክፍለ-ጊዜ ርዝማኔ በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ
  - ለሁሉም አስፈላጊ የኮርስ አቅርቦት፣ የክፍለ-ጊዜው ርዝማኔ (ዓመቱን ሙሉ፣ ሴሚስተር ወይም ተርም) በ A/B ፕሮግራም ወይም ሌላ ፎርማት ሊደረስበት የሚችል ሲሆን በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ ያህል ለተማሪዎች ይሰጣል።

## የ7ተኛ ክፍል ኢጋዥ ጥቅል አማራጮችና ተመራጮች

- ጥምር ኢጋዥ ጥቅሎች ለእንግሊዝኛና ሂሳብ፣ እንዲሁም ለሌሎች የተለያዩ ኢጋዦች የሚያገለግሉ ናቸው። ይህ ጊዜ አካዳሚያዊ እገዛ ለማያስፈልጋቸው ተማሪዎች ማጠናከሪያነት ያገለግላል።
- ተመራጮች ከትምህርት ቤቱ ትኩረትና ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚቀናጁ ክፍሎች ናቸው።

## ሁሉም የ8ተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚተሉትን ይወስዳሉ:-

- እንግሊዝኛ፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ ሳይንስና ሳይንስ (ዓመቱን ሙሉ)
    - አልጀብራ ቢያንስ ለአንድ ሴሚስተር መሰጠት
- የዓለም ቋንቋ (ቢያንስ ለሴሚስተር)
    - ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጅት፣ ተማሪዎች ትምህርቱን ዓመቱን ሙሉ መወሰድ ይችሉ ዘንድ የሁለተኛ ደረጃ የአንድ ሴሚስተር ክሬዲት የሚኖረው የዓለም ቋንቋ ትምህርት በስምንተኛ ክፍል በ A/B ስኬጁል ላይ መሰጠት ይኖርበታል።
- አርት ወይም ሙዚቃ (ከሁለቱ በ7ጠኛ ክፍል የማይሰጠው፣ ቢያንስ ለአንድ ተርም)
- ጤናና የሰውነት ማጎልመሻ (PE) (አንድ ሴሚስተር PE እና አንድ ተርም ጤና)
- የክፍለ-ጊዜ ርዝማኔ በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ
    - ለሁሉም አስፈላጊ የኮርስ አቅርቦት፣ የክፍለ-ጊዜው ርዝማኔ (ዓመቱን ሙሉ፣ ሴሚስተር ወይም ተርም) በ A/B ፕሮግራም ወይም ሌላ ፎርማት ሊደረስበት የሚችል ሲሆን[3] በየቀኑ ቢያንስ 45 ደቂቃ ያህል ለተማሪዎች ይሰጣል።
    - የ8ተኛ ክፍሉ ስኬጁል አራቱን ዓበይት የትምህርት ዓይነቶች ዓመቱን ሙሉ ማካተት አለበት፤ ይህም ለሁለተኛ ደረጃ በደንብ ያዘጋጃል።

## የ8ተኛ ክፍል ተመራጭ ትምህርቶች

- ተመራጮች ከትምህርት ቤቱ ትኩረትና ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚቀናጁ ክፍሎች ናቸው። ተመራጮች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለኢጋዥነት ወይም ለአማካሪነት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

የመካከለኛ ደረጃ ክፍሎችን ትምህርት ልምድ የተሻለ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮግራሞችን መጠቀም ይቻላል። እነዚህም የሚከተሉትን የጨምራሉ፤ በነዚህ ብቻ ግን የሚወሰኑ አይደሉም:-

- የተራዘሚ ቀን ፕሮግራም:- ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በዩኒየኑ ኮንትራት መሰረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመክፈል፣ የትምህርት ቀናትን በየቀኑ ለአንድ ሰዓት ያህል እስከ 4:15 ፒ.ኤም. ማራዘም። በሰራተኞች የተደገፈ እቅድ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ።

- የማህበረ-ስሜታዊ ሰራተኛ:- በትምህርት ዘመኑ ለእያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ክፍሎች ትምህርት ቤት የጋይዳንስ ካውንስለር ይመደባል። የጋይዳንስ ካውንስለሮች የተማሪዎችን ማህበረ-ስሜታዊ ችግሮች በመፍታት ላይ ያተኩራሉ።

- የመስክ ልምድና ጉብኝት:- ተማሪዎች ከተማውንና አካባቢውን እንደ ትምህርት ኢጋዥ ምንጭ ይጠቀማሉ። የመስክ ጉዞዎች አካባቢያዊና ዓለም-አቀፋዊ ጉዞዎችን፣ እንዲሁም የኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ጉብኝትን ይጨምራሉ። በተጨማሪም፣ ለሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች በየክረምቱ የሁለት-ሳምንታት ፕሮግራም (ዲሲ ከዋሽንግተን ይገናኛል) ይኖራል። ፕሮግራሙ ተማሪዎችን ዋሽንግተን ውስጥ ባሉ የስራ መስኮች ከፍተኛ ክፍያና ሙያ ካላቸውና መልካም አርአያ (ሮል ሞዴል) መሆን ከሚችሉ ሰዎች ጋር ያስተዋውቃቸዋል፤ በጥንቃቄ ወደሚመራ የስራ ቦታ ጉብኝትም በመውሰድ ስለ ግንባታ፣ ምህንድስና፣ የአይቲ እና መስተንግዶ ስራዎች ከባለሙያዎቹ ከራሳቸው በግምባር መማር ያስችላቸዋል። በመጨረሻም፣ ተማሪዎች ከፍተኛ ክፍያና ከፍተኛ:የሙያ እድገት መሰላል ያላቸውንና የትምህርት እድልም ሊሰጡ:የሚችሉትን የDCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንና የዲሲ ኮሌጆችን ይጎበኛሉ።

- የትምህርት ማበልጸጊያ እድሎች:- የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከተለያዩ ልምዶችና የትምህርት መስኮች ጋር መተዋወቅ ይፈልጋሉ። እንዲህ ያሉቱ አብዛኛዎቹ ፍላጎቶች፣ በየቀኑ ፕሮግራም በሚያዝላቸው ክለቦች፣ የማበልጸጊያና ኢጋዥ ተግባራት አማካኝነት ከግብ የሚደርሱ ናቸው። የDCPS ግብ፣ ተማሪዎች በሶስቱ ዓመታት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታቸው የሚሳተፉባቸውን በየትምህርት ቤቱ ያሉ የሙዚቃ ባንዶችን፣ ኳየሮችንና/ወይም ሌሎች የሙዝቃ ትምህርት ክፍሎችን መደገፍ ነው። ይህንንም ሙዚቃና ጤና-ነክ ተጨማሪ ስርዓተ-ትምህርታዊና ትምህርታዊ ድጋፍ በየትምህርት ቤቱ ሁለት የትርፍ-ሰዓት ባለሙያዎች ይሰጣሉ። የDCPS የአትሌቲክስ ዲፓርትመንት በሚያኪያሄደው የተማሪዎች ፍላጎት ቅኝት ውጤት ላይ በመመስረት፣ ለመካከለኛ ደርጃ ትምህርት ክፍሎች ተማሪዎች ልዩ ልዩ የአትሌቲክስ እድሎች ተለይተው ይሰጣሉ። የአትሌቲክስ ዲፓርትመንቱ እነዚህን የአትሌቲክስ እድሎች ለመደገፍ የሙሉ ጊዜ የአትሌቲክስ አሰልጣኝና የአትሌቲክስ ደንቦች አስተባባሪ አለው።



## ልዩ ፕሮግርሞችና ትምህርታዊ አቅርቦት

### ከፍተኛና የበለጸገ ትምህርት

የDCPS ሁሉም ተማሪዎች ተፈጥሯዊ ተሰጥኦዎች (talents) እንዳሏቸው ያምናል። ማንኛውም ከአማካይ አካዳሚያዊ ውጤት በላይ የሚያስመዘግብ/የምታስመዘግብ ልዩ ፈጠራዊነትና/ወይም ከፍተኛ ደረጃ የስራ ቁርጠኝነት ያለው/ያላት ተማሪ በከፍተኛ አካዳሚያዊ ተግባር ወስጥ ለመሳተፍ እድል ይኖረዋል/ይኖራታል። ትምህርት ቤት-አቀፍ የትምህርት ማበልጸጊያ ሞዴል SEM) እና መኻለኛ ታላቅ መጻህፍት በዲሲ.ህ.ት.ቤ.ት መምህራን የሚተገበሩ የዚህ ትምህርታዊ ተግባር ሁለት ምሳሌዎች ናቸው። ከፍተኛና ብልጽግ ትምህርት የህገወጥ መድሃኒት አጠቃቀም ማከላከያ ትምህርት (DARE) መራፎችና የኤም2/ኤም3 ሂሳብ ካሪኩለም ፕሮጄክትም ከመስጠቱም በላይ፣ ዓለም-አቀፍ የባካዩልሬት ፕሮግርማንም በበላይነት ይመራል።

### ከኻለኛ ታላቅ መጻሕፍት

በዚህ ከመዋእል-ህጻናት-8 ክፍል በሚሰጠው፡ፕሮግራም አማካኝነት፣ ተማሪዎች ውስብስብና በጭብጥ የበለጸጉ ስነጽሁፋዊ መጻሕፍትን ያነባሉ፤ ይወያዩባቸዋል። የመኻለኛታላቅ መጻህፍት ስርዓተ-ትምህርት በ45 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛል። ይህን ፕሮግራም የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/academics ላይ ይገኛል።

### ትምህርት ቤት-አቀፍ የማበልጽጊያ ሞዴል (SEM)

SEM ከተለምዷዊው አቀራርብ የተለየ ልዩ ተፈጥሯዊ ስጦታና ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች በማበልጸጊያ-ተኮር ሞዴል በመጠቀም የተለየ አስቸጋሪና ፈታኝ ትምህርታዊ ልምድ የሚያገኙበት አቀራረብ ነው። ተማሪዎች ከ SEM እና ሰብአዊ ሳይንስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውና ልዩ ልዩ ርእሰ-ጉዳዮችን ያካተቱ ኮርሶችን በመመርመር ፍላጎታቸን ለይተው ካወቁ በኋላ፣ የትምህርት በኢታቸውን ወይም ማህበርሰባቸውን ይሚመለከቱ ችግሮችን ለመፍታት በተለይ በተዘጋጁ ፕሮጄክቶች ውስጥ ይሰራሉ። የ SEM ፕሮግራም ያላቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/academics ላይ ይገኛል።

### ውሁድ ትምህርት

ውሁድ ትምህርት የግምባር-ለግምባር ትምህርትንና ከፍተኛ ጥራት ያለው ዲጂታል ይዘትንና ቴክኖሎጂን ባንድነት በማዋሃድ ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው መማር የሚችሉበት ነው። የዚህ ፕሮግራም ጠቀሚታው፣ ሶፍትዌር ተማሪዎችን በየራሳቸው ጊዜ፣ አቅም፣ መንገድ ወይም ስፍራ መማር የሚያስችል መሆኑ ነው። ይህን ፕሮግራም የሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/academics ላይ ይገኛል።

### ምሶሶዎች

ምሶሶዎች ተማሪዎች በDCPS በየክፍል ደረጃውና የትምህርት ዓይነቶች፣ ማለትም እንግሊዝኛ ቋንቋ አርትን፣ ሂሳብን፣ ሳይንስን፣ መራዊ ሳይንስን፣ አርትን፣ ጤናንና የሰውነት ማጎልመሻን፣ እና የዓለም ቋንቋን ጨምሮ፣ በሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ምእራፎች አማካኝነት የሚሳተፉባቸው ዓቢይና ጥልቅ የስርዓተ-ትምህርት ልምዶች ናቸው። ምሶሶዎች፣ ከፍተኛ የጥራት ደርጃና ውሱን-ይዘት ባላቸው የትምህርት ሞዴሎች ላይ ተመስርተው፣ ለተማሪዎች ጠንከር ያሉ የትምህርት ይዘቶችን ከመስጠታቸውም በላይ፣ ለመምህራን በሁሉም የክፍል ደረጃና በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በተማሪ ስራ ላይ የሚያተኩሩ፣ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያላቸው የተሻሻሉ ሙያዊ እድገትን ይሰጣሉ። የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው የምሶሶዎች ልምዶች ቁጥር የተለያየ ነው። ለተጨማሪ መርጃ፣ ዌብሳይቱን በ dcps.dc.gov/page/cornerstones ይመልከቱ ወይም የትምህርት ቤትዎን መምህር ያነጋግሩ።

### ዓለም-አቀፋዊ ባክሎሬት መካከለኛ ዓመታት ፕሮግራም (ከ6-8ተኛ ክፍሎች)

የመካከለኛው ዓመታት ፕሮግራም (MYP) ለጥልቅ ምርመራና መረዳት (critical thinking) እና ዓለም-አቀፋዊ ትኩረት አጽንኦት የሚሰጥ ስርዓተ-ትምህርት ሲሆን፣ ለተማሪዎች እራሳቸውን ችለው የምርምር ስራ እንዲያከናውኑ እድል የሚሰጥ ነው። የመካከለኛው ዓመታት ፕሮግራም፣ ተማሪዎችን በምርምር ስራ ውስጥ የሚያሳትፍ ፈርጀ-ብዙ-ምርምር-ምስርት አቀራረብ ሲሆን፣ ይህም በእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት በሚመረጡ ምርምር-ምስርት ፕሮጀክቶችን ማኪያሄድን፣ ሁለተኛ ቋንቋ መማርንና የጥልቅ ምርመራና መረዳት ክሂሎታቸውን በተግባር ላይ ማዋልን የሚጨምር ነው። ተማሪዎች ሶስቱን የመካከለኛ ደረጃ ዓመታት ሲያጠናቅቁ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለመጋፈጥ በደንብ ዝግጁ ይሆናሉ። ይህን ፕሮግራም የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና በ dcps.dc.gov/DCPS/IB ላይ ይገኛል።

### ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ (STEM)

በየጊዜው እየጨመረ በሚሄድ የ STEM ችሎታ (የተማሪዎች የሂሳብና ሳይንስ ስኬት)፣ ውጤታማ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የምህንድስና ልምድ፣ እና የተለምዱ ዓበይት የስቴት ስታንዳርዶች (CCSS) ላይ የሚተኩሩ ፕሮግራሞችን በመጠቀም፣ለተማሪዎች የበለጸገና አሳታፊ የ STEM ልምድ ይሰጣል። በየዓሙቱ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ STEM አውደ-ርእዮች የሚካሄዱ ሲሆን፣ እነዚህም ተማሪዎች የ STEM ዕውቀትና ክሂሎታቸውን በውኑ-ዓለም አውድ ውስጥ ተግባራዊ ለማደረግ የሚያስችሉ ናቸው።

### የዓለም ቋንቋ አቅርቦት

የDCPS ሁለት የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ፕሮግራም ሞደሎች ይሰጣል፡-ተለምዷዊና ጠላቂ ተሻጋሪ የቋንቋ ፕሮግራሞች። ተለምዷዊ ፕሮግራሞች አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ላቲን፣ ማንደሪንና ስፓኒሽ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣሉ። ይህ ፕሮግራም ለቋንቋ ትምህርት አዲስ ለሆኑ፣ ከአንደኛ ደረጃ የውጭ ቋንቋ (FLES) ክፍልና የአንደኛ ደረጃ የውጭ ቋንቋ አሰሳ (FLEX) ክፍል ለመጡ ተማሪዎች የሚሰጥ ነው። ተላቂ ተሻጋሪ ፕሮግራም፣ ወይም የስፓኒሽ ሰብአዊ ሳይንስ (SH) ብስፓኒሽ ቋንቋ ብቻ የሚሰጥ ነው። ይህ ፕሮግራም የDCPS ጥምር ቋንቋ ጠለቃ (DLI) ፕሮግራሞችን በውጤታማነት ላጠናቀቁ ተማሪዎች ወይም በላቀ የቋንቋ ችሎታቸው መሰረት ለተመደቡ ተማሪዎች የሚሰጥ ነው።

# ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12ኛ ክፍሎች)

የDCPS ተልእኮ ተማሪዎቻችንን ሁለተኛ ደርጃን ከማጠናቀቅ ባሻገር ላለ ስኬት፣ ማለትም ለኮሌጅ፣ ለስራና ለህይወት ማዘጋጀት ነው። ዓላማችን ተማሪዎቻችንን ለከፍተኛ ደረጃ ስኬት ለማብቃት፣ ህልማቸውን እውን ማድረግ እንዲችሉና በመጨርሻም ለሚኖሩበት ዓለም አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉ መርዳት ነው። ይህን ተልእኮ ለማሳካት የDCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወሳኝ ናቸው። እያንዳንዱ ተማሪ የየራሱ/ሷ የተለያዩ ፍላጎቶችና ራእዮች ያሉት/ሏት ሲሆን፣ እኒህንም እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የተሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አማራጮችን እንሰጣለን። የDCPS ዘጠኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ስድስት ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሰጡ የተለያዩ የሙያ ፕሮግርሞችን ይመራል። (በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ስላሉት አካዳሚያዊ ፕሮግራሞች ተጨማሪና ዝርዝር መረጃ አባሪ ውስጥ ይገኛል)።

## ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ (የሰፈር) ትምህርት ቤቶች

የDCPS ከፍተኛ ኮርሶችን፣ ከክፍል ውጭ የሚሰጡ የትምህርት እድሎችንና የሙያ ፕሮግራሞችን ቅምር ስፋት ያላቸው አካዳሚያዊ አቅርቦትን የሚያካትቱ፣ የማንኛውንም ተማሪ የመማር መብት የሚያከብሩ ዘጠኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች አሉት። ይህም ለሁሉም ተማሪዎች የኮሌጅና የስራ አማራጮችን ይሰጣል። ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤቱን ፕሮፋይል በ profiles.dcps.dc.gov ላይ ይመልከቱ። ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ የሚከትሉት ናቸው፦

- Anacostia HS
- Ballou HS
- Cardozo Education Campus
- Coolidge HS
- Dunbar HS
- Eastern HS
- H.D. Woodson HS
- Roosevelt HS
- Wilson HS

## ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ድንበር-የለሽ መላውን ከተማ-አቀፍ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ የራሱ የሆኑ የተማሪ ቅበላና መምረጫ መስፈርት አሉት። አንዳንድ ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰፊ የኮርስ አቅርቦት ስብስብሲሰጡ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከአርት ጀምሮ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን በመሳሰሉ የተወሰኑ የትምህርት ዘርፎች ላይ ያተኩራሉ። የDCPS በአሁኑ ወቅት ስድስት ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉት። ስለ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተጨማሪ መረጃና የማመልከቻ ሂደት በ dcps.dc.gov/DCPS/specializedhs ላይ ማግኘት ይቻላል። ልዩ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶቹ የሚከተሉት ናቸው፦

- Benjamin Banneker HS
- Columbia Heights EC
- Duke Ellington School of the Arts
- McKinley Technology HS
- Phelps Architecture, Construction, and Engineering HS
- School Without Walls HS

## የሙያ ትምህርት

የDCPS አካዳሚያዊ ጥንካሬን የተላበሱ የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚሰጥ ሲሆን፣ እነዚህም ተማሪዎችን ለቀጣይ የኮሌጅ ትምህርትና ለሌሎች የተለያዩ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ስልጠናና በመጨረሻም ለፍሬያማ የስራ መስክ የሚያዘጋጁ ናቸው። የDCPS ግብ ሁሉም የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞቻችን ጠንካራ፣ አሳታፊና ወደ ኮሌጅ ትምህርት የሚያመሩ መሆናቸውንና የሚከተሉትን አላባዎች የሚያካትቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፦



- ከተማው ከፍተኛ የደሞዝ ከፍያና ከፍተኛ-ተፈላጊነት ያላቸው የስራ መስኮች ጋር የተጣጣሙ፤
- በተለያዩ የስራ መስኮች የብቃት ማረጋገጫ እውቅና ያለው ሰርቲፊኬት/ቶች የሚያስገኙ ጠንካራ ስርዓተ-ትምህርቶችን ማቀረብ፤
- ፀበስራ ላይ የተመሰረቱ የትምህርት እድሎችን (ኢንተርንሺፖች፣ የእውቅ ስራተኞች ረዳትነት (job shadows)፣ ተጋባዥ ተናጋሪዎች) ማቅረብ፤

የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች ዝርዝር አባሪ ውስጥና ኦንልይን በ http://dcps.dc.gov/page/college-and-career-planning ይገኛል።

## ዓበይት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች (በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)

የDCPS የብቃት ደረጃዎች በሁሉም ስቴቶች ውስጥ ካሉ እጅግ ጠንካራና ከኮሌጅ ጋር የተጣጣሙ እንደሆኑ ከሚታወቁት አንዱ ናቸው። እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለኮሌጅ ትምህርትና ለስራ ስኬት የሚያደርጉትን ዝግጅት ለመደገፍ የተዘጋጁ ዓቢይ አካዳሚያዊ ፕሮግራም ይሰጣል። ይህም ዓቢይ ፕሮግራም ከዲሲ የሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ምረቃ መስፈርትና ዓበይት የጋራ የስቴት ደረጃዎች (Common Core State Standards) ጋር የተጣጣመ ነው። ዓቢይ ፕሮግራሙ በሚከተሉት የትምህርት ዘርፎች ውስጥ የሚካተቱ የኮርስ አቅርቦትን ይይዣል፦

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት (ቢያንስ 4 ክሬዲቶች)
- ሂሳብ (ቢያንስ 4 ክሬዲቶች)
- ማህበራዊ ሳይንስ (ቢያንስ 4 ክሬዲቶች)
- ሳይንስ (ቢያንስ 4 ክሬዲቶች)
- የዓለም ቋንቋዎች (ቢያንስ 2 ክሬዲቶች)
- አርት (ቢያንስ 0.5 ክሬዲት)
- ሙዚቃ (ቢያንስ 0.5 ክሬዲት)
- የጤናና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (ቢያንስ 1.5 ክሬዲቶች)
- ተመራጮች (ቢያንስ 3.5 ክሬዲቶች)

በተጨማሪም፣ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ ሁለት ክሬዲት ያላቸው የኮሌጅ-ደረጃ ወይም የሙያ-ማዘጋጃ ኮርሶችን መውሰድ አለባቸው። ይህም የግድ መሆኑ የተማሪዎቹን ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ስኬት ዝግጁነት ለማረጋገጥ ይረዳል።

## ልዩ ፕሮግራሞችና አካዳሚያዊ አቅርቦት

### የዘጠነኛ ክፍል ትምህርት

እያንዳንዱ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች በተሳካ ሁኔታ ወደ ሁለተኛ ደረጃ እንዲሸጋገሩና ወደ 10ኛ ክፍል እንዲያልፉ ለመርዳት የሚያስችል የዘጠነኛ ክፍል ትምህርት አለው። የዚህ ፕሮግራም ሞዴል በአራት ስትራቴጂዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፦ ዴታ-ምስርት ውሳኔ አወሳሰን፤ የአስተማሪ ስታፍ ማቀናጀት፤ የተማሪዎቹን የትምህርት ፍላጎት ለሚሟላት የሚያስችል ፕሮግራም፤ እና የተማሪዎች ተሳትፎ።

### የኮሌጅ ደረጃ ኮርሶች

ከፍተኛ ምድብ (AP)፦የDCPS በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ምድብ (AP) ኮርሶችን ይሰጣል። ከፍተኛ ምድብ ኮርሶች ተማሪዎች በኮሌጅ ትምህርት ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ የሚያስፈልጓቸውን ክሂሎትና ልምዶች ለማዳበር ይረዷቸዋል። ተማሪዎች የጽህፈት ክሂሎታቸውን ያሻሽላሉ፣ የሰላ የችግር-ፈቺነት ችሎታ ይኖራቸዋል፣ እንዲሁም የጊዜ-አጠቃቀም ክሂሎትና የጥናት ልምድ ያዳብራሉ። ተማሪዎች በትምህርት ዘመኑ መጨረሻ ላይ የከፍተኛ ምድብ ኮርሶች ፈተና በመውሰድ፣ የኮሌጅ ክሬድት የማግኘትና ከመጀምሪያ ዓመት የኮሌጅ ኮርሶች ነጻ የመሆን እድልም ይኖራቸዋል። ተማሪዎች በከፍተኛ ምድብ ኮርሶች መሳተፋቸው ጠንከር ያሉ ኮርሶች በመውሰድ ለኮሌጅ ትምህርታቸው መዘጋጀታቸውን ለኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ይጠቁማል። በየሁለተኛ ደረጃው የሚሰጡ ከፍተኛ ምድብ ኮርሶች አባሪ ውስጥ ተዘርዝረዋል፤ ለተጨማሪ መረጃ፣ የልጅዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር ያነጋግሩ።

እጥፍ ምዝገባ (Dual Enrollment)፦ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎቻችን ጎን ለጎን ክሬዲት የሚያሰጧቸው ኮርሶችን በኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ መውሰድ ይችላሉ። በሚከተሉት ትምህርት ቤቶችና ፕሮግራሞች፣ ተማሪዎች የተፈቀዱላቸውን ኮርሶች በስኬት ካጠናቀቁ በአንድ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃና የኮሌጅ እጥፍ ክረዲት (dual credit) ማግኘት ይችላሉ፦ GW Early College Program at Schools Without Walls HS and the Banneker/McKinley HS Howard University Early College Program በተጨማሪም፣ በዲሲ ዩኒቨርሲቲ ኮሙኒቲ ኮሌጅ (UDC-CC) ለተፈቀደላቸው ተማሪዎች በእጥፍ ክሬዲት የሚሰጡ 13 ኮርሶች አሉ፤ ለነዚህም የትምህርት ቤቱ ካውንስለርና ዲሬክቴር ፈቃድ ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት በሁሉም የDCPS የእጥፍ ክሬዲት ኮርሶችን ለመስጠት ከኮሌጆች ጋር ያለንን አጋርነት ለማስፋፋት እየሰራን ነው። ለተጨማሪ መረጃ በ http://dcps.dc.gov/service/dual-enrollment-program ላይ ይመልከቱ ወይም የትምህርት ቤትዎን ካውንስለር በማነጋገር ስለ እጥፍ ምዝገባ እድሎች ይረዱ።

ዓለም-አቀፋዊ የባክዩሎሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም (ከ11ኛ-12ኛ ክፍሎች)፦የዲፕሎማው ፕሮግራም (DP) ለጥልቀት ምርመራና መረዳትና ዓለማቀፋዊ ትኩርት አጽንኦት የሚሰጥ ስርዓተ-ትምህርት ሲሆን፣ ለተማሪዎች እራሳቸውን ችለው የምርምር ስራ እንዲያከናውኑም እድል የሚሰጥ ነው። ዲፕ በታም ጠንካራና ሙሉ ትኩረት የሚሻ የሁለት ዓመት ቅድመ-ዩኒቨርሲቲ ፕሮግራም ሲሆን፣ ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸውን ተማሪዎች ፍላጎት የሚያሟላ ነው። የDCPS በሚከተሉት ትምህርት ቤቶች የዲፕ ፕሮግራም ይሰጣል፦ Banneker and Eastern High Schools.

## ምሶሶዎች

ምሶሶዎች ተማሪዎች በDCPS በየክፍል ደረጃውና የትምህርት ዓይነቶች፣ ማለትም እንግሊዝኛ ቋንቋ አርትን፣ ሂሳብን፣ ሳይንስን፣ መራዊ ሳይንስን፣ አርትን፣ ጤናንና የሰውነት ማጎልመሻን፣ እና የዓለም ቋንቋን ጨምሮ፣ በሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ምእራፎች አማካኝነት የሚሳተፉባቸው ዓቢይና ጥልቅ የስርዓተ-ትምህርት ልምዶች ናቸው። ምሶሶዎች፣ ከፍተኛ የጥራት ደርጃና ውሱን-ይዘት ባላቸው የትምህርት ሞዴሎች ላይ ተመስርተው፣ ለተማሪዎች ጠንከር ያሉ የትምህርት ይዘቶችን ከመስጠታቸውም በላይ፣ ለመምህራን በሁሉም የክፍል ደረጃና በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በተማሪ ስራ ላይ የሚያተኩሩ፣ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያላቸው የተሻሻሉ ሙያዊ እድገትን ይሰጣሉ። የሁለተኛ ደረጃ ደረጃ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው የምሶሶዎች ልምዶች ቁጥር የተለያየ ነው። ለተጨማሪ መርጃ፣ ዌብሳይቱን በ dcps.dc.gov/page/cornerstones ይመልከቱ ወይም የትምህርት ቤትዎን መምህር ያነጋግሩ።

## International Academy at Cardozo EC

የካርዶዞ ትምህርታዊ ካምፓስ ዓለም-አቀፋዊ አካዳሚ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጀመሩ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አሜሪካ የመጡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመርዳት የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው። የDCPS Internationals Network for Public Schools (INPS) ከተባለውና መቀመጫውን ኒው ዮርክ ያደረገ በትርፍ-ላይ-ያልተመሰረተ ብሄራዊ የትምህርት ቤት ልማት ድርጅት ጋር አጋርነት ያለው ሲሆን፣ ድርጅቱም በቅርቡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመጡ ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት ነው።

## ትዋይላይት/ኢንቪዥን ፕሮግራሞች (Twilight/Envision Programs)

የትዋይላይት (የምሽት ጀምበር) ፕሮግራሞች፣ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰው የትምህርት ደረጃቸውን ማሻሻል ወይም መመረቅ ለሚፈልጉ በእድሜ ለገፉና በቂ ክሬዲት ለሌላቸው ተማሪዎች የተዘጋጁ ናቸው። የትዋይላይት ክፍሎች ከሰዓት-በኋላና ማታ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጣሉ፡- Dunbar, Anacostia and Eastern. ኢስተርን (ምስራቃዊ) የሚለው መጠሪያ፣ ፕሮግራሙ የ "ብሩህ ተስፋ" ፕሮግራም መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የኢህ ፕሮግራም ተማሪዎች ባጠቃላይ ከ16-19 እድሜ ያላቸው ሲሆን፣ ከ1-2 ዓመት (ከ 2 ዓመት ግን ላልበለጠ) ከአቻዎቻቸው ወደ ኋላ የቀሩ ናቸው። ይሄ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ፕሮግራም ነው።

## በስራ ላይ የተመሰርቱ ፕሮግራሞች

የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚከታተሉ በርካት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የ National Academy Foundation (NAF) ፕሮግራሞችን ጨምሮ፣ በትምህርት ዓመቱና በክረምት ጊዜም በየሚማሯቸው የትምህርት መስኮች ስራ እየሰሩና እየተከፈላቸው መማር በሚችሉባቸው ፕሮግራሞች የመሳተፍ እድል ይኖራቸዋል።

### ለወላጅ ምክር፡- ልጅዎን በቤት ስራዎች ስለ መርዳት

*የቤት ስራዎች ልጆችዎ በትምህርት ቤታቸው ስለ ተማሯቸው ነገሮች በተግባር መለማመጃ ናቸው። ተማሪዎች ለቤት ስራ መልመጃዎቻቸው ፍሬያም ጊዜ ሲሰጡ፣ በትምህርታቸው ስኬታማ የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ይሆናል።*

*እንደ አጠቃላይ መመሪያ፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረጋቸው ጠቃሚ ነው፡-*

- *ከመዋእለ-ህጻናት-2ኛ ክፍሎች፡- በየቀኑ ከ10-20 ደቂቃዎች የቤት ስራ መስራት፤*
- *ከ3-6ኛ ክፍሎች፡- በየቀኑ ከ30-60 ደቂቃዎች የቤት ስራ መስራት፤ እና*
- *ከ7-12ኛ ክፍሎች፡- በየቀኑ ከአንድ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ የቤት ስራ መስራት፤ በየማታው የሚመደበው ጊዜ የተለያየ ሊሆን ይችላል።*

*ልጅዎን በቤት ስራ ረግድ መርዳት የሚችሉባቸው ጥቂት መንገዶች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡-*

1. *ስለ ልጅዎ የቤት ስራ ምን እንድሚጠብቁ ከልጅዎ መምህራን ጋር ይነጋገሩ። በቤት ስራ ላይ ምን ያህል ጊዜ ማጥፋት ይገባል? የእርስዎስ ሚና ምን መሆን አለበት?*
2. *ለልጅዎ የቤት ስራ መስሪያ፣ ጸጥታ ያለበት፣ በቂ ብርሃን ያለው መደበኛ ቦታና ጊዜ ይመድቡ። ጤናማ ቅምሻ (snack) መስጠትም ይረዳል።*
3. *ልጅዎ አስፈላጊዎቹ መሳሪያዎች እንዳለው/ላት (ወረቀት፣ እርሳሶች፣ መጻህፍት፣ ወዘተ.) ያረጋግጡ።*
4. *ስለ የቤት ስራ አዎንታዊ አመለካከት ይኑሮት""*
5. *ልጆችዎ የቤት ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ መልሶችን ለመንገር ሳይሆን ለማበረታት ቀርበው ይመልከቷቸው።*
6. *ልጅዎ የቤት ስራዎቹን መስራት የሚቸግረው ከሆነ/ች ለመምህራኑ ያሳውቁ።*

# አካዳሚያዊ መስፈርት

## ከክፍል ወደ ክፍል ዝውውርና በትምህርት ገበታ ላይ ማስቀጠል

የዲሲ ከተማ ካውንስል በ2013 የደነገገው መመሪያ (Focused Student Achievement Act of 2013) የዲሲ.ህ.ግ.ት.ቤ.ት.ተማሪዎችን የዝውውርና በትምህርት ላይ መቆያ መስፈርት ለውጧል።

ከቅድመ-መዋእለ ህጻናት 4-8 ክፍሎች ድረስ፣ መምህሩ በሚሰጠው ሃሳብና በተማሪው/ዋ የማለፊያ ውጤቶች ላይ በመመስረት፣ ዲሪክቴሩ የተማሪው/ዋን የመጨረሻውን የዝውውርና በትምህርት ላይ መቀጠል/አለመቀጠል ውሳኔ ይወስናል።

- ከ9-12ኛ ክፍሎች፣ የልጅዎ ዝውውር ለየክፍሉ የሚያስፈልጉትን ክሬዲቶች ማሟላት በመቻል ወይም አለመቻሉ/ሏ ላይ ይወሰናል።
- ወደ 10ኛ ክፍል ለመዘዋወር፣ ተማሪዎች የ9ኛ ክፍልን እንግሊዝኛ አልጄብራ 1 ፈተና ማለፍና ቢያንስ 6 ክሬዲቶች ማጠራቀም መቻል ይጠበቅባቸዋል።
- ወደ 11ኛ ክፍል ለመዘዋወር፣ ተማሪዎች የ10ኛ ክፍልን እንግሊዝኛ 2 ፈተና ማለፍና ቢያንስ 12 ክሬዲቶች ማጠራቀም መቻል ይጠበቅባቸዋል።
- ወደ 12ኛ ክፍል ለመዘዋወር፣ ተማሪዎች የ11ኛ ክፍልን እንግሊዝኛ 3 ፈተና ማለፍና ቢያንስ 18 ክሬዲቶች ማጠራቀም መቻል ይጠበቅባቸዋል።

ስለ ዝውውርና በትምህርት ላይ ስለ መቀጠል ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የልጅዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር ያነጋግሩ።

**ምክር ለወላጆች**

*ልጆችዎ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው በኋላ ምን እንደሚሆኑ ለማሰብ 12ኛ ክፍል እስኪደርሱ አይጠብቁ። ከመዋእለ-ህጻናት ጀምሮ፣ ልጆችዎ በትክክለኛው አካዳሚያዊ መንገድ ላይ መሆናቸው ለማረጋገጥ ከልጆችዎና መምህራኖቻቸው ጋር ዘወትር ይነጋገሩ። ልጆችዎ የህይወት ግባቸውን እንዲወስኑ ይርዷቸው። ስኬቶቻቸውን ያክብሩ፤ አስቸጋሪ ነገሮች ሲያጋጥሟቸው ደግሞ እርዳታዎን ይለግሷቸው።*



## የምረቃ መስፈርት (ለሁለትኛ ደረጃ ት/ቤት)

የDCPS ዲፕሎማ ለማግኘት ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት ቢያንስ 24 ክሬዲቶች ሊኖራቸው ይገባል፡-

| የትምህርት ዓይነት | ክሬዲት |
|---|---|
| አርት | 0.5 |
| ተመራጮች | 3.5 |
| እንግሊዝኛ | 4.0 |
| ጤናና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት | 1.5 |
| ሂሳብ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-<br>• አልጄብራ 1<br>• ጂኦሜትሪ<br>• አልጄብራ 2<br>• ከፍተኛ ደረጃ ሂሳብ | 4.0 |
| ሙዚቃ | 0.5 |
| ማህበራዊ ሳይንስ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-<br>• ባዮሎጂ<br>• 2 የቤተ-መከራ (ላብ) ሳይንሶች<br>• 1 ሌላ ሳይንስ | 4.0 |
| ማህበራዊ ሳይንስ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-<br>• የዓለም ታሪክ 1 እና 2<br>• የዲስ ታሪክ<br>• የዩኤስ መንግስት<br>• የዩኤስ ታሪክ | 4.0 |
| የዓለም ቋንቋ | 2.0 |
| አጠቃላይ ክሬዲቶች | 24.0 |

በተጨማሪም ልጅዎ የሚከተሉትን መስፈርት ማሟላት መቻል አለበት/ባት፡-

- መሟላት ከሚገባቸው 24ቱ ክሬዲቶች መካከል ቢያንስ 2ቱ ከኮሌጅ ደረጃ ወይም የሙያ መዘጋጃ፣ ከፍተኛ ምድብ፣ ዓለም-አቀፋዊ ባክዩሎሬት ወይም የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ኮርሶች የተገኙ መሆን አለባቸው።
- 100 ሰዓታት የማህበረሰብ ግልጋሎት መስጠት

ልጅዎ ልዩ ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ/ች፣ ተጨማሪ አካዳሚያዊ ጉዳዮችን ማሟላት ወይም የማህበረሰብ ግልጋሎት መስጠት ሊጠበቅበት/ባት ይችላል።

ለምረቃ መሟላት ስለሚገባቸው ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃ ካስፈልግዎ፣ የሚከተለውን ዌብሳይት ይመልከቱ፡- http://dcps.dc.gov/page/graduation-requirements።

## ናቪያንስ/የቤተሰብ ትስስር (Naviance/Family Connections) (መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)

ናቪያንስ/የቤተሰብ ትስስር የኮሌጅና ስራ (ሙያ) ዝግጁነት ኦንላይን ፕሮግራም ሲሆን፣ የDCPS መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችና ቤተሰቦች ስለ ኮሌጅና ስራ ያሉ እድሎችን መቃኘት፣ እንዲሁም ስለ ወደፊቱ የኮሌጅ ትምህርት ስኬት ተገቢ እቅድ ማዘጋጀትና የኮሌጅ ማመልከቻዎቻቸውን መከታተል እንዲችሉ አስፈላጊውን መረጃና መሳሪያ የሚሰጥ ነው። ኮርሶች እየወሰዱ መቆየት፣ ተማሪዎች ግቦቻቸውን መንደፍ፣ ለቀጣይ የኮሌጅ ትምህርት፣ ብሎም በስራ መስክና ህይወታቸው ስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቅ እንዲችሉ ይረዳቸዋል። ወላጆች የልጆቻቸውን የናቪያንስ አካውንት በቤተሰብ ትስስር አማካኝነት ሊመለከቱ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ በ http://dcps.dc.gov/node/1013072 ይመልከቱ ላይ ወይም የልጅዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር ያነጋግሩ።

## ክሬዲት ማካካሻ (ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)

የDCPS በትምህርታቸው ወደ ኋላ ለቀሩ ተማሪዎች በልማዳዊው ወይም በውሁድ የመማር ሞዴሎች አማካኘነት የጎደሏቸውን ክሬዲቶች ማካካስና ወደ ለምረቃ የሚያበቃ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችሉ በርካታ እድሎችን ይሰጣል። ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማታ ክሬዲት ማካካሻ ፕሮግራሞችን ይሰጣሉ። ለተጨማሪ መረጃ የልጅዎን ት/ቤት ካውንስለር ያነጋግሩ።

**ምክር ለወላጆች**

*ልጆችዎ ለምረቃ የሚያደርስ መንገድ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡-*

1. *በ9ኛ ክፍል ትምህርት መጀመሪያ ላይ ልጅዎ ከትምህርት ቤቱ ካውንስለር ጋር በሚደረገው ስብሰባ ላይ ይገኙ። ስለ ትምህርት ግቦች፣ መወሰድ ስለሚገባቸው ኮርሶችና ተጓዳኝ ስርዓተ-ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ይነጋገሩ።*
2. *ስለ ልጅዎ ትምህርት አቀባበል ከትምህርት ቤቱ ካውንስለር ጋር የሚነጋገሩበት ተከታታይ የስብሰባ ጊዜ በመወሰን፣ የልጅዎን ስኬት በስትራቴጂና እቅድ ለመምራት የሚያስችል በቂ ጊዜና መደበኛ ተግባቦት ይኑርዎት።*
3. *የልጅዎን ትምህርት አቀባበል እርምጃ ይከታተሉ። የቤት ስራ ተሰርቶና ትጠናቶ በሰዓቱ ገቢ ተደርጓልን? በዓበይት የትምህርት ዓይነቶች ተጨማሪ ድጋፍ ወይም አስጠኚ ያስፈልጋልን? ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ ወይም ተጨማሪ የአማካሪ አገልግሎት ያስፈልጋልን?*
4. *ልጅዎ የወደቀበት/ችበት ኮርስ ካለ፣ ስለ ክሬዲት ማካካሻ የማታ ፕሮግራሞች፣ ኦንላይን ክሬዲት ማካካሻዎችና የክረምት ትምህርት አማራጮች ከልጅዎ ጋርና ከትምህርት ቤቱ ካውንስለር ጋር በመነጋገር የወደቀበትን/ችበትን ኮርስ ማካካስ ስለሚቻልበት መንገድ መወያየት እንዳለብዎት አይዘንጉ።*
5. *የወላጅ ናቪያንስ ፖርተፎሊዮ ይፍጠሩ http://dcps.dc.gov/service/college-planning.። ይህም ልጅዎን በተሻለ መንገድ ምርዳት እንዲችሉ የበለጠ መረጃ ይሰጦታል።*
6. *ስለ ረጅም ጊዜ ግባቸው ከልጆችዎ ጋር ይነጋገሩ። ከልጆችዎ ፍላጎቶች ጋር የሚሄዱት የትኞቹ ኮርሶች ናቸው? ልጅዎ በየትኞቹ ኮሌጆች ገብቶ/ታ መማር ይፈልጋል/ትፈልጋለች፤ የትኞቹን የኮሌጅ ምዝገባ መስፈርቶችስ ያሟላል/ታሟላለች? ስለሚፈልገው/ ስለምትፈልገው የስራ መስክ አስቀድሞ ተግባራዊ ልምድ ለማግኘት በየትኛው መስሪያ ቤት የስራ ልምምድ (ኢንተርንሺፕ) ማድረግ ይችላል/ትችላለች?*

## ምዘናዎች

ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚችሉ እናምናለን። የDCPS የተማሪ ተሳትፎን፣ የኮርስ ስራንና ፖርተሊዮዎችን ጨምሮ የተማሪዎችን እርምጃ የሚመዝንባቸው በርካታ መንገዶች አሉት። ደረጃቸውን የጠበቁ መዘናዎች ሁሉም ተማሪዎች የበለጸገ ትምህርት ማግኘት የሚችሉበት እኩል እድል እንዳላቸው ለማረጋገጥ እንድንችል ስለ ሁሉም ክፍሎችና ትምህርት ቤቶች የጋራ የሆነ መርጃን ያቀብላሉ። ምዘናዎች፣ ተማሪዎች “ስለሚያውቋቸው ነገሮች ማሳየት” የሚችሉባቸው ኢጋጣሚዎች እንጂ፣ የሚያውቋቸ ነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ማሳያ አይደሉም።

የስቴቱ የትምህርት የበላይ አስተዳደር ጽህፈት ቤት (OSSE)፣ ሁሉም በDCPS እና ቻርተ ትምህርት ቤ/ቶች የሚማሩ የዲሲ ተማሪዎች ሁሉ የኮሌጅና ስራ ዝግጁነት አጋርነት ምዘናዎችን (PARCC) እንዲወስዱ ያስገድዳል። ከ3-8ኛ ክፍል ያሉ ወይም አልጄብራ፣ ጂኦሜትሪ፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤ/ት እንግሊዝኛ 1 እና 2 ን የሚወስዱ ተማሪዎችም የ PARCC ፈተና ይወስዳሉ። በተጨማሪ ሁሉም የዲሲ ተማሪዎች፣ የዲሲን የሳይንስና ባዮሎጂ ፈተና በ 5ኛ እና 8ኛ ክፍሎች እንዲወስዱ OSSE ያስገድዳል; እነዚህ ሁለቱም ምዘናዎች በሁሉም የDCPS ኦንላይን ይሰጣሉ። በመጨረሻም፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ትምህርት የደረሱበትን እድገት ለመመዘን በየዓመቱ የ ACCESS ፈተና እንዲወስዱ የፌደራል ህግ ያስገድዳል።

ከፍተኛ የአእምሯዊ ዝግመት ላለባቸው ተማሪዎች አማራጭ ምዘናዎች አሉ። ተጨማሪ መረጃ ከግለ-ሁኔታ-ተጣጣሚ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ሂደት ማግኘት ይቻላል።

የDCPS ሁሉንም ተማሪዎች ለኮሊጅ ለማመልከት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጡ ምዘናውችን በነጻ ይሰጣል፡- የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የ SAT እና PSAT ፈተናዎችን በትምህርት ቀን በነጻ ይወስዳሉ (በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ሳይሆን)፤እንዲሁም ለከፍተኛ ምድብ ኮርሶች የተመዘገቡ ተማሪዎች የኤፒ ፈተና በነጻ ሊወስዱ ይችላሉ።

በተጨማሪም መምህራን የተማሪዎቻቸውን የትምህርት እርምጃ በየጊዜው ማከታተልና የትምህርት አሰጣጣቸውን ከእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና ችሎታ ጋር የተጣጣም ማድረግ እንዲችሉ ለማድረግ፣ የDCPS በርካታ ኢ-መደበኛ ምዘናዎችን ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ይሰጣል። እነዚህ ምዘናዎች ለተማሪና መምህራን ጊዜ ጠቃሚ መሆናቸውንና ስለ ተማሪዎች የትምህርት እርምጃ አስፈላጊ መረጃ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው ይከለሳሉ። ስለ ምዘናዎች ተጨማሪ መረጃ ከሚከተለው ማግኘት ይቻላል፤ http://dcps.dc.gov/page/student-assessment ወይም የበለጠ ለመረዳት የልጅዎን መምህር ማነጋገር ይችላሉ።

ምክር ለወላጆች

*የልጅዎን ፈተና አወሳሰድ ቀላል ለማድረግ ከሚችሉባቸው መንገዶች ጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው፡-*

1. *በፈተና ቀናት ልጅዎ በቂ እረፍት ማግኘቱን/ቷን እና ጤናማ ቁርስ መመገቡን/ቧን ያረጋግጡ።*
2. *ልጅዎ የቤት ስራዎቹን/ቿን እና አስይመንቶቹን/ቿን በትክክል እየሰራ/ች እንደነበረ ያረጋግጡ። ስጋት ካለብዎት፣ ከልጅዎና ከመምህሩ/ራሉ ጋር ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ስለሚቻልበት መንገድ ይነጋገሩ።*
3. *ልጅዎ ለፈተናው እንዲያጠና/እንድታጠና ይርዱት/ዷት። ልጅዎ አስፈላጊ የሆኑ ስፔሊንግና ቃላት፣ የሂሳብ መረጃ መጮችና የየምእሩፉን ትምህርት ማጥኛ መመሪያዎች እንዲያገኝ/እንድታገኝ ከልጅዎ መምህር ጋር ይነጋገሩ።*
4. *የፈተናውን ውጤቶች ከልጅዎ ጋር ይገምግሙ። ለተሻሉ ውጤቶች ማበረታቻ ይስጡ። ልጅዎ ከስህተቶቹ/ቿ እንድትማርና መረዳት እንዲችል/እንድትችል ለመርዳት ስለተሳሳቱ መልሶች ይነጋገሩ።*
5. *ከልጅዎ ጋር ስለ "እድገት" ወሳኝነት ይነጋገሩ። ማንም ሰው ከጅምሩ አንስቶ ፍጹም መሆን አይችልም። ዋናውና ጠቃሚው ነገር በጊዜ ሂደት ውስጥ በርትቶ በመስራት የምናገኘው እድገት (ለውጥ) ነው።*

## የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መመሪያ ማሻሻያ(ESEA) ለውጥ

የ2001 የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተና ደረጃ ትምህርት መመሪያ ማሻሻያ፣ ወይም አብዛኛውን ጊዜ በሚታወቅበት መጠሪያው፣ "ማንም ልጅ ወደ ኋላ አይቀርም" ("No Child Left Behind" (NCLB) የሚባለው፣ የትምህርት ቤቶችን አሰራር በተመለከት በርካታ ለውጦችን አምጥቷል። NCLB በዲሲ የትምህርት የበላይ አስተዳደር ጽህፈት ቤት (OSSE) የሚመራ ሲሆን፣ አሁንም በስራ ላይ መዋሉን ቀጥሏል።

በጁላይ 2012 OSSE ለዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት በማመልከት፣ ዲሲ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን ትምህርት ቤቶች የበለጠ መርዳት የሚችልበት ሌሎች መመሪያዎችን ያለመከተልና ከፌዴራል የሚያገኛቸውን ፈንዶችም ለዚሁ ተግባር የማዋል ፈቃድ ያገኘ ሲሆን፣ ይህንንም ሲያደርግ ዝቅተኛ ገቢና ከፍተኛ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ተፈላጊውን አገልግሎት እየሰጠ ነው። በዚህ የማሻሻያ ፈቃድ፡-

- ተጠያቂነት ስርዓቱ ተለውጧል። አዲሱ አቀራረብ፣ ትምህርት ቤቶች ስለ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበልና እድገት በመደበኛ ምዘና ላይ የተመሰረተ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው አድርጓል።
- ከዚህ የትምህርት ዓመት ጀምሮ፣ ከ3-8ኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች፣ እንዲሁም በተለይ ለተዘጋጁ ኮርሶች የተመዘገቡ ተማሪዎች የኮሌጅና ስራ ዝግጁነት አጋርነት ምዘናዎችን (PARCC) ይወስዳሉ። የ PARCC ምዘናዎች፣ የዲሲን CAS የንባብና ሂሳብ ፈተናዎች ይተካሉ።
- ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርታቸው የላቀ ውጤትና እድገት ማስመዝገብ በቻሉና ባልቻሉ ተማሪዎቻቸው ተመጣጣኝነት ላይ የሚመሰረት ተጠያቂነት ይኖራቸዋል። በዚህ የተጠያቂነት መለኪያ መሰረት ትምህርት ቤቶች በሚከተሉት አምስት ክፍሎች ይመደባሉ፡-
    - *ቅድሚያ የሚሰጣቸው* (ዝቅተኛ የትምህርት አፈጻጸም ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት ከፍተኛ ድጋፍ የሚሹ ትምህርት ቤቶች)፤
    - *ትኩረት የሚሹ* (ያለባቸውን ከፍተኛ የውጤት ልዩነት ወይም ክፍተት ለመሙላት ታላሚ ድጋፍ የሚሹ ትምህርት ቤቶች)፤
    - *ታዳጊ* (መካከለኛ የትምህርት አፈጻጸም ያላቸውና እድገታቸውን ለመቀጠል ድጋፍ የሚሹ)፤
    - *በመሻሻል ላይ ያሉ* (ከፍተኛ የትምህርት አፈጻጸም ያላቸውና እድገታቸውን ለመቀጠል ድጋፍ የሚሹ)፤ እና
    - *ተሸላሚ* (እጅግ ከፍተኛ ደረጃ የተማሪዎች የትምህርት አፈጻጸምና እድገት ያላቸው ትምህርት ቤቶች)።
- በአሁኑ ወቅት ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች እንዴት ያለ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው (እገዛና ማካካሻ የሚያስፈልጋቸውን ጨምሮ) መወሰንን በተመለከተ የበለጠ ነጻነት አላቸው።

## ደረጃ 1 ትምህርት ቤቶች

የነጻና በዝቅተኛ ዋጋ የምግብ አገለግሎት በሚሰጣቸው ተማሪዎች ቁጥር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ፈንድ የሚያገኝ ትምህርት ቤት፣ ደረጃ 1 ትምህርት ቤት (Title I school) በመባል ይታወቃል። ደረጃ 1 ፈንዶች፣ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊውን መሻሻል ማድረግ እንዲችሉና ተማሪዎች፣ የቤተሰቦቻቸውን የገቢ መጠን ከቁብ ሳይገባ፣ ጥራት ያለው ትምህርትና አካዳሚያዊ ስኬትን መጎናጸፍ እንዲችሉ ለመረዳት የሚዉሉ ናቸው።

ትምህርት ቤትዎ ደረጃ 1 መሆን አለመሆኑን ለማወቅ በ dcps.dc.gov/DCPS/TitleI ላይ የመልከቱ።

በደረጃ 1 ትምህርት ቤቶች ወላጆች የሚከተሉት መብት ይኖራቸዋል፡-

- የቤተሰብ-ትምህርት ቤት ጥምረት ይጠበቃል።
- ልጆችዎን ስለሚያስተምሩ የትምህርት ቤቱ መምህራንና ረዳት-ባለሙያዎች የሙያ ጥራት ጠይቀው ይረዱ። ወላጆች ከፍተኛ ጥራትና የስልጠና ደረጃ ያላቸው ሰራተኞች መለኪያ መስፈርት ምን እንደሆነ ማረጋገጫ የመጠየቅ መብት አላቸው። ይህን መረጃ በስልክ ቁጥር 202-442-4090 በመደወል የከፍተኛ ጥራት መምህር ክፍልን መጠይቅ ይቻላል።
- ስለ ልጅዎ መረጃ ልህዝብ የሚለቀቅ ከሆነ ሊነገርዎት ይገባል።
- ስለ ጎዳና-ተዳዳሪ ህጻናት መብቶች ሊነገርዎት ይገባል።
- ስለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መብቶች ሊነገርዎት ይገባል።
- ትምህርት ቤቱ ስለሚሰጠው የደረጃ 1 ፕሮግራሞች ማወቅ ይገባዎታል።
- ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ የተፈጸመ ሃይለኛ ወንጀል ሰለባ ከሆነ/ች ስለ ደህንነት-አልባ ምርጫ አማራጮች ማወቅ ይገባዎታል።
- ስለ ቅሬታ አፈታት ሂደቱ ማወቅ ይገባዎታል።
- ስለ ቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲው ማወቅ ይገባዎታል።

ስለ ደረጃ 1 ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በስልክ ቁጥር 202-442-6025

# የተማሪ ድጋፍ ፕሮግራሞች



# የተማሪ ድጋፍ ፕሮግራሞች

የDCPS እያንዳንዱ ተማሪ ሙሉ አቅሙን/ሟን እውን ማድረግ መቻሉን/ሏን የማየት ቁረጠኝነት አለው። ግባችን ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽና አቅምን የሚፈታተን፣ ደህንነትንና ማካባበርን የተላበሰ የትምህርት አካባቢን መስጠት ነው። የDCPS ከአጋዥ ደጋፊ ፕሮግራሞች ጋር ይህን ግብ እውን ለማድረግ ይጥራል።

- 500 ለ 500፡- በንባብ ፕሮግራም አማካኝነት የሚሰጥ ማስጠናት
- አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
- የከልኤ-ቋንቋ/እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች
- ነፍሰጡርና ልጅ ያላቸው ተማሪዎች
- የችግረኛ ህጻናት ፈንድ/ወደ ስኬት መሸጋገሪያ ድልድይ
- ቤትአልባ ወጣቶች
- ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ክልኤ-ጾታ፣ ቅዩር-ጾታና የተማሪ ድጋፍ ጥየቃ
- ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች እና የሰው-ሀይልና ገቢ ምንጮች
- የተማሪዎች ምደባ
- የክረምት ትምህርት

## 500 ለ 500፡- በንባብ አማካኝነት ማስጠናት

የ 500 ለ 500 ማስጠናት ፕሮግራም፣ የወረዳው ጥቁር ወንዶችን አቅም የማጎልበት ተነሳሽነት (EMOC) ቁልፍ አካል ሲሆን፣ ቁርጠኝነት ያላቸውን ጎልማሶች ከተማሪዎች ጋር በማጎዳኘት የማስጠናትና ተከታታይ አካዳሚያዊ ድጋፍ እንዲሰጧቸው የሚያደርግ ነው። ተቀዳሚው ግባችን፣ የጥቁርና ላቲኖ ወንዶች ልጆችን የንባብ ችሎታ ደረጃ ማሻሻል ሲሆን፣ ለአከዳሚያዊና ህይወት ስኬታቸውም አስፈላጊ የሆነውን በራስ የመተማመን መሰረትም መጣል ነው። ምርምር-ምስርት አቀራረባችን ቁርጠኝነት ያላቸውን የማህበረሰብ አባላት በተለይ በንባብ ላይ ያተኮረ የማስጠናት አገለግሎት እንዲሰጡ የሚያደርግ ሲሆን፣ ይህም ፕሮግራም በሁሉም የክፍል ደረጃ (ከመዋእለ-ህጻናት - 12ኛ) ላይ ያሉ ተማሪዎችን የማስጠናት አገልግሎት ይደግፋል። ፕሮግራሙ በተመረጡ ትምህርት ቤቶ ውስጥ ይሰጣል። ስለ ማስጠናት ለማወቅ ወይም አስጠኚ ለመሆን ለመፈረም፣ እባክዎ www.emocdc.org ይመልከቱ።

## የክረምት ትምህርት

የDCPS በርካታ የተለያየ ዓይነት ትምህርት-ቤት-ምስርት የክረምት ትምህርት እድሎችን ይሰጣል።

- የክረምት ትምህርት በዋና ዋና የትምህርት ዓይነቶች፣ እንግሊዝኛ፣ ሂሳብና ሳይንስን በመሳሰሉት፣ የክሬዲት ማካካሻ ለሚያስፈልጋቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚሰጥ ነው። ከ9-11ኛ ክፍል ላሉ ክሬዲት ማሻሻያ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በፈንድ መኖር ላይ ተመስርቶ መቀመጫዎች ክፍት ይሆናሉ።
- አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተስፈንጣሪ ተማሪዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስርዓተ-ትምህርት ለማዘጋጀት በክረምት ትምህርት ፕሮግራም እንዲሳተፉ ይጠይቃሉ።
- ከመዋእለ-ህጻናት-8 ክፍል ላሉ ተማሪዎችም የተወሰኑ የክረምት ፕሮግራሞች አሉ።

ስለ ክረምት ትምህርት ቤቶች አማራጮች ተጨማሪ መረጃ በየትምህርት ዓመቱ በተለይ በማርች ወር ማግኘት ይቻላል።

## የተማሪዎች ምደባ

የተማሪዎች ምደባ ጽህፈት ቤት የትምህርት ቤት ምደባ ድጋፍና መረጃ የሚሰጥ ሲሆን፣ ይህም ተማሪዎች ትምህርታቸውንና ግላዊ ህይወታቸውን በተመለከት ወደ ትክክለኛ ምርጫና ውሳኔና የሚመራ ነው። እነዚህ አገልግሎቶች ከ14-22 ዓመት እድሜ ላሉና የሚከተሉትን ለሆኑ ተማሪዎች ይሰጣሉ፡-

- የዲሲ አዳዲስ ነዋሪዎች፡-
- በተለያዩ የኑሮ ምክንያቶች ለረዥም ጊዜ ከትምህርት ተለይተው የሚመለሱ፤
- ከትምህርት ቤት አቋርጠው የመውጣት አዝማሚያ ያላቸው ወይም ያቋረጡ፤
- በተደጋጋሚ ወይም ያለ በቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት የመቅረት ጠባይ ጋር የሚታገሉ፤
- ከእስር ቤት ወይም ማረሚያ ፕሮግራም በሽግግር ላይ ያሉ፤
- ለምረቃ አስፈላጊ ከሆኑ ክሬዲቶች ወደ ኋላ የቀሩ፤
- በለጋ እድሜ ላይ የሚገኙ ወላጆች፤ ወይም
- በአሁኑ ትምህርት ቤታቸው ስኬት የራቃቸው።

የተማሪዎች ምደባ ጽህፈት ቤት አገልግሎቶች የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

- ተማሪዎችን በዲሲ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች የመመዝገብ ሂደት፣ እንዲሁም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ክሬድት ማካካሻና እነዚህን የመሳሰሉ የትምህርት ፕሮግራሞች ማግኘት እንዲችሉ መርዳት፤
- ተማሪዎችን ለአካዳሚያዊ እርምጃና ስኬት አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮችና አገልግሎቶች ጋር ማቆራኘት፤
- የተማሪዎችን የትምህርት ቤት ስኬት በመጀመሪያዎቹ ሶስት የምዝገባ ወራት በየሳምንቱ፣ ለቀሪው የትምህርት ዓመት ጊዜ ደግሞ በወር አንዴ መከታተል።

የትምህርት ቤት ምደባ እገዛ ለማግኘት ከማእከላዊ ጽህፈት ቤት ሰራተኛ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኛ፣ ከተማሪ፣ ከወላጅ ወይም የወላጅ ተወካይ (ማህበራዊ ሰራተኛ፣ የገደብ ወይም ይቅርታ ሰራተኛ፣ ተሟጋች፣ የፍርድ ቤት ሰራተኛ፣ ዘምድ) ወይም ማህበረሰብ-ምስርት ወይም የዲሲ አጀንሲዎች የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት ይቻላል። ለቀጠሮ እባክዎ 202-939-2004 ላይ ይደውሉ ወይም በኢሜል student.placement@dc.gov ይጠይቁ።

## አማራጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ሰባቱ አማራጭ ትምህርት ቤቶቻችን ከፍተኛ ችግር ያለባቸው ተማሪዎቻችንን እንኳን ሳይቀር ትምህርታቸውን እዲያጠናቅቁ ለመርዳት የተዘጋጁ ናቸው። አቅርቦቱ የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡- የተለመዱት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶች፣ ባለ ሰርቲፊኬት ዲፕሎማዎችና የቴክኒክ ሙያ ፕሮግራሞች። አማራጭ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- Ballou STAY Senior HS
- Choosing Higher Options for Individually Centered Education (CHOICE)
- Incarcerated Youth Program (IYP)
- Luke C. Moore Academy
- Roosevelt STAY HS
- Twilight Program
- Washington Metropolitan HS
- Youth Services Center.

ስለ አማራጭ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ መረጃ በ http://dcps.dc.gov/alternativehs ላይይገኛል።

## ባለሁለት ቋንቋ ትምህርት/እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች

በትምህርተቤትና/ወይም በቤታቸው ከእንግሊዝኛ ውጭ በሆነ ሌላ ቋንቋ የሚነጋገሩ ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤታቸው የእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ አገልግሎቶች ለማግኘት ይችሉ ይሆናል። ለነዚህ አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆንን ለመወሰን፣ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ችሎታ መመዘኛ ፈተና (IPT/WAPT) ከቋንቋ ለመዳ ክፍል (LAD) መውሰድ አለባቸው።

ከመጡበት ሃገር በ9ኛ ክፍልና ከዚያም በላይ የተማሯቸውን የትምህርት ዓይነቶችና ያገኟቸውን ነጥቦች የሚያሳዩ ወቅታዊና ህጋዊ ትራንስክሪፕት ወይም ሪፖርት ካርድ ማቀረብ የሚችሉ ተማሪዎች፣ የትምህርት ማስረጃዎቻቸውን በማስገምገም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲቶች ማግኘት ይችላሉ።

የመጀመሪያ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ መመዘኛ ፈተና ለመውሰድ ወይም ለውጭ ትራንስክሪፕት ግምገማ ቀጠሮ ለመያዝ፣ 202-671-0750 ላይ ይደውሉ።

## ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ክልኤ-ጾታ፣ ቅዩር-ጾታና የተማሪ ድጋፍ ጥየቃ

የDCPS የትምህርት ቤቶችን ደህንነት ለማረጋገጥና ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ክልኤ-ጾታ፣ ቅይር-ጾታና
ስለ ጾታዊ ማንነታቸው ገና እራሳቸውን በመጠየቅ ላይ ያሉ (LGBTQ) ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችና ቤተሰቦችን የሚያቅፉ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል። ትምህርት ቤቶችና ወላጆች ስለ LGBTQ ወጣቶች የሚኖራቸው አስተያየት፣ በአካላዊ ጤንነታቸው፣ አእምሯዊ ጤንነትና አካዳሚያዊ ሁኔታዎቻቸው፣ እንዲሁም በቀጣዩ ይወታቸው ውስጥ በሚያደርጓቸው ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።

የDCPS ሁሉን-አቀፍ ማህብረሰብ ለመፍጠር ካለው እቅድ አንድ አካል ከሆኑት የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- በእውን በሆነና ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ላይ የተመሰረተ ጾታዊ አዝማሚያን፣ ጾታዊ ማንነትን ወይም ገለጻን መሰረት የሚያደርግ አድሎንና ቡሊንግን መፍታት የሚያስችል ጸረ-ቡሊንግና አድሎ ፖሊሲዎችን ነድፏል፤
- LGBTQ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችንና ቤተሰቦችን መደገፍ የሚያስችል ፕሮግራም ተግባር ላይ በማዋል (ለምሳሌ፦ የጌይ-ቀጥተኞች ህብረት የድጋፍ ቡድን የመሳሰሉ)፣ ሁሉን-አቀፍና ተቀባይ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ መገንባት የሚቻልበትን መንገድ የሚያመቻቹ የትምህርት ቤት ሰራተኞችን አሰልጥኗል፤ እንዲሁም
- በትምህርት ቤት ስርዓተ-ትምህርትና በሌሎችም መሳሪያዎች ውስጥ LGBTQ አርእያዎችን ብዛት መጨመር።

የቅይር-ጾታና አፈንጋጭ-ጾታ መመሪያ ፖሊሲያችን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወላጆችና ተማሪዎች፣ የDCPS ቅይር-ጾታና አፈንጋጭ-ጾታ ተማሪዎችን ለመደገፍ የሚረዱ በስራ ላይ ያሉ ህግጋትን፣ ድንቦችንና ፖሊሲዎችን መተግበር እንዲችሉ በመሳሪያነት እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በእኩለንትና በክብር መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ይሰጣል። መሳሪያዎቻችን የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦ ትምህርት ቤቶች የፌዴራል/ወረዳ ግዴታዎችን በመወጣት ቅይር-ጾታ/አፈንጋጭ-ጾት ያላቸውን ተማሪዎች ከሌሎች በእኩልነት መያዝ እንዲችሉ የሚያዝ መመሪያ፤ጥያቄዎች ላሏቸው ቤተሰቦች፣ ተማሪዎችና የትምህርት ቤት ሰራተኞች የሚሰጡ ገለጻዎች፤ እንዲሁም ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ቤተሰቦችና ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ቅጾችች፣ መሳሪያዎችና መገልገያዎች። ለተጨማሪ መረጃ፣ ዌብሳይታችንን ይመልከቱ፦ http://dcps.dc.gov/health.




## ነፍሰጡርና ልጅ ያላቸው ተማሪዎች

የነፍሰ-ጡርና ባለ-ልጅ ተማሪዎች አዲስ ከፍታዎች ፕሮግራም (New Heights) ለDCPS ነፍሰ-ጡርና ባለ-ልጅ ተማሪዎች (ወንድ ወይም ሴት) ልጅ የማሳደግ ሃላፊነት ለመወጣትና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ አስፈላጊውን እርዳታ፣ ድጋፍና መመሪያ ይሰጣል። ፕሮግራሙ የተማሪዎችን የትምህርት ቤት ተሳትፎ ለማስቀጠል፣ የምረቃ ደረጃቸውን ለማሻሻል፣ ለኮሌጅና ለስራ ለማዘጋጀት፣ እንዲሁም ቀጣይ እርግዝናዎችን ለመከላከል የጥራል።

አዲስ ከፍታዎች የሚከተሉትን ይሰጣል፦

- ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር በሳይት የእርግዝና ክትትል ድጋፍ፣ እና የህጻናት ክብካቤ ቫውቸር፣ WIC፣ ቤት፣ TANF፣ የስራ ቅጥር፣ የስራ ስልጠና እድሎችና የኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ምዝገባ ደጋፍ፤
- የቅድመ-ወሊድ ክብካቤ፣ ልጅ አስተዳደግ፣ የህይወት ክሂሎት፣ የገንዘብ አያያዝ፣ የስራ እቅድ አስተቃቀድ፣ ጤናማ ግንኙነቶችና ሌሎችም ርእሰ ጉዳዮችን ጨምሮ (ሆኖም በነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን) ትምህርታዊ ዎርክሾፖች ማዘጋጀት፤
- ተሳታፊዎች አንዳንድ ነገሮችን፣ ለምሳሌ፦ ዳይፐር፣ ልብሶች፣ መጫወቻዎች፣ መሳሪያዎች፣ ቁሳቁስ፣ ወዘተ. ለልጆቻቸው በነጻ የሚያገኙበት የበማበረታቻ ፕሮግራም፤ እና
- በቂ ሆነው ከተገኙ፣ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ለመጓጓዣ የሚያገለግሉ የገንዘብ ኩፖኖች ያገኛሉ።

ለነፍሰ-ጡርና ባለ-ልጅ ተማሪዎች ስለሚደረጉ ድጋፎች የበለጥ:መረጃ:ለማግኘት፣ የDCPS ዌብሳይትን http://dcps.dc.gov/page/health-and-wellness ይመልከቱ።

## የችግረኛ ህጻናት ፈንድ/ወደ ስኬት መሸጋገሪያ ድልድይ

ችግረኛ ህጻናት በጎ-አድራጊ ድርጅት ሲሆን፣ አሁን ለድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ነገሮችን በመስጠት የተማሪዎቹ መሰረታዊ ፍላጎቶ ሳይሟሉ እንዳይቀሩ ለማረግ ከሚረዳው የህጻናትና ቤተሰቦች ብሔራዊ ማእከል ጋር የሚተባበር ነው። የድርጅቱ ተልእኮ ተማሪዎቹ ተቀዳሚ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት እንዲችሉ በመርዳት በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲቀጥሉና ሙሉ ችሎታቸውን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ መርዳት ነው። በአሁን ጊዜ፣ የDCPS ሰራተኞች ዩኒፎርሞች፣ ጫማዎች፣ ግሮሰሪዎች፣ የግል መጠቀሚያ ነገሮችና መድሃኒቶች በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ለሚሟላት መርዳት ይችላሉ። በዚህ ፕሮግራም ስለሚሰጡ ድጋፎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የልጅዎን ትምህርት ቤት ካውንስለር ወይም መምህር ያነጋግሩ።

## ቤትአልባ ወጣቶች

ከፌደራሉ የማኪኔይ ቬንቶ መመሪያዎች ጋር በሰመሩ መልኩ፣ የDCPS፣ የተወሰነ፣ መደበኛና/ወይም በቂ የሌሊት የመኝታ ቦታ ለሌላቸው የጎዳና ተዳዳሪ ህጻናትና ወጣቶች ፈጣን ምዝገባ ይሰጣል።

ቤት-አጥ ልጆች፣ ለትምህርት ቤት ምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ዋነኛ ማስረጃዎች፣ ለምሳሌ የልደት ሰርቲፊኬት፣ የትምህርት ቤት ወይም የጤና ሪከርዶች፣ ወይም የኗሪነት ማረጋገጫ የሌላቸው እንኳን ቢሆኑ ይመዘጋባሉ። ተማሪዎች በተፈናቀሉበት ወቅት ሲማሩበት በነበረበት የቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ወይም አሁን በሚገኙበት ጊዜያዊ መኖሪያ አካባቢ ባል ትምህርት ቤት የመቆየት መብት አላቸው።

የተማሪዎቹን ጥቅም በተሻል መንገድ መጠበቅ የሚያስችል መሆኑ ከታመነበት፣ በሌላ ትምህርት ቤትም ሊመዘገቡ ይችላሉ። ተማሪዎችና በለጋ እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች፣ ከትምህርት ቤታቸው የመጓጓዣ አገለግሎትን ጨምሮ (የሜትሮ መሳፈሪያ ፓስ ወይም ኩፖኖች) ሌሎች ተጨማሪ ትምህርታዊ ድጋፎችንም፣ ዩኒፎርሞችና የትምህርት ቤት መሳሪያዎችን በድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

ለቤት-አጥ ወጣቶች ስለሚደረጉ ድጋፎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የትምህርት ቤትዎን ትምህርት ቤት-ምስርት ቤት-አጦች ተወካይ ወይም ካውንስለር ያነጋግሩ።

# የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞችና ልዩ ልዩ ምንጮች

የመማርና ማስተማር ጽህፈት ቤት (OTL) ተጨማሪ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የላቀ ጥራት ያለው ትምህርትና አገልግሎቶችን በተቻለ መጠን ለቤታቸው ቅርብ በሆኑ ቦታዎችና በየጊዜውና ተከታታይነት ባለው መንገድ ይሰጣል። አገልግሎቶቹ የተማሪውን ስኬት፣ ተሳታፊነትና እራስን-መቻል ለማሳደግ የተዘጋጁ ናቸው።

የአካል-ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት መመሪያ (IDEA) በሚያዘው መሰረት፣ የልዩ ትምህርት ድጋፍ የሚደረግላቸውን ልጆችና ቤተሰቦች ደህንነት ለመጠበቅ፣ የደህንነት መጠበቂያ ሂደቶች አሉ። የዲሲ የደህንነት መጠበቂያ ሂደቶች ሰነድ ቅጂ በ http://osse.dc.gov/service/specialized-education ላይ ይገኛል።

ልጅዎ የአካል ጉዳት እንዳለበት/ባት የሚጠራጠሩ ከሆን፣ ለተጨማሪ ድጋፍ የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## የሙሉ-ጊዜ ፕሮግራሞች

የDCPS የሙሉ-ጊዜ ወረዳ-አቀፍ ክፍሎች፣ በግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራማቸው እቅድ (IEP) ውስጥ መውሰድ ከሚገባቸው አጠቃላይ ትምህርት ውጭ 20 ወይም ከዚያም በላይ ሰዓታት ልዩ ትምህርት ለሚወስዱ ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ይሰጣሉ። ክፍሎቹ ሊሟሉላቸው የሚገቡ ከፍተኛ ፍላጎቶች ላሏቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የበለጠ ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው።

### የባህርይና ትምህርት ድጋፍ (BES)ፕሮግራም

የባህርይና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ክፍሎች፣ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ተጽእኖ የሚያደርስ ህሊናዊ (አእምሯዊ) ጉዳት ወይም አስቸጋሪ ባህርይ እንዳለባቸው ተለይተው ለታወቁ ተማሪዎች የተዘጋጁ የሙሉ-ጊዜ ክፍሎች ናቸው። እያንዳንዱ ክፍል፣ በእያንዳንዱ ተማሪ ግቦች ላይ ያተኮረ ድጋፍ ለመስጠት በሰለጥነ/ች ሰራትኛ የሚታገዝ ደህንነትን የተላበሰና የተደራጀ የመማሪያ አካባቢ ይኖረዋል።

ስለ ባህርይና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በ osi.behavior@dc.gov ይጠይቁ።

### የተግባቦትና ትምህርት ድጋፍ (CES) ፕሮግራም

#### ቀደም ሲል የኦቲዝም ድጋፍ ፕሮግራም በመባል ይታወቃል

የተግባቦትና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ክፍሎች፣ የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር ወይም ሌላ የትምህርት አቀባበል ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚሰጡ የሙሉ-ጊዜ ክፍሎች ናቸው። የነዚህ የሙሉ-ጊዜ ክፍሎች መምህራንና ሰራተኞች፣ ተማሪዎቻቸው እራሳቸውን ችለው የመኖር ክሂሎት ማዳበር ይችሉ ዘንድ ለመርዳት የሚያስፈልጓቸውን አካዳሚያዊ፣ ባህርያዊና ማህበረ-ህሊናዊ ፍላጎቶች በሚሟላት ይደግፋሉ። ስለ ተግባቦትና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በ osi.autism@dc.gov ላይ ይጠይቁ።

### የቀዳሚ ትምህርት ድጋፍ (ELS) ፕሮግራም

የቀዳሚ ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ከመዋእለ-ህጻናት 3-2ኛ ክፍል (PK3-2) ላሉ ተማሪዎች የሙሉ-ጊዜ ቀዳሚ እገዛ ይሰጣል። እያንዳንዱ ክፍል፣ የተማሪውን ግቦች ለማስገኘት በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እርዳታና የተደራጀ ትምህርት ይሰጣል። ስለ ቀዳሚ ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ ነረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.els@dc.gov. ይጠይቁ።

### የእራስ-መቻልና ትምህርት ድጋፍ (ILS) ፕሮግራም

#### ቀደም ሲል የአእምሯዊ ጉዳት ፕሮግራም በመባል የሚታወቅ

የእራስ-መቻልና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራሞች፣ አእምሯዊ ዝግመት ወይም ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጁ የሙሉ-ጊዜ ክፍሎች ናቸው። እያንድዳንዱ ፕሮግራም ተማሪዎቹን ለስራ ቅጥርና ለዘለቄታዊ እራስን-መቻል ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የማንበብና-መጻፍና የህይወት ክሂሎትን ያስተምራል። ስለ እራስን-መቻልና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.lowincidence@dc.gov ይጠይቁ።

### የህክምናና ትምህርት ድጋፍ (MES)ፕሮግራሞች

የህክምናና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራሞች፣ ውስብስብ የጤና ችግሮችና አእምሯዊ ዝግመት ላለባቸው ተማሪዎች የተዘጋጁ የሙሉ-ጊዜ ክፍሎች ናቸው። እያንዳንዱ ክፍል በአምስቱ ህዋሳት ልምዶች ላይ ያተኮሩና በተዘማጅ ግልጋሎት ቅንጅት ላይ ያተኮሩ ድህንነትን የተላበሰና የተደራጀ የትምህርት አካባቢ ይሰጣል። ስለ ህክምናና ትምህርት ድጋፍ ፕሮግራሞች ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.sls@dc.gov ይጠይቁ።

### የስሜት ህዋሳት ድጋፍ ፕሮግራሞች

የስሜት ህዋሳት ድጋፍ ፕሮግራሞች፣ መስማት የተሳናቸው/የመስማት ችግር ያለባቸው፣ ወይም ዓይነ-ስውር/የማየት ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን የሚያገለግሉ ናቸው። የእነዚህ ፕሮግራሞች ዓላማ፣ ተማሪዎች ምንም የአካል ጉዳት ከሌለባቸው አቻዎቻቸው ጋር ስኬታማ በሆነ መንገድ መማርና እራሳቸውን ችለው መኖር እንዲችሉ አስፈላጊ የሆኑ ክሂሎትን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው። ስለ ስሜት ህዋሳት ድጋፍ ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.sls@dc.gov ይጠይቁ።

### የተወሰነ የመማር ድጋፍ (SLS) ፕሮግራም

#### ቀደም ሲል የተወሰነ የመማር አለመቻል ፕሮግራም ይባላል

የተወሰነ የመማር ድጋፍ ፕሮግራም፣ በትምህርት አቀባበል ላይ የተወሰነ ችግር ወይም የአእምሮ ዝግመት ላለባቸው ከ3-12 ክፍሎች ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። እያንዳንዱ ክፍል በእያንዳንዱ ተማሪ ሁኔታ ላይ ያተኮረ፣ ደህንነትን የተላበሰና የተደራጀ የመማሪያ አካባቢን ይሰጣል። ስለ የተወሰነ የመማር ድጋፍ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.sls@dc.gov ይጠይቁ።

## ሁሉን-አቀፍ ሞዴሎች

ሁሉን-አቀፍ የመማሪያ ክፍል ወይም ቦታ ዓይነት ሳይሆን፣ አካል-ጉዳተኛ ተማሪዎችን በጠቅላላው የትምህርት መቼቶች (ስፍራዎች) የማካተት ፍልስፍና ነው። የሁሉን-አቀፍ ዓላማ ለተማሪዎች በየክፍል ደረጃው ከሚጠበቀው የትምህርት ሁኔታ ጋር የተመጣጠነ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርትና በሁሉም መስኮች ስኬታማ መሆን የሚችሉበት እድል መስጠት ነው። ይህ ሊሆን የሚችልበት አንድ ዋነኛ መንገድ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ፍላጎት በመደበኛው ክፍል ትምህርት መሟላት እንዲችል ሲደረግ ነው።

### ትብብረ-ማስተማር

ትብብረ-ማስተማር ሁለት ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ጎልማሶች የክፍሉን ተማሪዎች በሙሉ ወይም የተወሰኑትን የማስተማር ሃላፊነት ሲጋሩ የሚፈጠር ነው። ይህ ተግባር ሁሉም ተማሪዎች ከሁለት አስተማሪዎች በተቀናጀ መንገድ የሚሰጥ የትምህርት ይዘት መማር እንዲችሉ እድል የሚሰጥ ነው።

### የመማሪያ ቤተ-መከራዎች (ቀደም ሲል የትምህርት መሳሪያዎች ክፍሎች የሚባሉት)

የመማሪያ ቤተ-መከራ ከመደበኛው የመማሪያ ክፍል የተለየ ሲሆን፣ የአካል-ጉዳቶች ያሉባቸው ተማሪዎች በቀጥታ ልዩ ትምህርትና አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያገኙበት ክፍል ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህ ዓይነቱ ድጋፍ "የትምህርት መርጃዎች ክፍል" ወይም "አገልግሎቶች መውሰድ" በመባልም ይታወቃል። በዚህ ሁኔታ የሚማሩ ተማሪዎች ገሚሱን ጊዜያቸውን በመማሪያ ቤተ-መከራ፣ ገሚሱን ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች እንዲመቹ ለውጥ በተደረገባቸው/ወይም አስፈላጊ መቀመጫዎችና ሌሎችም መሳሪያዎች በተጨመሩላቸው መደበኛ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ይማራሉ። ስለ ትብብረ-ማስተማርና የመማሪያ ቤተ-መከራዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.sit@dc.gov ይጠይቁ።

## ተጨማሪ የልዩ ትምህርት መርጃዎችና ፕሮግራሞች

### ሴክሽን 504 ፕሮግራም

ከልዩ ትምህርት ፕሮግራም በተለየ መልኩ፣ ሴክሽን 504 የተለየ የመማሪያ አቀራረብ ለሚገባቸው ተማሪዎች አያዝም። ከዚያ ይልቅ፣ ሴክሽን 504 አካል-ጉዳተኝነት ያለባቸው ተማሪዎች፣ በDCPS ትምህርት ቤታቸው የመደበኛውን ትምህርት ስርዓተ-ትምህርትና ሌሎችም የመማሪያ አጋጣሚዎች ለማግኘት የሚያስፈልጓቸውን መሳሪያዎችና አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። ስለ ሴክሽን 504 ፕሮግራም፣ እባክዎበኢሜይል 504@dc.gov ይጠይቁ።

### አጋዥ ቴክኖሎጂ (AT)

አጋዥ ቴክኖሎጂ በግለሰብ ሁኔታ ተጣጣሚ ትምህርት ቡድን (IEP) ፣ የትምህርት ቤቱን ስርዓተ-ትምህርት ወይም የትምህርት መቼት ለአካል-ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ይረዳሉ ተብለው የሚታወቁ ቴክኖሎጂዎች ሁሉ የጥቅል መጠሪያ ነው። አጋዥ ቴክኖሎጂ፣ የእርሳስ መያዣዎችንና ዝርግ ቦርዶችን ከመሳሰሉ ዝቅተኛ-ደረጃ-ቴክ መፍቲሄዎች እስከ ላፕቶፕና ሶፍትዌሮች የሚደርሱ ከፍተኛ-ደረጃ-ቴክን ያካትታል። ስለ አጋዥ ቴክኖሎጂ ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.at@dc.gov ይጠይቁ።

### ተራዛሚ የትምህርት ዓመት (ESY)

ተራዛሚ የትምህርት ዓመት፣ ለአካል-ጉዳተኛ ተማሪዎች IEP በሚያዘው መሰረት ከመደበኛው የትምህርት ዓመት ውጭ የሚሰጡ ልዩ ትምህርትና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚመለከት ነው። የDCPS ለተማሪዎቹ ጠቃሚ የሆኑ ክሂሎትን እንዳይረሱና በቀጣዩ አዲስ የትምህርት ዓመት (ፎል) ትምህርታቸውን ለመቀጠል ዝግጁ እንዲሆኑ ለመርዳት የሚያስችል የክርምት ፕሮግራም የሰጣል። የተራዛሚ ትምህርት ዓመት ፕሮግራም መስጫ ቦታዎች በየዓመቱ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ይኖራሉ። ስለ ተራዛሚ ትምህርት ዓመት ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.esy@dc.gov ይጠይቁ።

### የቤትና ሆስፒታል ትምህርት ፕሮግራም (HHIP)

HHIP በጤና የባህርይ ችግሮች ምክንያት ትምህርት ቤት መሄድ ለማይችሉ ከመዋእለ-ህጻናት 3-12 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ድጋፍ ይሰጣል። ስለ ቤትና ሆስፒታል ትምህርት ፕሮግራም ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በኢሜይል hip.dcps@dc.gov ይጠይቁ።

## የሽግግር ፕሮግራሞች

የDCPS የሽግግር ፕሮግራሞች ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እድሎች ለሚዘጋጁ ተማሪዎች የሚሰጡ መንገድ ከፋች አጋጣሚዎች ናቸው።

### የፍለጋ ፕሮጀክት

የፍለጋ ፕሮጀክት በትምህርት ቤት አንድ ቢሮ ተሰጥቶት የሚሰራ የሽግግር ፕሮግራም ሲሆን፣ ይኸውም እድሜያቸው ከ18-21 ዓመት የሆኑ የ IEP ማጠናቀቂያ ሰርቲፊኬት ለማግኘት እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች፣ የእውኑ-ህይወት ክሂሎት የሚማሩበት፣ የስራ ስልጠና የሚያገኙበትና በስራ ቅጥር ዝግጁነት ተግባራትውስጥ የሚሳተፉበት ነው። የፕሮግራሙ ግብ አእምሯዊ ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች በሚፈልጉት የስራ መስክ ስራ ለማግኘት እንዲችሉ መርዳት ነው። የፍለጋ ፕሮጀክት በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንትና ዩ.ኤስ. የጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት ውስጥ ይገኛል። ስለ ፍለጋ ፕሮጀክት ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በኢሜይል osi.transition@dc.gov ይጠይቁ።

### ተወዳዳሪ የስራ ቅጥር እድሎች (CEO) ፕሮግራም

የ CEO ፕሮግራም እድሜያቸው ከ 16-22 ዓመት የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ለማግኘት እየተማሩ ያሉ አካል-ጉዳተኛ ተማሪዎችን በተለያዩ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ከሚገኙ ፕሮፌሽናል አማካሪዎች ጋር የማያያዝ እድል ይሰጣል። የ CEO አማካሪዎች ተማሪዎች ስራ ለማግኘት በሚያደርጉት አሰሳ ሂደት ውስጥ የመምራት ድጋፍ ይሰጣሉ። ተማሪዎች ከአማካሪዎቻቸው ጋር ይሰራሉ፤ሳምንታዊ የፕሮፌሽናል እድገት ትምህርቶችን እየተከፈላቸው ይማራሉ፤ እንዲሁም በሙያ ላይ ያተኮሩ ፕሮጀክቶችን ያከናውናሉ። ተማሪዎች ፕሮግራሙን ሲያጠናቅቁ፣ አማካሪዎቻቸው በሚሰሩባቸው ድርጅቶች ውስጥ እየተከፈላቸው እንዲሰሩ የክረምት ስራ በማፈላለግና በማመልከት ይረዷቸዋል።

ስለ CEO ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ በ http://dcpsceo.com/ ላይ ይመልከቱ ወይም በኢሜይል osi.transition@dc.gov ይጠይቁ።

## ተዛማጅ አገልግሎቶች

### ባህርያዊና ስሜታዊ ድጋፎች

የአእምሮ ጤናና ባህርያዊ ድጋፍ አገልግሎቶች በማህበራዊ ሰራተኞች የሚሰጡ ሲሆን፣ እንዚህም አገልግሎቶች የቡድን ወይም የግል ካውንስሊንግን፣ የቤት ጉብኝትን፣ እና ማህበራዊ፣ ስሜታዊና ባህርያዊ ምዘናዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኞች ከመምህራን ጋር በመሆን የተማሪን ባህርይና የትምህርት አቀባበል ረዘም ላለ ጊዜ በማጥናት የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀባበልን ለማሳደግ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ ይሰራሉ። እነዚህ ማህበራዊ ሰራተኞች ተማሪዎችንና ቤተሰቦችን ከማህበረሰብ ግልጋሎት መንጮች ጋር በማያያዝ በትምህርት ቤት የሚሰጡ የባህርይ ድጋፍ አገለግሎቶችን ለማሳድግም ይሰራሉ።

### አካላዊ ድጋፎች፦ ስራ-ነክ ቴራፒና አካላዊ ቴራፒ (OTs)

ስራ-ነክና አካላዊ ቴራፒስቶች የተማሪዎችን እራስን-የመርዳት ክሂሎት፣ ከሌሎች ባህርይ ጋር መመሳሰልና ጨዋታ፣ እና ሌሎችንም የስሜት ህዋሳትና ሞተር ክሂሎት በማሳደግ፣ የእለት-ተእለት ስራ አከናወን ችሎታቸውን፣ ለምሳሌ፦ የተቀመጠ እቃ ላይ መድረስና መጨበጥ፣ ለማሻሻል ይሰራሉ። አካላዊ ቴራፒስቶች፣ ተማሪዎችን ከእንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ አዳጋች ተግባራትን፣ ለምሳሌ፦ ደረጃ መውጣት ወይም ከክፍል ወደ ክፍል መዘዋወር፣ ማከናወን እንዲችሉ ይረዳሉ። ተማሪዎቹ እነዚህ አካላዊ ችግሮች እንዳለባቸው በምርመራ ካረጋገጡ በኋላ፣ ቴራፒስቶች ድጋፍና አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን (ለመራመድ የሚረዱ መደገፊያዎች ወይም ምርኩዞች ያሉ) በመስጠት ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ መዘዋወር እንዲችሉ ይረዳሉ።

### ስነ-ልቦና

የስን-ልቦና ቡድን ለተማሪዎችና አስተማሪዎች ስነ-ልቦናዊና የእድገት መዘናዎችን በመስጠት፣ ስለ ተማሪዎች ባህርይና አእምሯዊ አሰራር በመተንተን፣ እንዲሁም እነዚህን የምርመራ ውጤቶችን ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞችና ወላጆች ጋር በማስተንተን ይረዳሉ። የትምህርት ቤት የስነ-ልቦና ባለሙያዎችም የትምህርት ቤቱ ሰራተኞችና ወላጆች የትምህርትና ባህርይ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ይረዳሉ።

### የንግግር-ቋንቋ አካላት ምርመራ

የንግግር-ቋንቋ አካላት ምርመራ ቡድን፣ የተማሪዎችን ከቋንቋና ተግባቦት ጋር የተያያዙ ችግሮችና ዝግመቶች ለይተው በመረዳት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ። ቡድኑ ተማሪዎች እነዚህ ችግሮች በአካዳሚያዊ ስኬታቸው ላይ ሊያደርሱ የሚችሏቸውን ተጽእኖዎች መቋቋም የሚያስችል ቴራፒ ይሰጧቸዋል። ስለ ተዛማጅ አገልግሎቶች ጥያቄ ካልዎት፣ እባክዎ በኢሜይል dcps.relatedservices@dc.gov ይጠይቁ።

## የመጀመሪያ ደረጃዎች

በአካል-ጉዳተኛ ግለሰቦች መመሪያ (IDEA) መሰረት፣ የትምህርት ቤት ወረዳ በወረዳው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ እድሚያቸው ከ3-5 ዓመት የሆኑ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ፍለጋ ልጅ በተባለ ሂደት አማካኝነት፣ ለይቶ፣ ያሉበትን ቦታ አውቆና ያለባቸውን ጉዳት መጠን ገምግሞ ማወቅ አለበት። የመጀምሪያ ደርጃዎች፣ በDCPS፣ እራስቸውን በቻልሉ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ በግል ወይም ሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች ወይም በህጻናት-ክብካቤ ማእከላት ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎችና ገና ትምህርት ቤት ካልገቡ ተማሪዎች ጋር ይሰራሉ። የመጀመሪያ ደረጃዎች የሲ ክፍል ሽግግርንም (Part C Transition) ይመራሉ። ይህም የመጀመሪያ እገዛ አገልግሎቶች የሚሰጣቸው ተማሪዎች የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችንም ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆናቸው የሚወሰንበት ሂደት ነው።

የመጀመሪያ ደረጃዎች ሁለት የምገማ ሳይቶች አሉት፡-

- Walker-Jones Education Campus, 1125 New Jersey Avenue, NW
- Department of Employment Services, 4058 Minnesota Avenue, NE.

ለተጨማሪ መረጃ፣ በኢሜይል referral@earlystagesdc.org ወይም info@earlystagesdc.org ይጠይቁ።

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች



# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ይህ ክፍል አንዳንድ አብዛኛውን ጊዜ በተደጋጋሚ ለሚጠየቁና በተቀዳሚው ይህዝብ ተሳትፎ ተግባቦት መስመራችን (ስልክ፣ ዌብሳይት፣ ኢሜይልና ህዝባዊ ስብሰባዎች) ለተቀበልናቸውን ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። እንዚህ ጥያቄዎች የተሟሉ አይደሉም፤ በመሆኑም በዚህ መጽሃፍ ውስጥ ያልተመለሱ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካልዎት፣ እባክዎ ለDCPS በስልክ ቁጥር 202-442-5885 በመደወል ወይም በኢሜይል OFPE.info@dc.gov ይጠይቁ።

- ምዝገባ
- የከአካባቢ-ውጭ-ትምህርት ቤት ሎተሪ
- የክፍል ተሳትፎ (Attendance)
- ልዩ ትምህርት
- ምዘናዎች
- የከትምህርት ቤት በፊትና በኋላ ፕሮግራሞች

## ምዝገባ

**ጥ፦** ስለ የDCPS ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችልበት የተሻለው መንገድ የትኛው ነው?

**መ፦** ስለ DCPS ማወቅ የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፦ 1) የDCPS ዌብሳይትን profiles.dcps.dc.gov; ይመልከቱ; 2) በየትምህርት ቤቱ ፕሮፋይል ገጾች ላይ የሚገኙትን የትምህርት ቤት ዌብሳይቶችን ይመልከቱ፤ ወይም 3) ትምህርት ቤቶችን ይጎብኙ።

**ጥ፦** የልጄን አካባቢ ትምህርት ቤት እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**መ፦** የልጅዎን አካባቢ ትምህርት ቤት ዌብሳይት በማየት http://1.usa.gov/1thQJAN ማወቅ ይችላሉ። በዌብሳይቱ “ለማወቅ አድራሻዎን ያስገቡ” በሚለው ውስጥ ተቀዳሚ አድራሻዎን ካስገቡ በኋላ “ፈልግ” የሚለውን ይጫኑ። ማስታወሻ፦ ተቀዳሚ አድራሻዎ በምዝገባ ሂደት ወቅት ትክክለኛነቱ ይጣራል።

**ጥ፦** ልጄን ለማስመዝገብ የዲሲ ነዋሪነቴን ለማረጋገጥ እንዴት እችላለሁ?

**መ፦** የት እንደሚኖሩ ማረጋገጥ፣ ወይም “ነዋሪነትን ማረጋገጥ” የሚባለው፣ የምዝገባው ሂደት አንድ ቁልፍ አካል ነው። በዲሲ ወረዳ ውስጥ ነጻ የህዝብ ትምርት ለማግኘት በቂ የሚሆኑት የዲሲ ነዋሪዎች ብቻ ናቸው። ይህን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸው ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ነዋሪነታቸውን እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ። አብዛኛውን ጊዜ፣ ወላጆች የዲሲ ነዋሪነታቸውን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን በምዝገባው ሂደት ለትምህርት ቤቱ ያቀርባሉ።

የነዋሪነት ማረጋገጫ ስለማቅረብ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ኦንላይን dcps.dc.gov/enroll የሚገኘውን ይምዝገባ ፓኬት ይቃኙ።

**ጥ፦** ልጄን ከትምህርት ዘመኑ መጨረሻ በፊት ትምህርት ቤት አላስመዘገብኩትም። በ DCPS አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ መማር ይችላል/ትችላለች?

**መ፦** ማንኛውም ልጅ በመኖሪያ አካባቢው ባለ ትምህርት ቤት የመማር መብት አለው/ላት። የልጅዎን አካባቢ ትምህርት ቤት ለማወቅ ኦንላይን http://1.usa.gov/1thQJAN ይመልከቱ። ልጅዎን ለማስመዝገብ ወደ ትምህርት ቤቱ መሄድ ይኖርቦታል። በዚያን ጊዜም የነዋሪነት ማረጋገጫዎን ማቅረብ አለቦት። ልጅውን ስለ ማስመዝገብ ተጨማሪ መረጅ ለማግኘት፣ እባክዎ የዚህን መጽሃፍ “በDCPS መመዝገብ” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ፤ ወይም በ dcps.dc.gov/enroll ላይ በማንበብ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።

**ጥ፦** [2]ልጄን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለማዛወር ሂደቱ ምንድን ነው?

**መ፦** በዓመቱ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ማዛወር የልጅዎን ትምህርትና እድገት ሊያስቋርጥ ይችላል። በመሆኑም፣ የDCPS፣ ወላጆች የትምህርት ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ ልጆቻችውን ከትምህርት ቤት አስወጥተው ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲያዛውሩ አያበረታታም። የተማሪው ወደ ሌላ ትምህርት ቤት መሄድ ሂደት ከመጀመሩ በፊት በነበረበት/በነበረችበት ትምህርት ቤት ያለውን ግጭትና አሳሳቢ ጉዳይ ለመፍታት የሚቻለው ሁሉ ጥረት መደረግ አለበት።

ማዛወር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ለጅዎን በአዲሱ ትምህርት ቤት ከማስመዝገብዎ በፊት ከቀድሞው ትምህርት ቤት ለማስወጣት የሚያስፈለገውን የጽህፈት ስራ ማጠናቀቅ ይኖርቦታል። የማዛወሩ ሂደት አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ የልጅዎን ሪኮርዶች ወደ አዲሱ ትምህርት ቤቱ ያስተላልፋል። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የDCPS የምደባ ጽህፈት ቤትን በስልክ ቁጥር 202-939-2004 ያነጋግሩ ወይም በኢሜይል student.placement@dc.gov ይጠይቁ።

## የከአካባቢ-ውጭ ሎተሪ

**ጥ፡-** *ሎተሪው ምንድን ነው?*

**መ፡-** የትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ፣ በDCPS እና በህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ ተብብር የሚሰጥ የትምህርት ቤት ምርጫ አገልግሎት ሲሆን፣ ለቤተሰቦች ልጆቻቸውን በቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ፕሮግራሞች (ፒኬ3 እና ፒኬ4 ክፍሎች) በሚገኙ ክፍት ቦታዎች፣ ከመኖሪያ አካባቢ ውጭ ባለ የDCPS ወይም ቻርተር ትምህርት ቤቶች (ከመዋእለ-ህጻናት-12 ክፍሎች) እና የተመረጡ ተማሪዎችን በሚቀበሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ9-12ኛ ክፍሎች) ለማስመዝገብ እድል የሚሰጥ ነው። የሎተሪው ማመልከቻ ሙሉ በሙሉ ኦንላይን MySchoolDC.org. የሚሞላ ነው። በወረቀት የሚሞላ ማመልከቻ የለም።

**ጥ፡-** *ወላጆች ስል ሎተሪውና የምዝገባ ሂደት መረዳት እንዲችሉ ለማገዝ ምን ምን የመረጃ ምንጮች አሉ?*

**መ፡-** የDCPS የምዝገባ ቡድን ስለ ሎተሪው ሂደት ለወላጆች አንድ በአንድ ለማስረዳት ዝግጁ ነው። ወላጆች ልጃቸውን ትክክለኛው ቦታ ላይ ማስገባታቸውን ለማረጋገጥ እንዲችሉ ለማድረግ የምዝገባ ሂደቱን ከእያንዳንዱ ልጅ ግለ-ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ማድረግ እንፈልጋለን። ይህ ከግለ-ሁኔታ ጋር ተጣጣሚ ምዝገባ እገዛ ጊዜ፣ የDCPS መረጃ ምንጮችን የመቃኘት እገዛን፣ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘትን፣ እና ስለ አዳዲስና በመከፈት ላይ ያሉ ፕሮግራሞች የማወቅ እድል መስጠትን ይጨምራል።

ለሎተሪው ሂደት ከግለ-ሁኔታ ጋር ተጣጣሚ እገዛ ለማግኘት፣ የምዝገባ ቡድኑን በስልክ 202-478-5738 ማነጋገር ወይም በኢሜይል enroll@dc.gov መጠየቅ ይችላሉ።

**ጥ፡-** *ልጄ በቅድመ-መዋእለ-ህጻናት ፒኬ3 ወይም ፒኬ4 መመዝገብ የሚችለው በስንት ዓመቱ/ቷ ነው?*

**መ፡-** በዲሲ አስተዳደር ድንብ መሰረት፣ ቤተሰቦች ልጆቻቸው በሴፕተምበር 30 እድሜያቸው 3 ዓመት ከሆነ በፒኬ 3፣ 4 ዓመት ከሆነ ደግሞ በፒኬ4 ማስመዝገብ ይችላሉ።

**ጥ፡-** *በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ መሳተፍ፣ ለልጄ በፒኬ3 ወይም ፒኬ4 ቦታ ለማግኘት የተሻለው እድል ነው?*

**መ፡-** ከመዋእለ-ህጻናት-12ኛ ክፍሎች በተለየ መልኩ፣ ቤተሰቦች ለልጆቻቸው በፒኬ3 ወይም ፒኬ4 ቦታ የማግኘት፣ በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት እንኳን ቢሆን፣ ሙሉ በሙል እርግጠኛ መሆን አይችሉም። አንድን ልጅ በፒኬ3 ወይም ፒኬ4 ለማስመዝገብ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ ኦንላይን በትምህርት ቤቴ ዲሲ ሎተሪ ማመልከቻ በማስገባት ነው። ስለ ፒኬ3/ፒኬ4 ሎተሪ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት MySchoolDC.org ይመልከቱ።

**ጥ፡-** *ልጄን በአካባቢያችን ትምህርት ቤት ላስመዘግበው/ባት አስቢያለሁ። የሎተሪ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርብኛል?*

**መ፡-** የለብዎትም። ልጅዎን ባካባቢዎ ትምህርት ቤት ከመዋእለ-ህጻናት-12 ክፍል ባለ ክፍል አስመዝግቦ ለማስተማር፣ የሎተሪ ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልጎትም። በአካባቢ ትምህርት ቤት ስለ መመዝገብ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የDCPS ዌብሳይት dcps.dc.gov/enroll ይመልከቱ።

**ጥ፡-** *ከግለ-ሁኔታ ተጣጣሚ ትምህርት ፕሮግራሞች ተማሪዎች በሎተሪ ውስጥ ለመሳተፍ ይችላሉ?*

**መ፡-** አዎ። ከግለ-ሁኔታ-ተጣጣሚ ትምህርት ፕሮግራሞች ተማሪዎች በሎተሪው ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። ለእንደዚህ ያሉት ተማሪዎች፣ ተቀባዩ ትምህርት ቤት ከተማሪዎቹ ግለ-ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ትምህርት ፍላጎቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት እንደሚችል ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማጣራት ሊካሄድ ይችላል።

## የክፍል ተሳትፎ (Attendance)

**ጥ፡-** *ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ግዴታ ነውን?*

**መ፡-** አዎ! በአዲሱ የትምህርት ዘመን ሴፕቴምበር 30 ላይ እድሜያቸው አምስት ዓመት የሆነ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት ገብተው፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማጠናቀቅና ለምረቃ የሚያበቃቸውን መመዘኛ መሟላት እስኪችሉ ድረስ ወይም እድሜያቸው 18 እስኪሆን ድረስ በየቀኑ መማር እንዳለባቸው ህግ ያስገድዳል።

**ጥ፡-** *ከትምህርት ቤት መቅረት የሚቻልባቸው ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው?*

**መ፡-** እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት መቅረት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው፣ ተቀባይነት ባለው/ህጋዊ ምክንያትና በወላጆች ፈቃድ የቀሩ ሲሆን ብቻ ነው። ከትምህርት ቤት መቅረት የሚቻልባቸውን ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ዝርዝር ለማየት፣ እባክዎ ገጽ 15 ላይ ይመልከቱ። ከትምህርት ቤት ቀሪ ሲኮን፣ ቀሪው ከተፈጠረ ከአምስተኛው የትምህርት ቀን በኋላ የተቀረበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወሻ መቅረብ አለበት።

**ጥ፡-** *ቢያንስ 80% ትምህርት የመከታተል ህግ ምንድን ነው?*

**መ፡-** በዲሲ ህግ መሰረት፣ አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት ቀን ከ20% በላይ ትምህርት ካልተከታተለ/ች፣ እንደ ቀሪ ይቆጠራል/ትቆጠራለች።

**ጥ፡-** *የDCPS በትምህርት ላይ መገኘትንና ካለበቂ ምክንያት መቅረትን እንዴት ያየዋል?*

**መ፡-** የDCPS ከዚህ በታች ባለው የቀሪ መከታተያ ፕሮቶኮል ላይ የተመሰረተ እገዛና ድጋፍ ይሰጣል።

## SY 14-15 የ DCPS የትምህርት ክትትል ፕሮቶኮል

### ተቀባይነት የሌላቸው ቀሪዎች

***ኮኔክት-ኤድ የሚባለው የቀሪ መከታተያ ተማሪዎች መቅረታቸው በዚያው ቀን ሲመዘገብ ብቻ ለተማሪዎች በየቀኑ የሚደወል የ ቀሪ ጥሪ ነው***




# ልዩ ትምህርት

**ጥ፡-** ልዩ ትምህርት ምንድን ነው?

**መ፡-** በአካል-ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ደንብ (IDEA) መሰረት፣ ልዩ ትምህርት የሚባለው የአካል ጉዳት ያለበትን/ባትን ልጅ ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በተለየ መንገድ የተዘጋጀ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማለት ነው። በዚህ ዓቢይ የፌደራል ህግ መሰረት፣ የDCPS ለእያንዳንዱ ተማሪ ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት በነጻ መስጠት አለበት። በተጨማሪም፣ IDEA ተማሪዎች ነጻነታቸውን በማይገድብ አካባቢ ውስጥ መማር እንደሚገባቸው ያስገድዳል። ይህም ማለት፣ አካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ተማሪዎች በተቻል መጠን የአካል ጉዳት ከሌለባቸው አቻዎቻቸው ጋር አንድ ላይ ይማራሉ፤ ከዚህ የመማሪያ አካባቢ ውጭ ሊሆኑ የሚችሉት ያለባቸው የአካል ጉዳት ሁኔታ ጉዳት ከሌለባቸው አቻዎቻቸው ጋር ለመማር የማስችላቸው ከሆነ ብቻ ነው።

**ጥ፡-** ከግለ-ሁኔታ ጋር ተጣጣሚ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምንድን ነው?

**መ፡-** IEP የአካል-ጉዳተኛ ተማሪዎችን ትምህርት-ነክ ፍላጎቶችና እነዚህንም ለማሟላት የሚያስፈልጉ ትምህርትና አገልግሎቶች የሚዘረዝር ሰነድ ነው።

**ጥ፡-** የአካል-ጉዳተኛ ልጇ ያሉት የትምህርት አማራጮች እንዴት ያሉ ናቸው?

**መ፡-** የልዩ ትምህርት ሂደት የሚጀምረው፣ መምህር፣ ወላጅ፣ የስነ-ልቦና ባለሙያ፣ እና ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም ሶስተኛ ወገን (ለምሳሌ:-የቀን ክብካቤ ሰጪ ማእከል ወይም ሂኪም) ስለ ልጁ አስፈላጊውን መረጃ ሲሰጡ ነው። የመረጃው ትክክለኛነት ከተመረመረ በኋላ ፣ መደበኛ ትምህርት መምህራንነ፣ የልዩ ትምህርት መምህራንነ፣ የትምህርት ቤቱነ አስተዳደርና ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎችነ፣ ተማሪውን (ተፈጻሚ ከሆነ) እና ወላጅ/አሳዳጊን አካቶ የሚዋቀረው ከግለ-ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ትምህርት ፕሮግራም ቡድን ስብሰባ ተቀምጦ ስለ ልጁ/ጂቷ በቀረበው መረጃ ላይ ይወያያል፤ ተጨማሪ ግምገማዎች ይሰበሰባል (ወይም እንዲሰበሰቡ ሃሳብ ያቀርባል)፤ እናም ተማሪው የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችነ ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆኑን/ኗን ይወስናል።

ተማሪው/ዋ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆኑ/ኗ ከተረጋገጠ በኋላ፣ የግለ-ሁኔታ ጋር ተጣጣሚ ትምህርት ቡድኑ በቀጣዩ ተግባር እቅድ ላይ ተነጋግሮ ከተማሪው/ዋ ጋር የሚጣጣም ትምህርት ያዘጋጅለታል/ላታል። ከግለ-ሁኔታ-ጋር ተጣጣሚ ትምህርት ፕሮግራሙ የተማሪው/ዋን የትምህርት ፍላጎቶችና ይህንንም ፍላጎት ለማርካት መሰጠት የሚያስፈልጉ ትምህርቶችና አገልግሎቶች በዝርዝር ያስቀምጣል። የአካል-ጉዳተኞችት ምህርት ድንብ (IDEA) በሚያዘው መሰረት፣ የDCPS የሁሉንም ተማሪዎች ነጻነት በማይጋፋ አካባቢ አገልግሎቶች ይሰጣል።

የDCPS፣ በእያንዳንዱ ተማሪ የአካባቢ ወይም ሰፈር ትምህርት ቤት ተገቢዎቹ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ካሉ በነዚሁ ስፍራዎች አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል። ይህን ማድረግ ሳይቻል ሲቀር፣ የDCPS፣ ተማሪው/ዋን በተቻል መጠን ለቤቱ/ቷ ቅርብ በሆነና የልዩ ትምህርት ፕሮግራሙን አገልግሎቶች መስጠት በሚችል፣ ክፍት ቦታ ባለው ሌላ ትምህርት ቤት ወረዳ-አቀፍ ክፍል ይመድባል።

## ምዘናዎች

**ጥ:-** የDCPS ለተማሪዎች ፈተናዎችን የሚሰጠው ለምንድን ነው?

**መ:-** የስቴት የበላይ የትምህርት አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ የDCPS ለ3-8ኛ ክፍሎችና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ የሂሳብና እንግሊዝኛ/ቋንቋ አርቶች/የንባብ ፈተና በ PARCC እንዲሰጥ፣ እንዲሁም ለመጀመሪያ ደርጃ፣ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንድ ጊዜ የሳይንስ ቴስት እንዲሰጥ ያስገድዳል። በተጨማሪም፣ የዲሲ ከተማ ካውንስል ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለኮሌጅ ትምህርት እንዲዘጋጁ የ SAT ፈተና እንዲወስዱ ያስገድዳል። ACCESS፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የእንግሊዝኛ ትምህርት አቀባበል እርምጃ በመከታተል፣ ከፍተኛ አእምሯዊ ጉዳቶች ያለባቸው ተማሪዎች በPARCC ምትክ NCSC እንዲወስዱ ያደርጋል። ሌሎቹ መመዘኛዎች መምህራንና ቤተሰቦች ስለ ተማሪው ትምህርት አቀባበልና አሰራር እንዲረዱ ለማስቻል፣ ብሎም የትምህርቱን ተገቢነት ለማረጋገጥ ወይም መስተካከል እንዳለበት ለማወቅ የሚያገለግሉ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃ የልጅዎን መምህር ያነጋግሩ ወይም በኢሜይል dcps.testing@dc.gov ይጠይቁ።

**ጥ:-** የ PARCC ፈተና በልጄ ውጤቶች ላይ እንደምን ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል?

**መ:-** በዲሲ የስታንዳርዶች እድገት ካውንስል (CAS) መመሪያ መሰረት፣ የልጅዎ የ PARCCፈተና ነጥቦች በክፍል ውጤቶቹ ላይ ምንም ተጽእኖ አይኖራቸውም።

## የከትምህርት ቤት በፊትና በኋላ ፕሮግራሞች

**ጥ:-** ለልጄ ያሉት የከትምህርት ቤት በፊትና በኋላ አማራጮች የትኞቹ ናቸው?

**መ:-** አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የክብካቤ-በፊት አገልግሎቶችን ሲሰጡ፣ ብዙ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከDCPS የትምህርት ቤት ውጭ ጊዜ ፕሮግራሞች ጽህፈት ቤት፣ ከማህበረሰብ-ምስርት ድርጅቶች ወይም በትምህርት ቤት ከሚመሩ ፕሮግራሞች ጋር በመተባበር ለመጀመሪያ ደረጃ፣ ለኢለመንተሪና መካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የከትምህርት ቤት በኋላ ፕሮግራም አማራጮችን ይሰጣሉ። ስለ ትምህርት ቤትዎ የከትምህርት ቤት በፊትና በኋላ አማራጮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ትምህርት ቤትዎን በቀጥታ ያነጋግሩ።

## የምግብ አገልግሎቶች

**ጥ:-** ልጄ የነጻ ወይም ቅናሽ ምግብ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆኑ/ኗን እንዴት ማወቅ እችላለሁ? ብቁ ካልሆነ/ች ለምሳው/ዋ እንዴት መክፈል ይችላል/ትችላለች?


**መ:-** ልጅዎን በሚያስመዘግቡበት ወቅት፣ የነጻና ቅናሽ ምግብ ፎርም (FARM)እንዲሞሉ ይጠየቃሉ። ይህ ፎርም በገቢ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ልጅዎ አገልግሎቱን ለማግኘት ብቁ መሆን አለመሆኑ/ኗ የሚወሰንበት ነው። ልጆችዎ ለነጻና ቅናሽ ምግብ ብቁ ካልሆኑ ምሳቸውን በየቀኑ መግዛት አለባቸው። በተማሪዎች ይምሳ አካውንት ገንዘብ መጨመሪያ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ስለ ተማሪዎች የምሳ ገንዘብ አከፋፈል ተጨማሪ መረጃ ኦንላይን http://dcps.dc.gov/page/nutrition-and-meals ማግኘት ይቻላል።

እባክዎ በማንኛውም የDCPS ቁርስ ለሁሉም ተማሪዎች በነጻ እንደሚሰጥ ያስታውሱ።

እዚህ ከተዘረዘሩት ሌላ ጥያቄ አሎት?

ለDCPS በስልክ ቁጥ202.442.5885 በመደወል ወይም በኢሜይል OFPE.info@dc.gov ነጻነት ይሰማዎት።

# የማእከላዊ ጽሕፈት ቤት ቢሮዎች ዝርዝር



## የቤተሰቦች እና ተማሪዎች አገልግሎቶች ቢሮዎች ዝርዝር

| | |
|---|---|
| የDCPS ማእከላዊ ጽህፈት ቤት | 202.442.5885 |
| የቻንስለር ጽህፈት ቤት | 202.442.5885 |
| አካዳሚያዊ አገልግሎቶች | 202.673.4488 |
| ከትምህርት ቤት-በኋላ ፕሮግራሞች | 202.442.5002 |
| ምዘናዎች | 202-727-7844 |
| አትሌቲክስ | 202.729.3288 |
| የክፍል ተሳትፎ (Attendance) | 202.442.5450 |
| ልሳነ-ክልኤ ትምህርት | 202.671.0750 |
| የኮሌጅና ሙያ ጽህፈት ቤት | 202.442.9243 |
| የኮሌጅ ፕሮግራሞች | 202-625-7293 |
| የሙያ ፕሮግራሞች | 202-727-7904 |
| Office of Teaching and Learning | 202.673.4488 |
| ተግባቦቶች | 202.805.2885 |
| የማህበረሰብ አጋርነት | 202.719.6613 |
| ዴታና ስትራቴጂ | 202-719-6637 |
| የዲሲ ዋን ካርድ | 202.671.2273 |
| ዲጂታል የውጤት መዝገብ | 202.719.6613 |
| የቅድመ-ልጅነት (ህጻንነት) ትምህርት | 202.698.1033 |
| የመጀመሪያ ደረጃዎች | 202.698.8037 |
| ምዝገባ | 202.478.5738 |
| የቤተሰብና ህዝብ ተሳትፎ | 202.719.6613 |
| የምግብ አገልግሎቶች | 202.442.5112 |
| ለምረቃ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች (መስፈርት) | 202-442-5047 |
| ቤትአልባ ወጣቶች | 202.576.9502 |
| የሰው ሃይሎች | 202.442.4090 |
| የትምህርት የበላይ አስተዳደሮች | 202.442.5885 |
| የቋንቋ ፈተና | 202.671.0750 |
| የ LGBTQ ተማሪዎች ድጋፍ | 202-724-1505 |
| የአካባቢ ትምህርት ቤት መማክርት ቡድን | 202.719.6613 |
| ዲሲ ትምህርት ቤቱ | 202-888-6336 |
| ኒው ሃይትስ ቲን ፓሬንት ፕሮግራም | 202.645.4040, |
| የከአካባቢ-ውጭ-ትምህርት ቤት ሎተሪ | 202.478.5738 |
| ከትምህርት ቤት ውጭ ጊዜ | 202.442.5002 |
| ነዋሪነት ማረጋገጫ | 202.442.5738 |
| ትምህርት ቤቶች | ለትምህርት ቤቱ ቢሮዎች የተሟላ መጠቆም http://profiles.dcps.dc.gov/ ይመልከቱ። |
| ልዩ ትምህርት | 202.442.4800 |
| የተማሪዎቸ ምደባ | 202.939.2004 |
| የክረምት ትምህርት | 202.442.5002 |
| መጓጓዣ (የወላጅ ጥሪ ማእከል፣ የ OSSE ልዩ ትምህርት ክፍል መጓጓዣ (DOT) | 202.576.5000 |
| የቤትና ሆስፒታል ትምህርት (ቀደም ሲል የጉብኝት ትምህርታዊ አገልግሎቶች) | 202.939.3506 |
| ፈቃደኞች | 202.442.5447 |

## ተጨማሪ አገልግሎቶች

### የዲሲ መንግስት

| | |
|---|---|
| የስቴት የትምህርት የበላይ አስተዳደር ጽህፈት ቤት (OSSE) | 202.727.6436 |
| የዲሲ ስቴት የትምህርት ቦርድ | 202.741.0888 |
| የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም(Ombudsman) | 202.741.0886 |
| የከንቲባ ጥሪ ማእከል | 311 |
| የከተማ ካውንስል | 202.724.8000 |
| የድንገተኛ አደጋ ምላሽ | 911 |
| የዲሲ ጤናማ ቤተሰቦች (ነጻ የጤና ኢንሹራንስ) | 202.639.4030 |
| የጤና ዲፓርትመንት | 202.442.5955 |
| የባህርይ ጤና ዲፓርትመንት | 202.673.7440 |
| የልጅና ወላጆች አገልግሎቶች አስተዳደር (CFSA) | 202.442.6100 |
| የጥፋት ሪፖርት (Report Abuse) | 202.671.SAFE (7223) |

# የDCPS አስተያየትዎን መስማት ይፈልጋል!

### ወላጆች፣ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፦

ይህ የDCPS የወላጅ መመሪያ መጽሃፍ ጠቃሚ ነውን?
የጎደለ ወይም ግራ-እሚያጋባ መረጃ አለ?
በወደፊት ህትመት እንዲሻሻል የሚፈልጉት አስተያየት አሎት?

### እባክዎ በሚከተሉት ያነጋግሩን፦



ofpe.info@dc.gov



202.719.6613

# የተለመዱ ምህጻር-ቃላት



## የተለመዱ ምህጻር-ቃላት

*(ይሄ የተሟላ ዝርዝር አይደለም)*

| ምህጻር-ቃል | ትርጉም |
|---|---|
| ANet | Achievement Network Assessment (የስኬት መረብ ምዘና) |
| ALT | Academic Leadership Team (የትምህርት አመራር ቡድን) |
| AP | Advanced Placement (ከፍተኛ ምድብ) |
| APL | Assistant Principal of Literacy (የማንበብና-መጻፍ ረዳት ሃላፊ) |
| CAT | Community Action Team (የማህበረሰብ ተግባር ቡድን) |
| CCSS | Common Core State Standards (የተለመዱ ዓበይት የስቴት ደረጃዎች) |
| CFO | Chief Financial Officer (ዋና የፋይናንስ ሃላፊ) |
| DC CAS | District of Columbia Comprehensive Assessment System (የዲሲ አጠቃላይ ምዘና ስርዓት) |
| DCMR | DC Municipal Regulations (የዲሲ ከተማ ደንቦች) |
| DCPS | District of Columbia Public Schools |
| DIBELS | Dynamic Indicators of Basic Early Literacy Skills (መሰረታዊ የመጀመሪ ደረጃ የማንበብ-መጻፍ ክሂሎት ተለዋዋጭ አመልካቾች) |
| DLI | Dual Language Immersion (ክልኤ ቋንቋ ጠለቃ) |
| DME | Deputy Mayor for Education (የትምህርት ምክትል ከንቲባ) |
| EC | Education Campus (የትምህርት ካምፓስ) |
| ECE | የቅድመ-ልጅነት (ህጻንነት) ትምህርት |
| ELL | English Language Learner (እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ) |
| ES | Elementary School (አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) |
| ESEA | Elementary and Secondary Education Act (የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መመሪያ) |
| ESL | English as a Second Language (እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ) |
| FARM | Free and Reduced Meal (ነጻና ቅናሽ ምግብ) |
| FLES | Foreign Language in Elementary School (የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የውጭ ቋንቋ) |
| FLEX | Foreign Language Exploratory in Elementary School (የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የውጭ ቋንቋ አሰሳ) |
| FOIA | Freedom of Information Act (የመረጃ ነጻነት መመሪያ) |
| GED | General Educational Development (የአጠቃላይ ትምህርት እድገት) |
| GPA | Grade Point Average (የክፍል አማካይ ነጥብ) |
| HHIP | Home/Hospital Instruction Program (የቤት/ሆስፒታል ትምህርት ፕሮግራም) |
| HS | High School (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) |
| IB | International Baccalaureate (ዓለም-አቀፋዊ ባካሎሬት) |
| IEP | Individual Education Program (የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም) |

| | |
|---|---|
| IS | Instructional Superintendent (የትምህርት የበላይ አስተዳደር) |
| LCD | Linguistically and Culturally diverse (የቋንቋና የባህል ብዝሃነት) |
| LEA | Local Education Agency (የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲ) |
| LGBTQ | Lesbian, Gay, Bisexual, Transgender, and Questioning (ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ከልኤ-ጾታ፣ ቅይር-ጾታ፣ እና ጠያቂ) |
| LSAT | የአካባቢ ትምህርት ቤት መማከርት ቡድን |
| MS | Middle School (መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) |
| NCLB | No Child Left Behind (ማንም ህጻን ወደ ኋላ አይቅር) |
| OCOM | Office of Communications (የተግባቦቶች ጽህፈት ቤት) |
| OCOS | Office of the Chief of Schools (የትምህርት ቤቶች ሃላፊ ጽህፈት ቤት) |
| OCOO | Office of the Chief Operating Officer (ዋና የትግበራ ሃላፊ ጽህፈት ቤት) |
| OCC | የኮሌጅና ሙያ ጽህፈት ቤት |
| ODS | Office of Data and Strategy (የዴታና ስትራቴጂ ጽሕፈት ቤት) |
| OFPE | Office of Family and Public Engagement (የቤተሰብና ህዝብ ተሳትፎ ጽህፈት ቤት) |
| OGC | Office of the General Counsel (የጠቅላላ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት) |
| OHC | Office of Human Capital (የሰብዓዊ ካፒታል ጽህፈት ቤት) |
| OIR | Office of Innovative and Research (የፈጠራና ምርምር ጽህፈት ቤት) |
| OOC | Office of the Chancellor (የቻንስለር ጽሕፈት ቤት) |
| OOO | Out of Office (ከስራ ውጭ) |
| OSSE | Office of the State Superintendent of Education (የስቴት የትምህርት የበላይ አስተዳደር ጽህፈት ቤት) |
| OTL | Office of Teaching and Learning |
| PARCC | Partnership for Assessment or Readiness for College and Career (የኮሌጅና ሙያ ምዘና ወይም ዝግጁነት አጋርነት) |
| PK3, PK4 | Pre-Kindergarten 3, Pre-Kindergarten 4 (ቅድመ-መዋእል-ህጻናት 3፣ ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4) |
| SST | Student Support Team (የተማሪ ድጋፍ ቡድን) |
| STARS | Student Tracking and Reporting System (የተማሪ ክትትልና ሪፖርት ሲስተም) |
| STEM | Science, Technology, Engineering and Math (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ) |
| TRC | Text Reading Comprehension (የጽሁፍ ንባብ መረዳት) |
| UHC | Universal Health Certificate (ዓለም-አቀፋዊ የጤና ሰርተፊኬት) |

# አባሪ፡ የትምህርት ቤት አካዳሚያዊ አቅርቦት



## የቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 3 እና ቅድመ-መዋእለ-ህጻናት 4 ፕሮግራሞች

| | | |
|---|---|---|
| የሬጊዮ ኤሚሊያ አቀራርብ | ብሬንት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሉድሎው-ቴይለር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ማን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ሚነር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያለ ት/ቤት<br>ዎልክ-ጆንስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| ሞንተሶሪ | በርቺል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ካፒቶል ሂል ሞንተሶሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ላንግዶን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ጄ.ሲ. ናል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| የአእምሮ መሳሪያዎች | አሚዶን-ቦዌን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ባንክሮፍት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በርናርድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቢርስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ብራይትዉድ የትምህርት ካምፓስ<br>በቢ.ኤች አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የብሩክላንድ ትምህርት ካምፓስ<br>ብራወን ትምህርት ካምፓስ<br>ቡሮፍስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሲ ደብሊዩ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ድሪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በፍራንሲስ-ስቴቨንስ ትምህርት ካምፓስ ኤስ ደብሊዩ ደብሊዩ<br>ጋርፊልድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ጋሪሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሃውስተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ጄ ኦ ዊልሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኪምባል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ማርቲን ሉተር ኪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሜሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኖይስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ኦር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ፓተርሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ፓይኒ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ፕሉመር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ፓወል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ራንድል-ሃይላንድስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሬይመንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሳቮይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሳተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሲሞን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ስሞዘርስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ስታንተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ታኮማ ትምህርት ካምፓስ<br>ቶማስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ትሩስደል ትምህርት ካምፓስ<br>ተምባን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በግሪን የተርነር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ዊትሊ ትምህርት ካምፓስ<br>ዊተር ትምህርት ካምፓስ |
| ፈጠራዊ ስርዓተ-ትምህርት | ኤይተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በፓርክ ቪው የብሩስ-ሞንሮ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በርቺል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኤች ዲ ኩክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሄንድሊ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሃውስተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሃይድ-አዲሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ጄኒ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ከችማ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ሉድሎው-ቴይለር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሚነር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በዊልኪንሰን የሞቴን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኔል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ፒቦዲ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቶምሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቴይለር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ዎከር-ጆንስ ትምህርት ካምፓስ<br>ዌስት ትምህርት ካምፓስ |

## የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች (ከመዋእለ-ህጻናት-5ኛ ክፍል)

| | | |
|---|---|---|
| ዓለም-አቀፋዊ ባካሎሬት-<br>የመጀመሪያ ዓመታት ፕሮግራም | የብራውን ትምህርት ካምፓስ (እጩ)<br>ኤች.ዲ. ኩክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሼፐርድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ቶምሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ተርነር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ክልሌ ቋንቋ | ባንክሮፍት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>በፓርክ ቪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ብሩስ ሞንሮ<br>ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>Columbia Heights EC | ሜሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>አይስተር-አዳምስ ባይሊንጓል ስኩል<br>ፓወል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቴይለር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| የኪነ-ጥበባት ትኩረትና ጥምረት | ፊልሞር፡-<br>ሃይድ-አዲሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኬይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሜሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሮስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ስቶደርት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ትኩረት-መላሽ ትምህርት ቤቶች፡-<br>በንከር ሂል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>መተን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኖየስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሳቮይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ተርነር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| መላው ትምህርት ቤት ውሁድ ትምህርት | ብራወን ትምህርት ካምፓስ<br>ጋርፊልድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሲሞን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>አሚዶን-ቦዌን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ትሩስዴል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ዊትሊ ትምህርት ካምፓስ<br>ክሊቭላንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ኬችማ<br>ራንድል-ሃይላንድስ<br>ፓተርሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቢርስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ለኪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኔል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ድሪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| የሳይንስ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ ጥምረት ትምህርት ቤቶች | ቢርስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ቡሮፍስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ላንግዶን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ላንግለይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ማልኮም ኤክስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ዊተር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |

## መካለኛ ትምህርት ቤት/ክፍሎች ፕሮግራሞች (ከ6-8ኛ ክፍሎች)

| | | |
|---|---|---|
| ትምህርት ቤት-አቀፍ የማበልጸጊያ ሞዴል (SEM) | ሃርዲ መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኬሊ ሚለር መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ጆንሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት | ሶሳ መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ስቱዋርት-ሆብሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ዌስት ትምህርት ካምፓስ |
| መላው ትምህርት ቤት ውሁድ ትምህርት | ብራወን ትምህርት ካምፓስ<br>ጆንሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ስቱዋርት-ሆብሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ትሩስዴል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ክራመር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ሃርት መካለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ኮሎምቢያ ሃይትስ ትምህርታዊ ካምፓስ<br>ዊትሊ ትምህርት ካምፓስ |
| የክልሌ ቋንቋ ትምህርት | ጆንሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት | አይስተር-አዳምስ |
| ትምህርት ቤት ማበልጸጊያ ሞዴል | ስቱዋርት-ሆብሰን መካለኛ ደረጃ ት/ቤት | ሶሳ መካለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት<br>ስቶዋርት-ሆብሰን መካለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት<br>ምእራብ ትምህርት ካምፓስ |
| ዓለም-አቀፋዊ ባካሎሬት - መካለኛ ዓመታት ፕሮግራም | ትሩስዴል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | ኢሊየት-ሃይን (እጩ) |
| የሳይንስ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ ጥምረት ትምህርት ቤቶች | ማኪንሌይ መካለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት<br>ቦሮፍስ ትምህርት ካምፓስ | ላንግሊ ኢ ኤስ ዊተር ትምህርት ካምፓስ |

### ሩዝቬልት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

| | |
|---|---|
| ከፍተኛ የኮርስ አቅርቦት | ኤፒ ካልኩለስ ኤቢ፣ ኤፒ እንግሊዝኛ ቋኝቋና ድርሰት፣ ኤፒ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሑፍና ድርሰት፣ ኤፒ ስቱዲዮ አርት/ድሮዊንግ፣ ኤፒ ዩ.ኤስ. ገቨርንመንት፣ ዩ.ኤስ. ሂስትሪ |
| የዓለም ቋንቋ አቅርቦት | ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ |
| የሌሎች ፕሮግራም መግለጫ | ጄ አር ኦ ቲ ሲ |

### ዊልሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቢርት

| | |
|---|---|
| ከፍተኛ የኮርስ አቅርቦት | ኤፒ ባዮሎጂ፣ ኤፒ ካልኩለስ ኤቢ፣ ኤፒ ካልኩለስ ቢሲ፣ ኤፒ ኬሚስትሪ፣ ኤፒ ቻይኒዝ ቋንቋና ባህል፣ ኤፒ ኮምፓራቲቭ ገቨርንመንት፣ ኤፒ ኮምፒዩተር ሳይንስ፣ ኤፒ ኤኮነሚክስ፡- ማክሮ፣ ኤፒ ኤኮኖሚክስ፡- ማይክሮ፣ ኤፒ እንግሊዝኛ ቋኝቋና ድርሰት፣ኤፒ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍና ድርሰት፣ አካባቢያዊ ሳይንስ፣ ኤፒ ፈረንሳይኛ ቋንቋ (V)፣ ኤፒ ሁዩመን ጆግራፊ፣ ኤፒ ላቲን፣ ኤፒ ፊዚክስ ቢ፣ ኤፒ ፊዚክስ ሲ፡- ኤሌክትሪክሲት አንድ ማግኔቲዝም፣ ኤፒ ፊዚክስ ሲ፡- ሜካኒክስ፣ ኤፒ ሳይኮሎጂ፣ ኤፒ ስፓኒሽ ቋንቋ፣ ኤፒ ስፓኒሽ ስነ-ጽሑፍ፣ ኤፒ ስታትስቲክስ፣ ኤፒ ስቱዲዮ አርት/2-ዲ ዲዛይን፣ ኤፒ ስቱዲዮ አርት/ድሮዊንግ፣ ኤፒ ዩ.ኤስ. ገቨርንመንት፣ ኤፒ ዩ.ኤስ ሂስትሪ፣ ኤፒ ዎርልድ ሂስትሪ |
| የዓለም ቋንቋ አቅርቦት | አመሪካን ሳይን ላንጉዌጅ፣ ቻይኒዝ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ላቲን፣ ስፓኒሽ |
| የሌሎች ፕሮግራም መግለጫ | አርት፡- ዲጂታል አርትስ ላብ፤ ጆርጅታዎን ስትሪት ሎው |

### ዉድሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

| | |
|---|---|
| ከፍተኛ የኮርስ አቅርቦት | ኤፒ እንግሊዝኛ ቋኝቋና ድርሰት፣ኤፒ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍና ድርሰት፣ ኤፒ ኢንቫይሮሜንታል ሳይንስ፣ ኤፒ ስታትስቲክስ፣ ኤፒ ዩ.ኤስ. ገቨርንመንት፣ ኤፒ ዩ.ኤስ. ሂስትሪ፣ ኤፒ ወርልድ ሂስትሪ |
| የዓለም ቋንቋ አቅርቦት | ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ |
| የሌሎች ፕሮግራም መግለጫ | የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት (ፒኢ)፡- አርቸሪ፤ ጆርጅታዎን ዩኒቨርሲቲ ስትሪት ሎው፣ 9ኛ ክፍል ኮምፒዩተር ሳይንስ |

## ኒው ሃይትስ ፕሮግራም

| | |
|---|---|
| አናኮስቲያ | 202.645.4040 |
| ባሎው | 202.645.3400 |
| ባሎው ኤስ ቲ ኤ ዋይ | 202.727.5344 |
| ካርዶዞ | 202.671.1995 |
| ሲ.ኤች.ኢ.ሲ | 202.939.7700 ቴክስት 5063 |
| ኮሊጅ | 202.282.0081 |
| ደንባር | 202.698.3762 |
| ሉክ ሲ. ሙር | 202.678.7890 |
| ሩዝቬልት | 202.576.8899 |
| ሩዝቬልት ኤስ ቲ ኤ ዋይ | 202.576.8399 |
| ዋሺንግተን ኤም ኢ ቲ | 202.727.4985 |
| ዊልሰን | 202.282.0120 |
| ዉድሰን | 202.939.2030 |

## ልዩ የDCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ9-12ኛ ክፍሎች)

የDCPS የራሳቸው የምዝገባ መስፈርት ያላቸው ስድስት ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያንቀሳቅሳል። ከተማው ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች ለምዝገባ እንዲያመለክቱ ተጋብዘዋል። እያንዳንዱ ልዩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የራሱ የሆኑና የተለያዩ ትምህርት አቅርቦቶች፣ እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በርካታ የሰርተ-ትምህርት ትኩረት አሉት። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አቅርቦቶች መግለጫ ከዚህ በታች ቀርቧል።

### McKinley Technology High School

ማኪንሌይ የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስናና ሂሳብ ትምህርት ቤት (STEM) ሲሆን፣ የራሱ የምዝገባ ማመልከቻ ሂደት አለው። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ የምህንድስና፣ ባዮቴክኖሎጂ፣ እና ኢንፎርማሽን ቴክኖሎጂ ኮርሶችን ይሰጣል። ምህንድስና ወይም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) የሚመርጡ ተማሪዎች የናሽናል አካዳሚ ፋውንዴሽን (NAF) አካዳሚስ አካላት ይሆናሉ።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ ስታትስቲክስ፣ ካልኩለስ ኤቢ፣ የዓለም ታሪክ፣ የዩ.ኤስ. መንግስት፣ ዩ.ኤስ. ታሪክ፣ ኬሚስትሪ፣ አካባቢያዊ ሳይንስ፣ ባዮሎጂ፣ ፊዚክስ 1-- አልጄብራ ላይ የተመሰረተ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሑፍና ሰብዓዊ ጆግራፊ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ስፓኒሽና ማንደሪንን ይጨምራሉ።

### ቤንጃሚን ባነከር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የቤንጃሚን ባነከር አካዳሚያዊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከዲሲ ዓለም-አቀፋዊ የባካሎሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም ሳይቶች አንዱ ሲሆን፣ የቅድመ-ዓለም-አቀፋዊ ባካሎሬት ኤፒንና የራሱን የክረምት ተቋም እንደ አንድ ተጨማሪ ጠንካራ አካዳሚያዊ አማራጭ ያቀርባል። የመምህር-አማካሪና ማህበረሰብ በተ-መከራል ፕሮግራሞች የአንድ-ለአንድ የማማከር አገለግሎት በመስጠት፣ የተማሪዎችን የወደፊት ህይወት መልክ ለማስያዝ በተገቢ ሰብዓዊ ግንኙነቶች ውስጥ እንዲሳተፉ ያበረታታል። የተማሪዎች ቅበላ በራሱ የማመልከቻ ሂደት አማካኘነት የሚካሄድ ሲሆን፣ በተለያዩ የባህርይ-እና
ከሂሎት ግንባታ ተጓዳኝ-ስርዓት-ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚደገፍ ነው። የባነከር የተማሪ ልምድ፣ ተማሪዎች እውቀት፣ ተሰጥኦዎችና ልዩ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ልምዶችን እንዲያዳብሩ ያስችላል።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ ካልኩለስ-ኤቢ፣ የዩ.ኤስ. ታሪክ፣ የዩ.ኤስ. መንግስት (ፖለቲካና አወዳዳሪ)፣ የዓለም ታሪክ፣ ሰብዓዊ ጆግራፊ፣ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍ፣ ስታትስቲክስ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ባዮሎጂ፣ የአርት ታሪክ፣ የሚዚቃ ቲዎሪ፣ እና ኪሚስትሪ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛንና ላቲንን ይጨምራል።

### Columbia Heights Education Campus

የኮሎምቢያ ሃይትስ ትምህርታዊ ካምፓስ 9 CHEC) ለየት ያለና ዓለም-አቀፋዊነ ጭብጥን የተላበሰ ልሳነ-ክልኤያዊ ካምፓስ ሲሆን ፣ ከ6-12ኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎችን የሚያገለግልና ሁሉንም ተማሪዎቹን ለኮሌጅና ለሙያ ስኬት የሚያዘጋጅ ነው። CHEC በከፍተኛ ምድብ ፈታኣኝነት የደርጃ ሰንጠረዥ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች የከፍተኛ ምድብ ፕሮግራሞችን በመስጠት ከላይ ከሚቀመጡት በአካባቢውና በሃገሪቱ ውስጥ ካሉት ትምህርት ቤቶች አንዱ ነው። በዋሺንግተን ዲሲ ውስጥ ያለው ብቸኛው የስፓኒሽ ቋንቋ ድርብ-ጠለቃ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም የሚገኝበትም ነው። ተማሪዎች እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ሙሉ በሙሉ ልሳነ-ክልኤ የሆነ ፕሮግራም መከታተል ይችላሉ። CHEC በ2013 ባሳየው ትምህርታው ፈጠራ፣ ፋይት ፎር ቺልድረን በተሰኘው ድርጅት ለትምህርት ቤቶች ጥራት ሽልማት (Quality Schools Initiative Award ተመርጦ ነበር። የ CHEC ተማሪዎች ከ 20 ከሚበልጡ ሃገራት የሚመጡ ሲሆን፣ ይህን ብዝሃነት ዓለም-አቀፋዊ ጭብጥ የተላበሰውን ስርዓተ-ትምህርታችንን የበለጠ ለማጠናከር እንጠቀምበታለን። እያንዳንዱ ክፍል አንድ ዓለም-አቀፋዊ ጭብጥን በስፋት የሚያሥ ሲሆን፣ ይህም የተማሪዎችን ትምህርት እርስ-በርስ የሚያስተሳስርና ዓለም-አቀፋዊ ግንዛቤያቸውንም የሚያዳብር ነው።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ ስቱዲዮ አርት/2-ዲ ዲዛይን፣ ስቱዲዮ አርት/3-ዲ ዲዛይን፣ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የዩ.ኤስ. ታሪክ፣ የዩ.ኤስ. መንግስት፣ ፈረንሳይኛ፣ጣሊያንኛ፣ ስፓኒሽ ስነ-ጽሁፍ፣ ስፓኒሽ ቋንቋ፣ ካልኩለስ ኤቢ፣ ስታትስቲክስ፣ ኮምፒዩተር ሳይንስ፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ ቢ፣ እና የሙዚቃ ቲዎሪ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት አረብኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ የቻይና ማንደሪን እና ድርብ ጠለቃ ስፓኒሽን ይጨምራሉ።

## Duke Ellington School of the Arts

የዱክ ኤሊንግተን የኪነ-ጥበባት ትምህርት ቤት፣ በዲሲ ውስጥ ያለ፣ ሙሉ የኮሌጅ መዘጋጃ ስርዓተ-ትምህርትን በአጭር-ጊዜ ከሚሰጥ እምቅ የቅድመ-ሙያ የኪነ-ጥበብ ስልጠና ጋር አዋሕዶ የሚያቀርብ ብቸኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ኤሊንግተን ከአጋሮቹ ጋር በሚያገኘው ድጋፍ በመታገዝ፣ ከከተማው የተለያዩ ክፍሎች የሚመጡ ብዝሃነትና ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ያገለግላል። የተማሪዎች ቅበላ ቃለ-መጠይቅና ተግባራዊ-ክዋኔ ፈተናን (audition) በሚያካትት የማመልከቻ ሂደት የሚከናወን ሲሆን፣ ከሚከተሉት ስምንት ዓቢይ መስኮች አንዱን መምረጥ ይቻላል፦ ዳንስ፣ የመሳሪያ ሙዚቃ፣ ስነጽሁፋዊ ሚዲያና ተግባቦቶች፣ የሙዚየም ጥናቶች፣ ቴክኒካዊ ዲዛይንና ፕሮዳክሽን፣ ቲያትር፣ እይታዊ ኪነ-ጥበባትና የድምጻዊነት ሙዚቃ። ተማሪዎች ስራዎቻቸውንና ኤግዚቢሽን በኬኔዲ ማእከል፣ በኋይት ሃውስና በብሄራዊና ዓለም-አቀፍ ሁነቶች ያቀርባሉ።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ የአርት ታሪክ፣ ስቱዲዮ አርት/ስእል፣ ንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የዩ.ኤስ. ታሪክ፣ የዩ.ኤስ መንግስት፣ የዓለም ታሪክ፣ ፈረንሳይኛ፣ ካልኩለስ ኤቢ፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ እና የሙዚቃ ቲዎሪ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛና ስፓኒሽን ይጨምራል።

## ስኩል ዊዘውት ዎልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (SWW)

SWW የህዝብ ማግኔት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ1971 የተመሰረተና በመካከለኛ ደረጃ የኮሌጅና የትምህርት ቤት የስቴት ማህበር እውቅና ያለው ነው። ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ዓመታት በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ ካሉ እጅግ ታዋቂ ትምህርት ቤቶች አንድ ለመሆን በቅቷል። SWW በ2010፣ በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የብሉ ሪባን ስኩል እውቅና የተሰጠው ሲሆን፣ ይህም ተማሪዎቹን ለከፍተኛ ደረጃ ስኬት ማብቃት ለቻሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ እውቅና ነው። በኒውስዊክ የ2013 የአሜሪካ ምርጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ውስጥ ስኩል ዊዘውት ዎልስ ትምህርት ቤት አንደኛውን ደረጃ ይዟል። ስኩል ዊዘውት ዎልስ ጥራት ያለው ተማሪ-ተኮር የትምህርት አካባቢን የሚሰጥ ሲሆን፣ ይህም በሰብዓዊ-ሳይንሶች የትምህርት ማእቀፍ አቀራረብ የሚሰጥን አሳታፊ፣ ተራክቧዊና ተግባራዊ ትምህርትን ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ነው። ይህ ፕሮግራም ዓላማውን ከግብ የሚያደርሰው ከተማውንና ዓለምን ለተማሪዎች ትምህርት እንደ መማሪያ ክፍል በመጠቀም ነው።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ ስቱዲዮ አርት/ስእል፣ እንግሊዝኛ ስነ-ጽሁፍ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የዩ.ኤስ. ታሪክ፣ የዓለም ታሪክ፣ ሰብዓዊ ጅግራፊ፣ ሳይኮሎጂ፣ የዩ.ኤስ. መንግስት፣ ፈረንሳይኛ ላቲን፣ ስፓኒሽ ቋንቋ፣ ቻይኒዝ፣ ካልኩለስ ኤቢ፣ ካልኩለስ ቢሲ፣ ስታትስቲክስ፣ አካባቢያዊ ሳይንስ፣ ባዮሎጂ ኪሚስትሪ፣ ፊዚክስ ሲ፦ ሜካኒክስ. ፊዚክስ 1፦ አልጄብራ ላይ የተመሰረተ፣ እና የሙዚቃ ቲዎሪ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ፈረንሳይኛ፣ ላቲን፣ ስፓኒሽና የቻይና መንደሪንን ይጨምራል።

## ፊልፕስ የስነ-ህንጻ (አርኪቴክቸር)፣ ግንባታና ምህንድስና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ፊልፕስ ጠንካራና ፈጠራዊ ስርዓተ-ትምህርት ያለው፣ ከመላው-ከተማ ማመልከቻ ተቀባይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ለኮሌጅ ማዘጋጀና የሙያና የቴክኒክ ትምህርት የሚሰጥ በሃገሪቱ ውስጥ ያለ ብቸኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ በዲዛይን ሙያዎችና ግንባታ ስራዎች ላይ ብቻ በማተኮር በተከታታይ ኮርሶች መጠናቀቅ ላይ የተመሰረተ የስራ ሰርቲፊኬት የሚሰጥ ትምህርት ቤት ነው። መላው የትምህርት ቤቱ ህንጻ እንድ አንድ የመማሪያ መሳሪያ እንዲያገለግል ተደረጎ ዲዛይን የተደረገና፣ ግድግዳዎቹም ለጡብ-ድርደራና ያልተሸፈኑ የቧንቧ መስመር ዝርጋታ ትክክለኛ ምሳሌነትና ከፍተኛ የትምህርት መርጃ መሳሪያነት የሚያገለግሉበት ነው። ፊልፕስ የአርክቴክቸር፣ ግንባታና ምህንድስና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በዓበይት አካዳሚያዊ ኮርሶች፦ በእንግሊዝኛ፣ በሂሳብ፣ በፊዚካል፣ ሶሻልና ኮምፒዩተር ሳይንሶች፣ ታሪክ፣ ስነ-ጥበባትና የዓለም ቋንቋዎች የተደገፈ፣ በእውኑ-ዓለም ላይ የሚያተኩር፣ ፕሮጄክት-ምስርት ስርዓተ-ትምህርት ያለው ነው። ኮርሶች የሚሰጡት ልዩ ልዩ የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን፣ የሙያና ቴክኒክ ትምህርትና ማህበራዊ ዝግጁነትን፣ የተዋሃዱ ዓበይት ትምህርቶችን፣ የትብብር ትምህርትና የቡድን ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ሲሆን፣ ይህም በተማሪዎች ስኬት ላይ ያተኮረ ፈርጀ-ብዙ የእውኑ ዓለም አካዳሚያዊ አካባቢን ይሰጣል።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚከተሉት ኤፒ ኮርሶች ይሰጣሉ፦ ስቱዲዮ አርት/ስእል፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ የዩ.ኤስ. ታሪክ፣ ሳይኮሎጂ፣ አካባቢያዊ ሳይንስ፣ ባዮሎጂ፣ እና የሙዚቃ ቲዎሪ።

የዓለም ቋንቋ አቅርቦት ስፓኒሽና መንደሪንን ይጨምራል።

# የሙያ ትምሕርቶች ፕሮግራሞች በDCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

የDCP የሙያ ትምህርት ቢሮ ዓላማ ከወረዳው ከፍተኛ ደመወዝ፣ ከፍተኛ ብቃትን ከሚጠይቁ ሙያዎች አንጻር ትምህርት ቤቶቻችን ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ፕሮግራሞች እንደሚሰጡ ማረጋገጥ ነው:: እነዚህ ፕሮግራሞች የተነደፉት፣ ተማሪዎች በኮሌጅ እና በሙያ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት ነው:: በ2014-15 የትምህርት ዓመት በ15 ትምህርት ቤቶቻችን የሚማሩ ከ6,000 በላይ ተማሪዎቻችን ለCTE ፕሮግራሞች ተመዝግበዋል:: ከዚህ በማስከተል የወቅቱ የ CTE ፕሮግራሞች ማጠቃለያ የተቀመጠ ሲሆን፣ በእርሱም ስር ከእያንዳንዱ ፕሮግራም ጋር አግባብነት ያላቸው በኢንደስትሪ ዕውቅና ያላቸው የብቃት ማረጋገጫዎች ተካትተዋል::

| የትምህርት ቤት ስም | የሙያ ትምህርት ፕሮግራም | የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት |
|---|---|---|
| አናኮስቲያ | ህግ አስከባሪ | የለም |
| | የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት | • ሲፒአር (CPR)<br>• ብሔራዊ መዝገብ EMT |
| ባሎው | የብዙሃን መገናኛ እና ኮሙኒኬሽን | • Adobe CC: After Effects, Premier Pro<br>• Final Cut Pro X |
| | የመኪና ቴክኖሎጂ | • ASE የመኪና እና ቀላል ጥገና ምሥክር ወረቀት |
| | ባዮቴክኖሎጂ | የለም |
| | የምግብ ዝግጅት (በ2015-16 የትምህርት ዘመን የሚከፈት) | • ServSafe የምግብ ዝግጅት የምሥክር ወረቀት<br>• ProStart ብሔራዊ ብቃት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የሬስቶራንት ማሕበር) |
| | የመስተንግዶ ማኔጅመንት (ከሪር አካዳሚ) | • የተረጋገጠላቸው የመስተንግዶ አገልግሎት ባለሙያ<br>• የተረጋገጠላቸው የእንግዳ አቀባበል ወኪል<br>• የመስተንግዶ እና ቱሪዝም አመራር የምሥክር ወረቀት (አሜሪካን ሆቴል ኤንድ ሎጂንግ ኢንስቲቲዩት) |
| ባሎው ኤስቲኤዋይ | የምግብ ዝግጅት | • ServSafe የምግብ ዝግጅት የምሥክር ወረቀት<br>• ProStart ብሔራዊ ብቃት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የሬስቶራንት ማሕበር) |
| | ተራክቧዊ ሚዲያ (በ2015-16 የትምህርት ዘመን የሚከፈት) | • Adobe CC: Photoshop, After Effects, Premier Pro, Dreamweaver<br>• Maya |
| | ኮስሞቶሎጂ (Cosmetology)*<br>ጸጉር ማስተካከል* | • ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የጸጉር አስተካካዮች ፈቃድ |
| ካርዶዞ ኢሲ | ምህንድስና | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | ኤሌክትሮ-ሜካኒካል ቴክኖሎጂ | • ISCET (የተመሰከረላቸው የኤሌክትሮኒክስ ቴክኒሺያኖች ዓለም ዓቀፍ ማሕበር) |
| | ተራክቧዊ ሚዲያ (ከሪር አካዳሚ) | • Adobe CC: Photoshop, After Effects, Premier Pro, Dreamweaver<br>• Maya |

*ፕሮግራሙ በሙያ ትምህርት ቤት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት አይደለም::

| የትምህርት ቤት ስም | የሙያ ትምህርት ፕሮግራም | የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት |
|---|---|---|
| ኮሉምቢያ ሃይትስ ኢሲ | ምህንድስና | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | የመስተንግዶ ማኔጅመንት (ከሪር አካዳሚ) | • የተመሰከረለት የእንግዶች አገልግሎት ባለሙያ<br>• የተመሰከረለት የእንግዶች መስተንግዶ ወኪል<br>• የመስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት ፕሮግራም የምሥክር ወረቀት (አሜሪካን ሆቴል ኤንድ ሎጂንግ ኢንስቲቲዩት) |
| | ኮምፒውተር ሳይንስ | • CompTIA Security+ |
| | ኮስሞቶሎጂ (Cosmetology)* | • የኮሉምቢያ ዲስትሪክት የጸጉር አስተካካዮች እና የኮስሞቶሎጂ ፈቃድ ቦርድ |
| ኮሊጅ | የንግድ አስተዳደር | • ማይክሮሶፍት ኦፊስ ስፔሻሊስት የምሥክር ወረቀት |
| | የብዙሃን መገናኛ እና ኮሙኒኬሽን (በ2015-16 የትምህርት ዘመን የሚከፈት) | • Adobe CC: After Effects, Premier Pro<br>• Final Cut Pro X |
| ደንባር | ፋይናንስ | የለም |
| | የቅድመ ልጅነት (ህጻንነት) ትምህርት | • የሕጻናት እድገት ማህበር (CDA) |
| | ምህንድስና (ከሪር አካዳሚ) | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | የጫማ ጥገና* | የለም |
| ኢስተርን | የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት | • CPR<br>• ብሔራዊ መዝገብ EMT |
| | ባዮሜዲካል ሳይንስስ | የለም |
| ሉክ ሲ. ሙር | የንግድ አስተዳደር | • ማይክሮሶፍት ኦፊስ ስፔሻሊስት የምሥክር ወረቀት |
| | ተራክቧዊ ሚዲያ (በ2015-16 የትምህርት ዘመን የሚከፈት) | • Adobe CC: Photoshop, After Effects, Premier Pro, Dreamweaver<br>• Maya |
| የለም | ባዮቴክኖሎጂ | የለም |
| | ምህንድስና  (ከሪር አካዳሚ) | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | ኔትወርኮንግ/አይቲ (ከሪር አካዳሚ) | • CompTIA A+ & Security+<br>• Cisco CCENT |
| ፔልፐስ ኤሲኢ | አናጺነት | • NCCER የምሥክር ወረቀት |
| | ኤሌክትሪካል | • NCCER የምሥክር ወረቀት |
| | HVAC | • NCCER የምሥክር ወረቀት |
| | ብየዳ እና ላሜራ | • NCCER የምሥክር ወረቀት |
| | የቧንቧ ሥራ | • NCCER የምሥክር ወረቀት |
| | ኔትወርኮንግ/አይቲ (ከሪር አካዳሚ) | • CompTIA A+ & Security+<br>• Cisco CCENT |
| | ምህንድስና | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | አርኪቴክቸር እና ዲዛይን | • NOCTI አርክቴክቸራል ድራፍቲንግ |

*ፕሮግራሙ በሙያ ትምህርት ቤት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት አይደለም፡፡

| የትምህርት ቤት ስም | የሙያ ትምህርት ፕሮግራም | የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት |
|---|---|---|
| ሩዝቬልት | የንግድ አስተዳደር | • ማይክሮሶፍት ኦፊስ ስፔሻሊስት የምሥክር ወረቀት |
| | የምግብ ዝግጅት (የሕንጻ እድሳት እስኪጠናቀቅ ድረስ ተግባራዊ የማይደረግ) | • ServSafe የምግብ ዝግጅት የምሥክር ወረቀት<br>• ProStart ብሔራዊ ብቃት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የሬስቶራንት ማሕበር) |
| ሩዝቬልት<br>ኤስ ቲ ኤ ዋይ | ተራክቧዊ ሚዲያ (በ2015-16 የትምህርት ዘመን የሚከፈት) | • Adobe CC: Photoshop, After Effects, Premier Pro, Dreamweaver<br>• Maya |
| | የምግብ ዝግጅት (የሕንጻ እድሳት እስኪጠናቀቅ ድረስ ተግባራዊ የማይደረግ) | • ServSafe የምግብ ዝግጅት የምሥክር ወረቀት<br>• ProStart ብሔራዊ ብቃት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የሬስቶራንት ማሕበር) |
| | ጸጉር አስተካካይነት* | • የኮሉምቢያ ዲስትሪክት የጸጉር አስተካካዮች እና የኮስሞቶሎጂ ፈቃድ ቦርድ |
| | ኮስሞቶሎጂ* | • የኮሉምቢያ ዲስትሪክት የጸጉር አስተካካዮች እና የኮስሞቶሎጂ ፈቃድ ቦርድ |
| ዊልሰን | የብዙሃን መገናኛ እና ኮሙኒኬሽን | • Final Cut Pro X |
| | ፋይናንስ | የለም |
| | ምህንድስና | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| | ባዮሜዲካል ሳይንስስ | የለም |
| | ተራክቧዊ ሚዲያ | • Adobe CC: Photoshop, After Effects, Premier Pro, Dreamweaver<br>• Maya |
| | የመስተንግዶ ማኔጅመንት (ከሪር አካዳሚ) | • የተመሰከረለት የእንግዶች አገልግሎት ባለሙያ<br>• የተመሰከረለት የእንግዶች መስተንግዶ ወኪል<br>• የመስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት ፕሮግራም የምሥክር ወረቀት (አሜሪካን ሆቴል ኤንድ ሎጂንግ ኢንስቲቲዩት) |
| | ኮምፒውተር ሳይንስ | • CompTIA Security+<br>• AP Computer Science |
| ዉድሰን | ታዳሽ ኤነርጂ | • የኤሌክትሮኒክስ ቴክኒሻኖች ማሕበር፦ PV Installer, SW Installer, & Smart Grid<br>• RESNET የምሥክር ወረቀት: ኤነርጂ ኦዲቲንግ |
| | ኮምፒውተር ሳይንስ | • CompTIA Security+ |
| | ንግድ አስተዳደር | • ማይክሮሶፍት ኦፊስ ስፔሻሊስት የምሥክር ወረቀት |

*ፕሮግራሙ በሙያ ትምህርት ቤት መሥሪያ ቤት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት አይደለም፡፡

የDCPS ተጠሪ: ዶ/ር ኤሪን ቢቦ (Dr. Erin Bibo)፣ የኮሌጅ እና የሙያ ትምህርት ምክትል ኃላፊ (erin.bibo@dc.gov)

# በDCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሙያ ትምሕርቶች

ብሔራዊ አካዳሚ ፋውንዴሽን (NAF) የትምህርቶች ማዕከል በሦስት ዋና ዋና መስኮች ዙሪያ ይሠራል፡- ምህንድስና፣ መስተንግዶ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT)፣ እነዚህም በዲስትሪክቱ ከፍተኛ ደመወዝ ከሚከፈልባቸው እና በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ ከሆኑ ሥራዎች ጋር በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በአካዳሚው ሞዴል ውስጥ ጠንካራ የኮሌጅ እና የኢንደስትሪ አጋርነት፣ የሥራ ላይ ስልጠና እና በኢንደስትሪ ዕውቅና የሚገኝበትን የምሥክር ወረቀት ሚያስገኙ ቀጥተኛ ሥርዓተ ትምህርት ተካትተዋል፡፡ ሁሉም አካዳሚዎች በኢንደስትሪ አማካሪ ቦርዶች ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ ከቦርድ አባላት መካከል የአካባቢው የንግድ ተቋማት መሪዎች ይገኙባቸዋል፡ ፡ሁሉም የአካዳሚ ተመራቂዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የኮሌጅ ትምህርት ይከታተላሉ ብለን እንጠብቃለን፡፡

| # | የትምሕርት ቤት ስም | የአካዳሚው ዓይነት | የኢንደስትሪ እና ኮሌጅ አጋሮች | የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባሎው ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት | መስተንግዶ | • DC የመስተንግዶ ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ | • የተረጋገጠላቸው የመስተንግዶ አገልግሎት ባለሙያ እና የደንበኛ መስተንግዶ ወኪል የምሥክር ወረቀቶች (የአሜሪካ የሆቴል እና ሎጂንግ ማሕበር የትምሕርት ኢንስቲቲዩት)<br>• የደንበኞች አገልግሎት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የችርቻሮ ፌዴሬሽን) |
| 2 | ካርዶዞ EC | ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | • DC የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካሪ ቦርድ<br>• የኮሌጅ አጋርነትን ማጎልበት | • Adobe ACA Printshop, Dreamweaver, Flash, & Premier<br>• Maya |
| 3 | ኮሎምቢያ ሃይትስ EC | መስተንግዶ | • DC የምህንድስና ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ<br>• በሞንትጎምሬ ኮሌጅ ድርብ ምዝገባ (በሃሳብነት የቀረበ)<br>• በUDC ድርብ ምዝገባ | • የተረጋገጠላቸው የመስተንግዶ አገልግሎት ባለሙያ እና የደንበኛ መስተንግዶ ወኪል የምሥክር ወረቀቶች (የአሜሪካ የሆቴል እና ሎጂንግ ማሕበር የትምሕርት ኢንስቲቲዩት)<br>• የደንበኞች አገልግሎት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የችርቻሮ ፌዴሬሽን) |
| 4 | ደንባር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ምህንድስና | • DC የምህንድስና ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ<br>• ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ (PLTW) ለኮሌጅ ብቁ የሚያደርግ የትምህርት ኮርስ መገባደጃ ፈተናዎች<br>• በ PLTW አማካኝነት የኮሌጅ አጋርነት | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| 5 | ማክኒንሌ ቴክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ምህንድስና | • DC የምህንድስና ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ<br>• ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ (PLTW) ለኮሌጅ ብቁ የሚያደርግ የትምህርት ኮርስ መገባደጃ ፈተናዎች<br>• በ PLTW አማካኝነት የኮሌጅ አጋርነት | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |

| # | የትምሕርት ቤት ስም | የአካዳሚው ዓይነት | የኢንደስትሪ እና ኮሌጅ አጋሮች | የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት |
|---|---|---|---|---|
| 6 | ማክኒንሌ ቴክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | • DC የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካሪ ቦርድ<br>• የኮሌጅ አጋርነትን ማጎልበት | • Adobe ACA Printshop, ADA Dreamweaver, Flash, & Premier<br>• Maya<br>• CompTIA A+ & Security+<br>• Cisco CCENT |
| 7 | ፔልፕስ ኤሲኢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ምህንድስና | • DC የምህንድስና ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ<br>• ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ (PLTW) ለኮሌጅ ብቁ የሚያደርግ የትምህርት ኮርስ መገባደጃ ፈተናዎች<br>• በ PLTW አማካኝነት የኮሌጅ አጋርነት | • አውቶዴስክ የምሥክር ወረቀት ያለው የተጠቃሚ የምሥክር ወረቀት |
| 8 | ዊልሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | መስተንግዶ | • DC የመስተንግዶ ኢንደስትሪ አማካሪ ቦርድ<br>• በUDC ድርብ ምዝገባ | • የተረጋገጠላቸው የመስተንግዶ አገልግሎት ባለሙያ እና የደንበኛ መስተንግዶ ወኪል የምሥክር ወረቀቶች (የአሜሪካ የሆቴል እና ሎጂንግ ማሕበር የትምሕርት ኢንስቲቲዩት)<br>• የደንበኞች አገልግሎት የምሥክር ወረቀት (ብሔራዊ የችርቻሮ ፌዴሬሽን) |

# ይሳተፉ!

ከትምህርት ቤትዎ ጋር በዚህ ዓመት የበለጠ ተቀራርበው ይሰራሉ? ይህን ለማድረግ የሚችሉባቸው መንገዶች እነሆ!

- የትምህርት ቤትዎ የወላጅ ማህበር ወይም የአካባቢ ትምህርት ቤት መማክርት ቡድን አባል ይሁኑ።
- ስለ ትምህርት ቤት በመጠየቅ የልጅዎን የቤት ውስጥ ትምህርት ይደግፉ።
- በትምህርት ጊዜ ወይም ከትምህርት ቤት በኋላ ከተማሪዎች ጋር ያንብቡ።
- ተማሪዎችን በማስጠናት የህይወት ልምዶችዎንና እውቀትዎን ያካፍሉ።
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመስሪያ ቤትዎ በኢንተርንሺፖች ያስተሳስሩ።
- መጻህፍትን ለትምህርት ቤት በተ-መጽሃፍት ወይም ክፍሎች በስጦታ ያበርክቱ (ሆኖም በቅድሚያ ይጠይቁ!)።
- ከትምህርት ቤቶች ጋር በሚሰሩ ድርጅቶች ውስጥ የፈቃደኝነት አገልግሎት ይስጡ (ሁሉም ዓይነት ክሂሎት ተቀባይነት አላቸው!)።
- ለተጨማሪ መረጃ dcps.dc.gov/DCPS/volunteer ይመልከቱ።

## በእነዚህ ቦታዎች ያግኙን

### በትምህርት ቤት

ሰራተኞች መረጃ ለመስጠት፣ ጥያቄዎች ለመምለስ፣ ትምህርት ቤቱን ለማስጎብኘትና አሳሳቢ ጉዳዮችን ለመፍታት ሁሌም ዝግጁ ናቸው።

### ኦንላይን

ወቅታዊ መረጃ ለማግኘትና የተማሪዎችን ታሪክ ለማንበብ በየጊዜው dcps.dc.gov ይመልከቱ።

የDCPS ትምህርት ቤቶችን ህይወት የሚያሳዩ ፎቶዎችን ለማየት በቲዊተርና ኢንስታግራም ይከታተሉን:- @dcpublicschools።

ፌስቡክ ላይ ላይክ ያድርጉን:- facebook.com/dcpublicschools።

### በስልክ

ጥያቄዎች አልዎት? ለመርዳት ዝግጁ ነን:- 202.442.5612.

ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት ለ "DCPS" በስልክ ቁጥር 91990 ቴክስት በመላክ ይመዝገቡ። መደበኛ የዳታና መልእክት መላኪያ ክፍያዎች ሊጠየቁ የችላሉ።

### በማህበረሰቡ ውስጥ

ለDCPS ፕሮግራሞችና ተግባራት የበኩልዎን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ ዓመቱንሙሉ በሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ ለመገኘት ጥሪዎችን ነቅተው የጠባበቁ።